
# አደራ

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008




# የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን

# አደራ

**አደራ** በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ መፅሔት ስም ነው። የወቅቱ የታሪክ ባለተራ የሆነው የዛሬው ትውልድ አገራችን ካንዣበባት አደጋ ለማዳን አባትና እናቶቻችን ያቆዩል ሃገር መልሰን ለመጪው ትውልድ ለማሰረከብ የገባነው ቃል ኪዳን በድጋሚ ለማደስ ይህ መፅሔት አደራ ተብሎ ተሰይሟል። በመፅሔቱ ውስጥ የሚወጡ ጽሑፎች፣ አስተያየቶች፣ ሃሳቦች፣ ወዘተ… በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴን አላማ የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም የግለሰብ አቋሞች፣ አስተያየቶች፣ መልዕክቶች፣ ወዘተ… ማንፀባረቂያ መድረክም ጭምር ነው።

አደራ በየሶስት ወር የሚወጣ መፅሔት ነው። መፅሔቱን በይዘትም ሆነ በጥራቱ ለማሻሻል ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል። ለዚህም የአንባቢያን ተሳትፎ ከፍተኛ ድርሻ አለው።


አድራሻ: ADERA EDITORIAL BOARD
Postfach 1310

65782 Hattersheim

GERMANY

Email: aderametshet@yahoo.de

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

# ማውጫ

ከዝግጅት ክፍል ........................ 2
መልዕክት ................................. 3
ደብዳቤዎቻችሁ.............................. 4
የትዝብት አድማስ. ቁ.46...................... 5
ሴናተር ባራክ ኦባማ መመረጡንስ ....... 8
መጣጥፎች ሕገ ወጦች ሲጋለጡ............................ 12
ደርሶባችሁ ይሆን ?ክፍል አምስት ካለፈው የቀጠለ................ 14
መጣጥፎች.................................. 18
ግጥሞች...................................... 22
መጣጥፎች የአምባገነኖች ሥርዓት በኢትዮጵያ............ 25
ከታሪክ አምባ ጳውሎስ ኞኞ ........................ 32
ከግልፍተኝነት የእንካ ቴስታ !....................... 37

ከዝግጅት ክፍል

# ከዝግጅት ክፍል

የሀገራችን እጣ ፋንታ የሆነ ይመስል ሰንቆ የያዘን ድህነት፣ ረሀብ፣ በሽታ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት ተጨምሮበት በሀገራችንና በሕዝቦቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃው መጠኑን እያለፈ ከመጣ ጀምሮ ሃገሩን የሚወድ ሁሉ አፅዕኖት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

- ታዲያ እነዚህን ችግሮቻችንን እንዴት አድርገን መቅረፍ እንችላለን?
- መፍትሔውስ ምንድን ነው?
- የተረከብነውን አደራ የማስረከብ ሀላፊነት የለብንም?
- ቅድሚያ ልንሰጣቸው የሚገባቸው ምንድን ናቸው?
- ከእያንዳንዳችን ኢትዮጵያችን ከምንል ዜጎች ምን ይጠበቃል?
- የወያኔ መሰላሎች ምን ምን ናቸው?

በዛሬው እትማችን ወቅታዊሁኔታንና ከላይ የተጠቀሱ ጥያቄዎችን ሁኔታን አስመልክቶ የሚዳስሱ መጣጥፎች ግጥሞች ቀርበዋል መልካም ንባብ ተሳትፏችሁን አጠናክሩ።

ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በወያኔ ላይ ማዕቀቡን ያጧጡፍ!!!!!!!!
መልካም ንባብ
ቸር ይግጠመን።

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

# መልዕክት

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ከአውሮፓው ዞናል ኮሚቴ

ለኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን

መስከረም 2001 ዓ.ም.

በቅድሚያ ገድላዊ ሰላምታችንን እናስቀድማለን

ጉዳዩ የምስጋና ድብዳቤን ይመለከታል:-

ኢሕአፓ በአገራችን ለዘመናት ሰፍኖ የቆየውን የኋላቀርነት ሥርዓት ለመለወጥና በምትኩ የሁሉም ዜጎች መብትና እኩልነት የተከበረባት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ያልተቋረጠ ህዝባዊ ትግል የበኩሉን ሚና ሲጫወት መቆየቱ የሚታወቅ ነው:: ረጅም አመታትን ያስቆጠረው ህዝባዊ ትግል ዛሬም ግቡን አልመታም። በመሆኑም ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ህዝብ የገባውን ህዝባዊ የትግል ቃል ኪዳን ሳያጥፍ እነሆ ትግሉን ቀጥሏል:: በዚህ መራራና እልህ አስጨራሽ ህዝባዊ ትግል በርካታ የህይወትና የንዋይ መስዋዕትነት ተከፍሏል:: በተከፈለው መስዋእትነትም የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ዋንኛውን ሥፍራ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ ያስመዘገቡ ለመሆናቸው ታሪክ የሚዘክረው ነው:: በመሆኑም በጀርመን በኢሕአፓ ደጋፊነት በመሰባሰብ ለረጅም አመታት ኢሕአፓን በሁሉም መስኩ ለማጠናከር የአደረጋችሁት አስተዋጽኦ የሚያኮራና የሚያስመሰግን መሆኑን የኢሕአፓ የአውሮፓው ክፍል ሲገልጥ በታላቅ ኩራት ነው:: ለወደፊቱም ከዚህ ቀደም ስታደርጉት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ኢሕአፓ የመርዳትና የማጠናከሩን ተግባር በሁሉም መስኩ እንድትቀጥሉበት ከአክብሮት ምስጋና ጋር የትግል ጥሪአችንን እናቀርባለን::

በተባበረ ህዝባዊ ትግል የኢትዮጵያ ልዑላዊነት ይረጋገጣል።

እናቸንፋለን!!!

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

# ደብዳቤዎቻችሁ

## ከዝግጅት ክፍል

**የተለያየ ምክርና ማበረታቻ ላቀረባችሁልን ኢትዮጵያን ወገኖች በሙሉ የዝግጅት ቦርዱ ሳያመሰግን አያልፍም። ተሳትፏችሁ ይቀጥል። መፅሔቷ በየሶስት ወሩ የምትወጣ እንደመሆኑ. ፅሁፎቻችሁን ከተቻለ በኢሜል ካልሆነ በአድራሻችን ቀደም ብላችሁ ብትልኩልን ለስራችን ቅልጥፍናና ጥራት ይረዳናል።**

ለአደራ መፅሔት አዘጋጆች፣ በቅድሚያ የከበረ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል ተናፋቂ መፅሔታችሁ የምትወጣበትን ቀን በማወቄ ያቅሜን ያህል ጀባ ልበላችሁ ብዬ ነው። መቼም አንድ ጥግ እንደምትሰጧት አልጠራጠርም። የዘወትር ትብብራችሁ እንደማይለየኝ እተማመናለሁ።

ዳዊት ሚካኤል ከሄነፍ ጀርመን

አደራ አቶ ዳዊት ለተከበረው ሰላምታዎ ሰላምታችን ከእኛም ይድረስዎ።
በቅድሚያ ለአዲሱ አመት የላኩልን መልካም ምኞት መግለጫ በጣም እናመሰግናለን።ለእርስዎም መልካምና የብሩህ ተስፋ አመት እንዲሆንልዎ እንመኛለን። ፅሁፍዎን ጥግ አልነሳናትም።

ለተከበራችሁ የአደራ መፅሔት አዘጋጆች፣
እኔ ስሜ ከታች የተገለፀው ግለሰብ በአደራ መፅሔት ላይ እንዲወጣልኝ የላኩት አርቲክል ተመልክታችሁ በመፅሔቱ እንዲወጣልኝ ስጠይቅ በታላቅ ትህትና ነው።
ኤልዳ ኃይሉ
አደራ እህታችን ኤልዳ ሰላምና ጤንነት ለእርስዎም እንመኛለን።

ሰላም ጤና ይስጥልኝ የአደራ መጽሄት አዘጋጆች፣
ይህንን ግጥም በቀጣይ የሚታተመው መጽሄት ውስጥ ይታተምልኝ ዘንድ መልካም ትብብራችሁን እጠይቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር
ሚኪያስ ታደሰ

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የአስተዳደሩ ብልሹነት አምባገነንነቱ ነው።

ኢትዮጵያን በጠመንጃ ሀይል የተቆጣጠረው የወያኔ መንግስት ሕዝብን ሲያሰቃይና ሲገድል ይኸው 17 አመታት አልፏል። ለጊዜው እውነትና የጠመንጃ አፈሙዝ እኩል እንደማይሚገቱ እናውቃለን። ነገር ግን ባሩድ እየጨሰ፣ እየበነነ፣ እየተነነ በሄደ ቁጥር የጨረሰውን ጨርሶ ያቆሰለውን አቁስሎ የታሪክ ጠባሳና የሕሊና ቁስል ጥሎ መሄዱ የማይቀር ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ዕውነት እያደገች እየለመለመች የምትመጣበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግስት ኢትዮጵያ ምድር እየኖረ ኢትዮጵያዊነት የሚታፈንበት በአንፃሩም ዘረኝነት፣ ጎሰኝነት የሚኮራበትና የሚሞካሽበት ፣ በዓለም አቀፍ መድረክ የልመና አቅማዳቸውን ይዘው ሲዞሩ የአንድ ጎሳ ወገን ነኝ ብለው ሳይሆን ኢትዮጵያ ነን ብለው ነው። ታዲያ በኢትዮጵያ ሕዝብ እየተለመነ በዘረኝነትና በጎሰኝነት የሚነገደው እስከ መቸ ነው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህመሙና በሽታው የአስተዳደር ብልሹነት፣ የፍትህ መዛባት የእኩልነት አለመኖር፣ የሠላም እጦት እንጂ የዘረኝነት የጎሰኝነት ችግር አይደለም።

ኢትዮጵያ በአንድነቷ ለዘላለም ትኖራለች እናሸንፋለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!
ነቢላ ሰይድ (ካስል)

## ፓኖራማ ቁጥር 46

## የትዝብት አድማስ

## ጥቅምት 8 2001 ዓም

## የዕለት ጉርስ የዓመት ልበስ

"ርሀብ ከገደለው በሰይፍ የሞተው" እንደተባለው፥ ርሀብን ጥማትን፥ ዕርዛትንና ድኅነትን በትክክል ሊያውቅ የሚችለው፥ የእነርሱ ሰለባ የሆነው ሰው ብቻ ነው:: ተርቦ የማያውቅ ስለ ርሀብ፥ ታርዞ የማያውቅ ስለብርድ፥ ሊሰማው ቀርቶ ሲያልፍም የሚነካው አይሆንም:: አንድ ሰው፥ ሌላው ወገኑ የራበው፥ የጠማውና የተራዘ ወገኑን ሰያይ፥ምናልባት ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ወይም ህሊናው ካልሞተ ፥ ሊያዝ - ሊራራ ሊቸርም ይችላል:: የችግረኛውንም ጉስቁልና በመመልከት መንፈሱ ሊሸበርበት ይችልም ይሆናል:: እንደ ርሀብተኛውና እንደ ተጎጂው ግን፥ ጉዳቱ አይሰማውም፥ በተለይ በሕይወቱ ውስጥ ዕርቦት የማያውቅ ሰው፥ስለ ርሀብ ደንታ ሊኖረው አይችልም:: በዓለም ከሚኖሩ ጎስቋላ ዜጎች መካከል በድኅነት የሚማቅቅ ያው የኛው ሕዝብ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘ በመሆኑ፥ ስለድህነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስረዳት መሞከር ምናልባት፥ ምጥ ለእናቷ አስተማረች ይሆናል:: ያ ስለተባለ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የሚሄደውን የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግር ከማንሳት እንቆጠባለን ማለት አይደለም:: ቢያንስ ቢያንስ፥ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፥ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ እንደማያገኝ፤ የዓለም አቀፍ ጥናቶች በሀቅ የተደገፉ ማስረጃዎችን በመጥቀስ ያረጋግጣሉ:: ይህንን ሀቅ እያወቅን፥ የሀገራችንን ችግር መስማት አንገፍግፎናልና የራሱ ጉዳይ ነው በማለት በዝምታ ልናልፍ አይጠበቅም:: ስለሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ያለመታከት ከማንሳት አንታበይም:: ከቆምንበት ዓላማ ፍንክች አንልም:: የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮች በዘለቄታ መልኩ ለማስወገድ እንታገላለን::

"በገብስማ ዶሮ እየተመካኘ፥ የኔማ በሽታ ሰው ሆኖ ተገኘ" እንደተባለው፥ በሀገራችን ውስጥ ለሚከሰቱት ልዩ ልዩ ችግሮች፥ በየጊዜው የሚሰጡት ምክንያቶች ያው እንደተለመደው የተለያዩ ናቸው:: እስካሁን ግን ዋናውን በሽታና ምክንያት በአመዛኙ አልታሰበበትም:: ቢታሰብበትም እንኳ ጨርሶ መፍትሄ ሊገኝለት አልተቻለም:: የሀገሪቱን ችግሮች ለመቋቋምና ለመጋተርም እስካሁን የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ ግባቸውን መትተዋል ለማለት አልተቻለም:: ለኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች ምክንያቱ የፖለቲካ ችግር መሆኑን በተገቢው መልኩ አልተጤነም:: ግንዛቤው አለ ከተባለም መፍትሔ አምጪውን እርምጃ ለመወሰድና ከግቡ ለማድረስ እስካሁን አልተቻለም:: በዚህም ምክንያት ይመስላል፥ "በአየሩ ጠባይ እየተመካኘ፥ በዝናቡ ዕጥረት እየተመካኘ፥ የእኛው ችግርማ ፖሊቲካ ሆኖ ተገኘ" እያለ የሚያጉረመርመው ርሀብተኛው ሕዝብ:: ምንም እንኳን በየጊዜው ወቅቱን እየጠበቀ የሚከሰተው የዝናብ ዕጥረትም ሆነ አልፎ አልፎ የሚታየው የአየር-ንብረት መለዋወጥ በሰብሉ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ቀላል እንዳልሆነ ቢታወቅም፥ ረሃብ ከሀገራችን የማይወገድበት መሠረታዊው ምክንያት ፖለቲካዊ መሆኑ አሌ ሊባል አይችልም:: ይህንን ዛሬ የምናነሳው፤ እንደ አዲስ ክስተት ቆጥረን ሳይሆን፥ አሁንም ይህንን ምክንያት በሚገባ ተረድተን፥ ችግራችንን ለአንዴና ለምን ጊዜውም ቢሆን ለማስወገድ ዘለቄታ መፍትሄ መፈለግ ያለብን መሆኑን እንደገና ለማስገንዘብ ነው:: የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ የሚቆጣጠሩት ክፍሎች ሁሉ፥ ለሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ዋነኛዎቹ ምክንያቶች እስከሆኑ ድረስ፥ ረሀብም ሆነ በሽታ፥ መሃይምነትም ሆነ ድኅነት፥ ወደኋላ መቅረትም ይሁን ልመና ከምድረ-ኢትዮጵያ ሊወገድ ቀርቶ ሊቀረፈም አይችልም:: የምዕራባውያን ችሮታም ሆነ፥ የምግባረ ሰነይ ድርጅቶች ምፅዋት፥ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ብድር፥ ወይም ደግሞ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋጋታ ለችግራችን ሁሉ ዘላቂ መፍተሄ ያስገኙልናል ብለን ማመን ቀርቶ መመኘትም የለብንም:: ብዙዎቹ በችግራችን ላይ የሚነግዱና በዘለቄታውም የሚጎዱን ናቸው:: ሁሉም ትጠቅ- አስፈችዎችና የትኩረት አቅጣጫችንን የሚያስቱን ናቸው::ለአንድ ነፃ ሕዝብ ደግሞ፥ የሰውን እጅ ከማየት የበለጠ ቅስም የሚሰብርና እንደ እሳት የሚፋጅ ነገር የለም:: በውጭ ርዳታና ምፅዋት ያደገ፥ የበለፀገ ሀገር እስካሁን መኖሩን ማስታወስ ይቸግረናል:: ምናልባት አሣ መግቡን ብሎ ከመለመን፥ አሣ ማጥመድን አስተምሩን ማለቱ እራስን ለመቻል የሚረዳ ብልሃት መሆኑን ተገንዝበን፥መሠረታዊ የአገዛዝ ችግራችንን ካልፈታን ወይም፥ ባለው ዘዴ ሁሉ ተጠቅምን፥ የራሳችንን ችግር ለመፍታት ታጥቀን ካልተነሳን፥ የልመና አቁማዳችንን ይዘን ብንከራተት መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን አልፈን ለችግራችን ዘላቂ መፍተሄ አናመጣም:: የክፍለ ዘመናችን ሕዝብ የሚመዘነው፥ የሚገመተው፥ የሚገመገመው፥ የሚለካውና የሚፈረደው፥ በኑሮ ደረጃው ዕድገት፥ በምጣኔ ሀብቱ መደርጀት፥ በሳይንስና ቴክኖሎጅው ምጥቀት እንጅ ባለፈ ታሪኩ ገናንነት ብቻ አይደለም::

ወይም በዕድሜው ርዝማኔ አይደለም፡፡

የባለ ሦስት ሽ ዘመን ታሪክ ባለቤቶች መሆናችን ብቻ፥ ለሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ለሚኖር ሕዝብ መስፈርት ይጠቅመናል ብለን ማመን እንቸገራለን፡፡ ዝንት ዓለማችን ስለአድዋ ጦርነትና ድል፤ ስለማይጨው ወረራና ጥቃት፥ ስለኃይለ ሥላሴ ጭቆና ስለመንግሥቱ ኃይለማርያም ጭፍጨፋና ፍርጠጣ፥ ስለውጭ ጣልቃ ገብነት፥ወይም ያን የታገለን ትውልድ አላግባብ በመተቸት ወዘተ ለችግሮቻችን ሁሉ ሰበብና ማጠየቂያ እየፈለግን መኖር አይገባንም፡፡ የዛሬው ትውልድ የራሱን የወቅት ችግር መፍታት ኃላፊነትም ግዴታም እንዳለበት ካልተገነዘበ፥ ያለፈውን እየተቸን ብቻ በመገኘትና ትግልንም በመሸሽ ለኢትዮጲያ ችግር መፍትሔ አናመጣም፡፡ በድርጊታቸው እያፈሩና እየፈሩ ከኢትዮጵያ መፈርጠጥ ያለባቸው ወያኔዎቹ እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊሆን አይችልም፡፡ አይገባውምም፡፡

ህልውናውን በይፋ የዛሬ 36 ዓመት ያወጀው ኢሕአፓ፥ ለሀገራችን ችግር ከከንፈር መምጠጣ ባሻገር፥ ጠንክሮ መስራትና ውጤት ማስመዘገብ አለብን ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም፥ ፓርቲው፥ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ደኅንነትና ለዜጎቿም ጥቅምና ክብር ሲል አይከፍሉ መሥዋዕ እንደከፈለ እንኳንስ የሚታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ፥ ጠላቶቹም ቢሆኑ ሳይወዱ በግድ የሚቀበሉት ታሪካዊ ሃቅ ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን የሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ተልዕኮ ለመፍትሔው ስኬት መታገል እንጂ ስል ችግር ማውራት ብቻ ሊሆን አይገባም ብሎ ኢሕአፓ ያምናል፡፡ ይህም በመሆኑ፥ለችግራችን መወገድ ቅድሚያ ካልሰጠነው፥ ብሎም እሱን ለማስወገድ ካልተረባረብን ለምን ጉዳይ እንደምንተባበር ለመረዳት ያስቸግረናል፡፡ እኛ እኮ ርሀብተኞች ነን፥ ታርዘናልም፡፡ ድሆችም ነን፡፡ ህይወታችን ሁሉ በርዳታ፥ በብድርና በምፅዋዕት ዙሪያ ያጠነጠነ ነው፡፡ በሽታና ድኅነት፥ ኋላቀርነትና መኃይምነት የብሔራዊ ገፅታችን መታወቂያ መሆኑን ዓለም ካወቀው ከአርባ ዓመታት የሚቆጠር ዕድሜ አስመዝግበናል፡፡ አሁንም እኮ በማስቆጠር ላይ ነን፡፡ የመጀራ ዕድሜ ማስቆጠሩን አቁመን አዲስ የብሩኅ ተስፋ ራዕይና አቅጣጫ ለማምጣት አዲስ ምዕራፍ መክፈት ያለብን ይመስለናል፡፡ ጨርሶ ሰማይ-ምድሩ ካልተደፋብን በስተቀር፥ ይህን ማድረግ የሚሳነን ዜጎች አይደለንም፡፡ ምክንያቱም ከማንም በፊት የራሳችን ፊደል፥ ሥነጽሁፍ፥ የህንፃ ሥራና የመንግሥት አስተዳደር የነበረን ዜጎች በመሆናችን ነው፡፡ “የመጀመሪያዎቹ የመጨረሻ ይሆናሉ” ካልተባልን በስተቀር፥ ሌላው ቢቀር፥ ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን መግባታችንን አውቀን፥ ብሔራዊና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመመሥረት ከአሁኑ ቅድመ-ዝግጅት ለማድረግ መሰናዳት ይኖርብናል፡፡ “ኢትዮጵያ ታበፅኅ እደዊኃ ሀበ ምዕራብያውያን” የሚባልብንን ምፀት ማስቆም አለብን፡፡ በዚህ ምትክ ግን ኢትዮጵያ በራሷ እየተማመነች፥እጆቿንና ኃይሏን ወደወንዞቿ፥ ማዕድኗ፥ ወደከርሰ-ምድር ኃብቷ መዘርጋት አለባት፡፡ ለትጉኅ ሠራተኛ ሕዝብ ደግሞ ይህ ከባድ አይሆንም፡፡ ሌላ ሌላውን ለጊዜው እንተወውና፥ ዛሬ ከማነኛውም ጉዳይ በበለጠ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን፥ የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ ሁሉም ዜጋ የሚያገኝበትን ማረጋገጥ እንደሆነ ማንም ሊነግረን አይገባም፡፡ አንድ ሀገር ከሁሉ በፊት ማድረግ ያለበት፥ በርሀብ ምክንያት እንደቅጠል የሚረግፉትን ዜጎች ማዳን ነው፡፡ ረሀብና ጠኔ ጊዜ የማይሰጡ አደገኛ ጠላቶች መሆናቸውን ለእኛ ኢትዮጵያውያን ማንም አስታዋሽ ሊነግረን የሚያስፈልገን አይመስለንም፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ፥ እንዲያው በምኞትና በዘፈቀደ የሚሆን አይደለም፡፡ ለሀገር አሳቢ፥ ለወገን ተቆርቋሪ፥ ለታሪክ ቀናዒ የሆነ ብሄራዊ መንግሥት እንዲመጣ ያስፈልጋል፡፡ ይህ እስካሁን የለም፡፡ ብሄራዊ ተልዕኮና ራዕይ ያለው መንግሥት የላትም ዛሬ ኢትዮጵያ፡፡ ከምኒልክ ግቢ መሽጎ የተቀመጠው ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን፥ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም እንዳልቆመ፥ የ17 ዓመታት ተግባሩና ባኅርዩ አረጋግጠዋል፡፡ አፈጣጠሩና ዕድገቱ፥ አሁንም የሚኖርበት ሕይወቱ፥ ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ጥፋት እንጅ ልማት እንዳልሆነ ማንም ዜጋ የሚጠራጠር ባለመሆኑ፥ በዚያ ላይ ጊዜውን የሚያጠፋ ኢትዮጵያዊ ሊኖር አይችልም። ሁሉም ወደ መፍትሄውና ወያኔን ለማስወገድ፥ ብሎም ከወያኔ በኋላ ሊሆን ስለሚገባው ብሔራዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባው ሁሉም የተስማማበት ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ፥ የመፍትሄው ፍለጋ የመጀመሪያ ርምጃ ስለሚሆን የሚደገፍና የሚበረታታ ው፡፡ ለዚህ ተግባር በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነቱና ተግባሩ የተጣለበት ወያኔን፥ ያለማወላወል አስወግዶ በዴክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት ቆርጦ የተነሳው የፖለቲካ ኃይል ብቻ ነው ፡፡ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ፥ ብሎም መጠጊያ ጎጆ ለመቀል-በስ በግድ፥ ለሕዝብ፥ ለሀገርና ለወገን የሚያስብ መንግሥት መቋቋም አለበት፡፡

*ይህንን ለማስገኘት የሁሉም ዜጋ ዓይነተኛና የግንባር-ቀደም አጀንዳ መሆን አለበት ብለን እናምናልን። ተወደደም ተጠላ፥ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግር የሚያጠነጥነው በአመዛኙ በፖለቲካ ዙሪያ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ከሆነ ውሎ አድሯል። የፖሊተካ ችግር ሲባል፥ የኢትዮጵያን የፖሊቲካ ሥልጣን የያዘው ክፍል፥ የችግሩ ሁሉ መንስዔና በግምባር ቀደምም ተጠያቂው እርሱ ነው ማለታችን ነው። ተጠያቂነቱም ችግር ፈጣሪው እርሱ እራሱ መሆኑን እያወቀ፥ መፍትሄ ለመፈለግ ደንታ ቢስ በመሆኑ ነው። የአንድ ሀገር መንግሥት፥ አስተዳድረዋለሁ ለሚለው ሕዝብ፥ ለሕይወቱ ፥ ማለት ለኑሮው፥ ለደኅንነቱ፥ ለጤናው፥ ለትምሕርቱ፥ ለልማቱ፤ ለዕድገቱ፥ ወዘተ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት ካላወቀና ግዴታውንም ካልተወጣ በሥልጣን ላይ የሚቆይበት አንዳችም ምክንያት አይኖረውም። መውረድ አለበት። በግድም ሆነ በውድ። በኢትዮጵያ ታሪክ ደግሞ መንግሥት በውድ ከሥልጣኑ የወረደበት ጊዜ አልታየም። በግድ እየመጣ በግድ ከመውረድ በስተቀር!*

*የመንግሥት መሰየም ለሕዝብ ጥቅም እንጅ፥ የተገላቢጦሽ ሊሆን አይችልም። የፖለቲካ ችግር ደግሞ ሰው-ሠራሽ ነው። ሰው-ሠራሽ ችግር የሚፈታው ደግሞ በራሱ ችግሩን በፈጠረው በሰውየው ነው። የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግር፥ ወጣም ወረደ የፖሊቲካ ችግር ነው የሚባለውም በዚህ ረገድ ነው።*

*ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በርሀብ ይረግፋሉ። ከድኅነቱና ከረሃቡ ክፋት የተነሳ ዛሬ በአዲስ አበባ አንድ ሰው ረሀቡን ለማስታገስ አንድ ጉርሻ ትራፊ በአንድ ብር እየገዛ እንደሚቀምስ የሚያዩ ሁሉ የሀፍረት ሀዘናቸውን ይገልፃሉ። ይህ አሳዛኝና አሳፋሪ ትዕይንት ለኢትዮጵያ አዲስ ክስተት ሆኗል። በአያሌ ሽዎች የሚቆጠሩት በወሀኒ ቤቶች ይማቅቃሉ። ሀገሩን እየለቀቀ የሚሰደደው ዜጋ፥ ቤቱ ይቁጠረው ተብሏል። ኤች አይ ቪ ወይም ኤይድስ የሚባል ዘመን አመጣሽ በሽታ መቅሰፍት ሆኖ ኀልቁ መሳፍርት የሌለውን ዜጋ እየቀጠፈው ይገኛል። በኑሮ ችግር አስገዳጅነት ወደ መካከለኛው ምሥራቅና የዐ ረብ ሀገሮች በመሰደድ፥ ለአሳፋሪ ተግባርና ውርደት የሚዳረጉት የሀገራችን ወጣት ሴቶች ሁኔታ የኀሊና ዕ ረፍት የሚሰጥ አልሆነም። ይህ ክስተት በተለይ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነው። የፖለቲካው ችግር ያመጣውን ሰቆቃና መከራ ዘርዝረን አንጨርሰውም። ስለሆነም፥ በድኅነትና በጭቆና የሚገዛ አምባገነን ዘ ረኛ ሥርዓት ማስወገድ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን ተገንዘበን፥ ወያኔን ማስወገድ እንዳለብን፥ ሌላ አስታዋሽና ጎስጓሽ ሊኖረን አይገባም። ይህ እስካልሆነ ድረስ፥የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ማጣታችን እስከ ፍፃሜ-ዓለም ይቀጥላል።*
*የኢትዮጵያ ሕዝብ ታታሪና ላቡን አንጠፍጥፎ ሊያመርት የሚጥር ነው። ኢትዮጵያ በተፈጥሮ አልተበደለችም። የችግሯና የውርደቷ ምንጮች ግን በሥልጣን ተሰይመው ሕዝብን የሚበዘብዙ ስግብግብ ገዢዎቹ ናቸው። ዛሬ የኢትዮጵያ መከራና ስቃይ የዘረኛው የወያኔ ቡድን አፀያፊ ሥርዓትና ፖለቲካ ውጤት ነው።*

*ለአንዴም ለሁሌም ከችግር ማጥ እንድንወጣ፥ ከችግር አረንቋ ገብተን እንድንማቅቅ ያደረገንን ይህን ዘረኛና መሰሪ አረመኔ የወያኔ አገዛዝ በትግል ማስወገድ አለብን። ሌላ መፍትሄ ከቶም የለም። ከሁሉ በፊት በሀገራችን ሠላም ሊመጣ ግድ ይላል። ከዚያም የመጀመሪያው አጀንዳችን ሕዝባችን ቢያንስ የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን የሚያገኝበትን ሁኔታ በአስቸኳይ ማመቻቸት ሊሆን ይገባል። ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ከመከራ ወደ ባሰ የመከራ ሁኔታ ዜጋችን የሚጓጓዝበትን ክስተት ለአንዴም ለሁሌም ማስወገድ አለብን ብለን ቆርጠን በመነሳት የሀገራችንን የጥፋት ሂደት ማስቆም አለብን። ሁላችንም በመተባበር!!!!*

# ሴናተር ባራክ ኦባማ መመረጡንስ ይመረጡ፤ ለእኛ ግን ያው "በገሌ ነው"

ከምሕረት ሰጠኝ

ሴናተር ባራክ ኦባማ የመጀመሪያው ጥቁር የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆነው ቢመረጡ ታላቅ ታሪካዊ ሁኔታ እንደሚሆን አይጠረጠርም። አሜሪካ ውስጥ ለዘመናት በጥቁሮች ዘር ላይ ከባርነት አንስቶ ከፍተኛ ጭቆና፣አድልዎና ንቀት እንዲሁም በርካታ ኢሰብአዊና ዘግናኝ በደሎች ሲፈጸሙባቸው የቆዩ በመሆኑ፤አሜሪካ ውስጥ ከጥቁሮች ዘር የወጣ ሰው ፕሬዝዳንት ሆኖ ለመመረጥ ከቻለ፤አሜሪካ ውስጥ የነጭ የበላይነት እየተፋቀ መሄዱንና አገሪቱ ለሁሉም ዘሮች እኩል እድል የምትሰጥ መሆኗን የሚያመላክት ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው ቀርቶ ሴናተር ኦባማ የፕሬዝዳንት ክሊንተንን መረብ መበጣጠስ መቻላቸውና በአጭር ጊዜ ውስጥ በብሔራዊ ደረጃ ታዋቂነትና ተወዳጅነትን በማግኘት በዲሞክራቲኩ ፓርቲ ለፕሬዝዳንትነት መታጨት መቻላቸው ብቻ ትልቅ እንድምታ ያለውና ለወደፊቱም አሜሪካ ውስጥ ለሚኖሩ ጥቁሮችና ሌሎች አናሳ በመባል ለሚጠሩት ህዝቦች ፋና ወጊ እንደሚሆንላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ሴናተር ባራክ ኦባማ ለስምንት ዓመታት በፕሬዝዳንት ቡሽ መስተዳድር የወደቀውን የአገሪቱን ኢኮኖሚ ሊያሻሽሉ የሚችሉ እርምጃዎችን እንደሚወስዱና አገሪቱ በዓለም አቀፍ ግንኙነትዋ የደረሰባትን ጥላቻ ሊያስተካክሉ እንደሚችሉ ይጠበቃል። ሴናተር ኦባማ የውጭ ፖሊሲን በተመለከተ ግጭቶችን በውይይትና በድርድር እንዲፈቱ እንደሚያደርጉና አሜሪካ ከመፈራት ይልቅ በመወደድ ላይ የተመረካዘ የውጭ ፖሊሲ ይኖራታል በማለት በተደጋጋሚ ተናግረዋል። በመሆኑም በአሜሪካ የውጭ ግንኙነት አፈጻጸም ላይ ለውጥ ሊመጣ እንደሚችልና ፕሬዝዳንት ቡሽ ከአንዳንድ አገሮች ጋር የፈጠሩት አላስፈላጊ ውጥረት ሊረግብ እንደሚችልም ይጠበቃል።

በአሜሪካ ውስጥ የሚካሄደው የፕሬዝዳንት ምርጫ ውድድር የበርካታ ኢትዮጵያዊያንም ቀልብ የሳበ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሴናተር ኦባማ ፕሬዝዳንት ሆነው ቢመረጡ፣ የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ኢትዮጵያን በተመለከተ ሊለወጥ ይችል ይሆናል ከሚል እምነት የመነጨ ነው። ሆኖም የሴናተር ኦባማ የውጭ ፖሊሲ የአፍሪካ አህጉርና በተለይም ኢትዮጵያን በተመለከተ ያራምዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችለውን በጥንቃቄ ብንመረምር የምናገኘው ውጤት ብዙዎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በስሜትና በጉጉት ከምንጠብቀው ጋር የሚጣጣም አይመስልም። ይህንንም ከዚህ በታች በዝርዝር እንመልከት፣

1. ሴናተር ኦባማም ሆኑ ከእርሳቸው ጋር አብረው ለምርጫ ዘመቻው የሚንቀሳቀሱት ባልደረቦቻቸው የውጭ ፖሊሲን በተመለከተ ከአፍሪካ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ሊያመጡ ያቀዱትን ለውጥ በተጨባጭ ሁኔታ ይፋ አላደረጉትም። እንደውም እስከ አሁን ባለው መረጃ መሠረት የአፍሪካ አህጉርን በተመለከተ የዳርፉር ግጭትንና በደፈናው ድህነትን መቀነስና በሽታዎችን ማጥፋት ከሚል በስተቀር በፖሊሲ ደረጃ የተቀመጠ ከሴናተር ኦባማ አካባቢ የመጣ ምንም ዓይነት ፍንጭ የለም። ይህንንም የሴናተሩን ድረ-ገፅ በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል። ከዚህም በመነሳት ሴናተሩ ከበፊቶቹ ፕሪዝዳንቶች የተለየ ለአህጉሩ የሚጠቀም ተግባር ይፈጽማሉ ብሎ ለመገመትአያስችልም።

2. ሴናተር ኦባማ ያቀዱትን የውጭ ፖሊሲ ብንመለከት ለምሳሌ ሽብር ፈጠራ መዋጋትን በተመለከተ የእርሳቸው መስተዳድር በአፍጋኒስታንና በሌሎች አገሮች ውስጥ የሚካሄደውን ዘመቻ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥሉበት አስታውቀዋል። በመሆኑም አሜሪካ በሽብር ፈጣሪዎች ላይ የከፈተችው ጦርነት ብቻዋን ተዋግታ ለማሸነፍ የምትችለው ዓይነት ጦርነት ስላይደለ በአጋዥነት ከእርሷ ጋር የተሳተፉት ወዳጆቿ ጋር ያላትን ግንኙነትን ትቀጥልበታለች ማለት ነው። ይህም በዚህ ጦርነት ላይ ከተሳተፉ አምባገነንና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችም ጋር ይካሄዱ የነበሩ ግንኙነቶች ይቀጥላሉ ማለት ነው። ይህ ለጥቅም ሲባል ከአምባገነን አገሮች ጋር የሚካሄድ ወዳጅነት አሜሪካ ውስጥ የተለመደና በተደጋጋሚ በዲሞክራቲክም ሆነ በሪፐብሊካን መስተዳደሮች ተግባራዊ ሲሆን የኖረ ነው። ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ ወዲህ እንኳን በፕሬዝዳንት ክሊንተን የተሰራበት ሲሆን አሁንም በፕሬዝዳንት ቡሽ በስፋት እየተሰራበት ይገኛል።

አሜሪካ ከወያኔዎች የምትፈልገው ጥቅም እስካለ ድረስ ማንኛውም ዲሞክራቲክም ሆነ ሪፐብሊካን ፕሬዝዳንት ቢመረጥ ግንኙነቱ ሳይለወጥ መቀጠሉ አይቀርም። ይህንን በዲሞክራቲኩ ፕሬዝዳንት ክሊንተን ጊዜ እንዴት ይካሄድ እንደነበር ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንቃኝ፣ ሴናተር ኦባማም ሊያካሂዱት ካቀዱት ጋር ያለውን መስተጋብር ሊያሳየን ይችላል። ፕሬዝዳንት ክሊንተን እንደ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ የውጭ ፖሊሲያቸው በፀረ ሽብርፈጣሪነት ላይ ያነጣጠረም እንኳ ባይሆን፣ ለምሳሌ የሱዳንን መንግሥት ለመገልበጥ የአገሪቱን ገዥ ፓርቲ የሆነውን "ብሔራዊ እስላማዊ ግንባር" በሽብር ፈጣሪነት በመፈረጅ በተቀነባበረው ሴራ የሱዳን አጎራባች የሆኑና የራሳቸው የሆነ ችግር ከሱዳን ጋር የነበረባቸውን ሶስት ከወንበዴነት ወደ መንግሥታትነት የተሸጋገሩ የኢሳያስ፣የመለስና የሙሴቬኒ (ዩጋንዳ) አገዛዞችን በአንድ ቡድን ውስጥ አሰባስበው እርዳታ በመስጠት መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ እንደሚባለው "የአዲስ ትውልድ መሪዎች" (New Generation of Leaders) የሚል ስም በመስጠት ሲንቀሳቀሱ እንደነበር አይዘነጋም።

ይህ ቡድን ወያኔና ሻቢያ ሲዋጉ ሊፈርስ በቅቷል። እንደውም ሻቢያና ወያኔ ሱዳንን በጦርነቱ እንድትረዳቸው በየፊናቸው መለማመጣቸው የፕሬዝዳንት ክሊንተን ፖሊሲ በአሳፋሪነት እንዲከሽፍና እንዲመክን አድርጎታል። የፕሬዝዳንት ክሊንተን መስተዳድር ምንም እንኳ ለወያኔና ሻቢያ ቀለብ ሰፋሪ የነበረ ቢሆንም እነዚህ ከዓለም በድህነት በአንደኛ ተርታ የሚገኙና ህዝባቸውን ለመመገብ እንኳ የተሳናቸው አገሮች ዓላማና ምክንያትና ለሌለው ጦርነት በርካታ ገንዘብ ሲያፈሱና የጦር መሳሪያ ከውጭ በገፍ ሲሸምቱ ጦርነቱ እንዳይጀመር ለማድረግና ከተጀመረም በኋላ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ሳይቀጥፍ ለማስቆም አልቻሉም ነበር። መለስና ኢሳያስም በዚሁ ጊዜ እርስ በርሳቸው በአምባገነንነት በመወጋገዝ ከአሜሪካ የበለጠ ተወዳጅነት ለማግኘት ሲወራጩ የነበረበት ጊዜ ነበር።

የፕሬዝዳንት ክሊንተን መስተዳድር እነዚህ ለአብነት ያህል እዚህ የተጠቀሱ የኢሳያስ፣የመለስና ሙሴቬኒ አምባገነን አገዛዞች ከረዥም ጊዜ ጦርነት በኋላ ሥልጣን ላይ እንደወጡና ጫካ በነበሩበት ጊዜ ለበርካታ የአገራቸው ንጹሃን ዜጎች ሰቆቃ፣እልቂት፣ንብረት ዘረፋና ውድመት እንዲሁም ለሌሎች ከፍተኛ ወንጀሎች ተጠያቂ መሆናቸውና ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጡም በኃላ "ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ" እንደሚባለው የዲሞክራሲ መብቶችን በመርገጥ፣የሰብዓዊ መብቶችን በማፈን ህዝባቸው ላይ ሳንጃ ወድረው የሚገዙ መሆናቸው በስፋት እየታወቀ ከሌሎች የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ አገሮች ተለይተው ለወጃጅነት ተመርጠዋል። ዲሞክራቱ ፕሬዝዳንት ክሊንተን ሲያወድሷቸው የነበሩት እነዚህ አገዛዞች ከበርካታ የአፍሪካ ገዥዎች በበለጠ አፋኝ፣ አምባገነንና ሰብዓዊ መብት ረጋጭ ቢሆኑም አገሮቹ ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ሁኔታው ተገልብጦ የአሜሪካ የጥብቅ ወዳጅ ሆነው የወታደራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊና ሌሎችንም እርዳታ ከአሜሪካን ይሰጣቸው ነበር።

ከላይ የተመለከተው የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ አፈፃም የተለያየ ገፅታና መልክ ቢኖረውም አዲስ ግን አይደለም። ይህ አሰራር "ብሔራዊ ጥቅም" በመባል ይታወቃል። የአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅም ተብሎ በሌሎች አገሮች ላይ በተለያዩ ስልቶች ተፈፃሚ የሚሆኑ ፖሊሲዎች በዲሞክራቲኩም ሆነ በሪፐብሊካን መስተዳድሮች ሲሰራባቸው የኖሩና ተቀባይነት ያገኙ አሰራሮች ናቸው።ማንኛውም አገር ትልቅም ሆነ ትንሽ የራሱ የሆነ ብሔራዊ ጥቅም አለው። ብሔራዊ ጥቅም በአገሮች መካከል ባለ ግንኙነት ውስጥ አብይ ቦታ የሚይዝ ነው። እያንዳንዱ አገር ብሔራዊ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የሚያራምደው ፖሊሲ በወታደራዊ፣በንግድ፣በባህልና በሌሎችም መስኮች የሚጸባረቅ ነው። ዲሞክራሲያዊ የሆነ የመንግሥት አወቃር ያላቸው ለምሳሌ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ካናዳ፣ ፈረንሳይ፣ህንድ የመሳሰሉትና እንዲሁም አምባገነን መንግስታት እንደ ቻይና፣ የመሳሰሉት ከሌሎች አገሮች ጋር ባላቸው ግንኙነት የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። ስለሆነም ለብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማሟላት አገሮች ከፍተኛ እንቅስቃሴና ጥረት ያደርጋሉ። አገሮች ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚል ሽፋን በሌሎች አገሮች ላይ ኢሰብዓዊና ህገወጥ ድርጊቶችን ፈጽመዋል። ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል ምክንያት በርካታ አገሮች ውስጥ በተለያዩ ጊዜዎች ህጋዊ መንግሥታት ተገልብጠዋል፣ በህዝብ የተመረጡ መሪዎች ተገድለዋል፣ንጽሃን ዜጎች ተጨፍጭፈዋል፣ምርጫዎች ተጭበርብረዋል፣ የኢኮኖሚ አሻጥሮች ተፈጽመዋል፣ የሰብዓዊ መብቶች ተገፈዋል እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች ተደርገዋል።

በዓለም ላይ እንደ አገር ብሔራዊ ጥቅም የሌላት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው አገዛዝ የአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን የማያስከብር እንዲሁም የህዝቡን አንድነትና ደህንነት የማያስጠብቅ በጠባብ የጎሳ ጥቅም ናላው የዞረ የቅጥረኞች ቡድን የሆነው ወያኔ ነው። ወያኔ በኢትዮጵያ አገራዊ ልእልና ላይ አምጾ ነፍጥ በማንሳት ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ አገሪቱን በጎሳ ከፋፍሎ፣አዳክሞና በረሃብ እየቆላ በመግዛት ላይ ያለና ከሥልጣን በሚወገድ ጊዜ አገሪቱን በታትኖ ወደተነሳበት መንደር ለመወተፍ ዝግጅቱን አጠናቆ ጊዜውን በመጠበቅ ላይ የሚገኘው የትግራይ የገዥ መደብ ነው። ይህ የገዥ መደብ ለጠባብ የጎሳ ጥቅም ማስገኛና በሥልጣን ላይ ተፈናጦ ለመኖር የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት ላይ የሚገኝና ምንም ዓይነት ብሔራዊ ስሜት፣ተቆርቋሪነትና አመለካከት የሌለው የቀጣሪዎቹን ጥቅም ለማስከበር የቆመ የነፍሰ ገዳዮች ጥርቅም ነው።

አሜሪካ "በሽብር" ላይ የከፈተችው ጦርነት በቀላሉና በተወሰነ ጊዜ ያልቃል ተብሎ ሊገመት የሚችል ስላይደለና እንደነ መለስ ዜናዊ ዓይነት እራሳቸውን እንደ ሸቀጥ ለሽያጭ ያቀረቡና "ሳይጠሯቸው አቤት፣ ሳይልኳቸው ወዴት" የሚሉ ሰው ሆነው ተፈጥረው እነሱ ግን በውሻነት ጌቶቻቸውን ለማስደሰት ጭራቸውን የሚቆሉ፣ ህዝባቸውንበጠላትነት ፈርጀው ከባእዳን እርጥባን በመቃረም በስልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠው ለመቆየት የሚቅበዘበዙ ነፈሰበላዎች እስካሉ ድረስና ዲሞክራሲያዊ የሚባሉ አገሮች አሜሪካንን ጭምር እንደነዚህ ዓይነት ታዛዦች መኖራቸውን ስለሚፈልጉና እንዲኖሩም ስለሚያደርጉ፣ ሴናተር ኦባማም ከዚህ ለዘመናት ሲሰራበት ከቆየ አሰራር ውጭ ይወጣሉ ብሎ ለመገመት አይቻልም። ሴናተር ኦባማ በሽብር ላይ በመካሄድ ላይ ባለው ጦርነት ከእነ መለስ ዜናዊ ዓይነትነፈሰ ገዳዮች የሚቀርብላቸውን የትብብር ጥሪ በደስታ የሚቀበሉ እንጅ የእነሱን ማንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአምባገነኖች ጋር አብሬ አልሰራም በማለት እነመለስ ዜናዊን ፊት ይነሳሉ ማለት ከእውነታ ውጭ መሆን ነው።

እ.አ.አ. በኦክቶበር 2008 "የሰብዓዊ መብት ተመልካች" (Human Rights Watch) የተባለው የሰብዓዊ መብት ተካራካሪ ድርጅት ባወጣው ሪፖርት ከዩናይትድ ስቴትስ፣እንግሊዝና ካናዳ ጨምሮ ከ18 አገሮች የመጡ ቁጥራቸው 150 የሚሆኑ

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

እስረኞች ለሁለት ዓመታት ለፍርድ ሳይቀርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ በእስር ሲማቅቁ የቆዩ መሆናቸውን አስታውቋል። እነዚህ እስረኞች ከአሜሪካ በመጡ መርማሪዎች ምርመራ የተደረገባቸው መሆኑንና ሰቆቃም የተፈጸማባቸው እንደሚገኙና ከነዚህም ሌላ ቁጥራቸው 22 የሚሆን የደረሱበት ያልታወቀ መሆናቸውን ገልጿል።መለስ ዜናዊ ከቡሽ መስተዳድር ጋር በማበር "የአፍሪካ ጓንታናሞ" በመክፈት ታማኝነቱን ለአሳዳሪዎቹ አሳይቷል።ይህንንም በማድረግ እሱ የሚፈጽመው ወንጀል ሳያንሰው ሌሎች አገሪቷ ውስጥ ወንጀል እንዲፈጽሙ በማድረግ ኢትዩጵያ በጥቁር መዝገብ ላይ ስሟ አወንዲሰፍር አድርጓል። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት "ሲጭኑበት አነሰኝ ጨምሩልኝ" የሚል ታማኝ አጋሰስ እያለላቸው በሌላ በምንም ዓይነት እንዲተካ አያደርጉም። አንደዚህ ዓይነቱን ወንጀልና ኢሰብዓዊ ድርጊትስ መለስ ካልሰራላቸው ማን ሊሰራላቸው ይችላል?

በእርግጥ ሲናተር ኦባማ ለምሳሌ "የቀድሞ የፓኪስታን ፕሬዝዳንት ከነበሩት ከሙሻረፍ መሰሎች ጋር አብሬ አልሰራም ህዝቡን፣ መያዝ አለብን" የመሳሰሉ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል። ነገር ግን ይሄ ለምርጫ ውድድር ከሚነገር ጉንጭ አልፋ የቅስቀሳ ዘዴ ያለፈ ስለማይሆንና በተግባርም ላይ ለማዋል የሚቻል ስላይደለ በዙ ሊባልበት አይገባም። ስለሆነም በሽብር ፈጠራ ላይ የሚካሄደው ጦርነት ላይ "በወዶ ገብነት" (Coalition of the Willing) የተሰለፉት እንደነመለስ ዜናዊ ያሉ ፈላጭ ቆራጮች በሚገዙት አገር ውስጥ ምርጫ ሰርቀውና አጭበርብረው ጉልበትና በማናለብኝነት ንፅሃን ዜጎችን እየፈጁና በረሃብ እየጨረሱ ስልጣን ላይ ቢቆዩ የሴናተር ኦባማ መስተዳድር "እናንተ እጃችሁ በደም የተጨማለቀ አራጆች ጋር አብሬ አልቆምም፣ የናንተንም ትብብር አልፈልግም" የሚል ወኔ ይኖራቸዋል ብሎ መገመት በአገሮች መካካል ያሉ ግንኙነቶችን ካለመረዳት የሚመጣ ነው።

እንደውም ሴናተር ኦባማ በብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች ላይ ለዝብተኛ ናቸው፤ አገራቱንም ከጥቃት ለመከላከል ልምዱና ብቃቱ የላቸውም፤ ተብለው ተብለው በተደጋጋሚ የተተቹበትን ወቀሳ ለማስቀየር እንደሚፈልጉ ስለሚታመንና እንዲሁም ከአራት ዓመታት በኋላም ለድጋሚ ምርጫ መወዳደራቸው ስለማይቀር እራሳቸውን የአሜሪካ ብሔራዊ ድህንነት አስከባሪነታቸው ለማሳየት እነመለስን ተሸክመው ከመሄድ ሌላ አማራጭ የላቸውም።ለዚህም አንዱ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ሲናተር ኦባማ ለኢራቅ ጦርነት መታወጅ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት አንዱ ከነበሩት ሪፐብሊካኑ ጄኔራል ኮሊን ፓወል ጋር የእርሳቸው መስተዳድር አብሮ እንደሚሰራ ማሳወቃቸው ነው።

ምናልባት የኦባማ አስተዳደር አንዳንድ ከዚህ በፊት የነበሩ መስተዳድሮች የተጠቀሙባቸውን የተሰለቹና የተነቃባቸውን ማስመሰያዎች መጠቀም ሊያቆሙ ይችላሉ። ለምሳሌ እ.አ.አ. በ1997 ኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ጊዜ እንደታየው ትጥቅ ያልያዙና በሰላም ህገመንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው "ምርጫ ተጭበረበረ፣ ድምፃችን ተሰረቀ" በማለት ተቃውሚቸውን የግለፁ በርካታ ቁጥር ያላቸው ንፁሃን ላይ የአጋዚ ጦር በአልሞ ተኳሾች እየለቀመ በመፍጀት አገሪቱን የደም አውድማ ሲያደርጋት፤ የፕሬዝዳንት ቡሽ እስቴት ዲፓርትመንት ወያኔን ጭፍጨፋውን እንዲያቆምና የሕዝቡን ውሳኔ እንዲያከብር በማድረግ ፈንታ በመገደልና በመሞት ላያ ያሉት ንፁሃን ላያ በማላገጥ "ሁሉም ወገኖች ማለትም በመገደል ላይ ያለው ህዝብ ጭምርና ወያኔ ሊታቀቡ ይገባል" የሚል እጅግ አሳዛኝ፣ የነሱንም ማንነት ያጋለጠ ለይስሙላ የተነገረ ፍሪቢስ መልእክት ያስተላልፉ እንደነበር እናስታውሳለን። እንደዚህ ዓይነቱ ጭፍንና እርቃኑን የቀረ ማደናገሪያ በግላጭ መስጠት በሴናተር ኦባማ መሥተዳድር ሊቀር ይችል ይሆናል።

3. ሌላው እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት አብይ ጉዳይ ከሴናተር ኦባማ የምርጫ ቡድን ጋር በቅርብ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙትን የዲሞክራቲክ ፓርቲው ከፍተኛ አባላት በተለይም በውጭ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ የተሳተፉትን ሰዎች ብንመለከት ብዙዎቹ ከዚህ በፊት በፕሬዝዳንት ክሊንተን መስተዳድር ጊዜ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩና ኢትዮጵያን በተመለከተ የተዛባና የተወላገደ አመለካከት ያላቸውና ለወያኔም ጭፍን ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩም ይገኙበታል። ሴናተር ኦባማ አዲስ ፖሊሲ ይዣለሁ ቢሉም የፖሊሲው ቀራፆች ያው የበፊቶቹ ሲሆኑ የፖሊሲው አስፈፃሚዎችም እነዚሁ ሰዎች እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ሴናተር ኦባማ ከከበቧቸው አማካሪዎቻቸው መካካል አንድም እንኳ ከሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ወይም መንሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የመጣ ሰው አልተመለከትንም። ከዚህም በተጨማሪ ሴናተር ኦባማ የዲሞክራቲኩን ፓርቲ እጩነታቸውን በተቀበሉብት ጊዜ ባደረጉት ንግግር "አንድን ተግባር ተመሳሳይ ሰዎች በተደጋጋሚ እየሰሩት የተለየ ለውጥ መጠበቅ ዘበት ነው" ብለው ከተናገሩትም ጋር አሁን በማድረግ ላይ ያሉት የሚጣጣም አይደለም።

እ.አ.አ. ኦገስት 28 ቀን 2008 የዲሞክራቲክ ፓርቲው የፕሬዝዳንት እጩውን በሚሰይምበት ጊዜ "የውጭ ፖሊሲ በኦባማ መስተዳድር" (Foreign Policy in an Obama Administration) በሚል ርእስ በዴንቬር፣ኮሎራዶ ውስጥ የተካሄደው ጉባዔ ላይ የነበረውን ሁኔታ ብንመረምር የሴናተር ኦባማን የውጭ ፖሊሲ አፈጻጸም በሚገባ ያመለክታል። በዚህ ጉባዔ ላይ ከተሳተፉት ስድስት ግለሰቦች መካከል ሶስቱ በፕሬዝዳንት ክሊንተን መስተዳድር ጊዜ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ሲሆን እነሱም ሚስተር አንቶኒ ሌክ የብሔራዊ ድህንነት ምክር ቤት ዋና ኃላፊ የነበሩ፣ሚስ ሱዛን ራይስ ረዳት የእስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩ፣እንዲሁም ሚስ ጌል ስሚዝ የብሔራዊ ድህንነት ምክር ቤት ከፍተኛ አማካሪ የነበሩ ናቸው። ፕሬዝዳንት ክሊንተን ለስምንት ዓመታት በሥልጣን ላይ በነበሩበት እ.አ.አ. ከ1993 እስከ 2001 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ይፈጽም የነበረውን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ፣ የዲሞክራሲ መብቶች አፈና

በተለይም የንፁሃን ዜጎች ጭፍጨፋና ሌሎች በርካታ ኢሰብዓዊ ድርጊቶች በመቃወም፤ ለወያኔ ከአሜሪካ የሚሰጠው እርዳታ እንዲቆም በአሜሪካ ውስጥ በተለያየ ከተሞች ውስጥ በርካታ ትእይንተ ሕዝቦች፣ሰላማዊ ሰልፎችና ሌሎችም አግባብነት ያላቸው ወያኔን የማጋለጥ እንቅስቃሴዎች በተደጋጋሚ የተካሄዱ መሆናቸው ይታወሳል።

ሆኖም የስቴት ዲፓርትመንት ኃላፊዎች ይሰጡ የነበረው ምላሽ ሲጠቃለል የኢትዮጵያ መንግሥት የብሔር ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሙከራ በማድረግ ላይ ስለሚገኝ፣ ሙከራው ስለመስራቱና አለመስራቱ ለማወቅ ጊዜሊሰጣቸው ይገባል በማለት በህዝባችን ላይ በወያኔ የደረሰውን ፍጅትና እልቂት እንዲሁም ረሃብ፣እርዛትና ስደት ሳይቆረቁራቸው በላቦራቶሪ ውስጥ እንዳለ አይጥ ሙከራ ሲካሄድብን ሆዳቸው እያወቀ ዝም ብለው ከመመልከት አልፈው ከፍተኛ እርዳታ ለወያኔ ማጉረፋቸውን ቀጠሉበት። በወያኔ "ቤተሙከራ" ንፅሃን ኢትዮጵያውያንን ለእልቂትና ለሰቆቃ መዳረጋቸውና የወያኔ "የክልል አስተዳደር" ብዙዎችን ለከፍተኛ መፈናቀል የኢኮኖም ኪሳራ እንደዳረጋቸው በሚነገራቸው ጊዜ ሁኔታው ከደርግ ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ነው እያሉ ሲያላግጡብን እንደነበር ያታወሳል።ይህም ሁኔታ እ.አ.አ. በ1991 ወያኔ አዲስ አበባን በወረረበት ጊዜ መርቀው ካስገቡት ከሚስተር ኸርማን ኮኸን ፖሊሲ ጋር የሚመሳሰልና "ዲሞክራሲ ከሌለ እርዳታ አይሰጥም" የሚለውን ለኢትዮጵያ ህዝብ የተገባውን ቃል አጥፈው በጭፍንና በማንአለብኝነት ለወያኔ ከአሜሪካን የሚጎርፈው እርዳታ መቀጠሉ ሆን ተብሎ የተደረገ የፖለቲካ ውሳኔ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

በዚሁ በዴንቬር ከተማ በተካሄደው ጉባዔ በቀጥታ ከወያኔ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንደውም የወያኔ ድርጅት አባል ናቸው ተብለው የሚታሙት ሚስ ጌል ስሚዝ፣ ከሴናተር ኦባማ ዋና የውጭ ፖሊሲ አማካሪዎች አንዷ መሆናቸው የአሜሪካ ፖሊሲ ኢትዮጵያን በተመለከተ ፈቀቅ እንደማይል የሚያመላክት ነው። ወያኔ በእነዚህ ግለሰቦች እየተጠቀመና አግባቢዎችና ደላሎች (ሎቢስቶች) ከረሃብተኛ ኢትዮጵያዊያን እየቀማ በከፍተና ዋጋ በመቅጠር በሥልጣን ላይ ተንፈላንሶ ለመቀጠል መንደፋደፉን ይቀጥልበታል። የስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ኃላፊ የነበሩት ሚስ ሱዛን ራይስም ባልሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈንና የሰብዓዊ መብት መከበር ረዥም ጊዜ የሚፈጅ ሂደት ነው በማለት ኢትዮጵያዊያን ለወያኔ ዘመን አሜን ብለውና ተስፋ ቆርጠው እንዲገዙ የተቃዋሚዎችን እጅ ሲጠመዝዙ እንደነበር አይዘነጋም።

ሴናተር ኦባማ እንደነዚህ ዓይነት አፍቃሪ ወያኔና ፀረ ኢትዮጵያ አማካሪዎቻቸውን ይዘው ምን ዓይነት ለውጥ ለኢትዮጵያ ሊያመጡ ይችላሉ? እነዚህ አማካሪዎቻቸው ወያኔ በሥልጣን ላይ እንዲቆይላቸው እንጅ ሌላ ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ፣እንዲሁም ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያዊያን የሆነ መንግሥት እንዲመሠረት ይፈልጋሉ ብሎ መገመት ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት የመጠበቅ ያህል ነው። እነዚህ ባእዳን "ሰዶ ማሳደድ ያማረው ዶሮውን በቆቅ ይለውጣል" የሚለው እንዲደርስባቸው የሚፈልጉ አይደሉም። እንደልባቸው የፈለጉትን ማስደረግና በር ተከፍቶላቸው መፈትፈት ለምደው በሌሎች ለእነሱ ሸከም ትከሻ በሌላቸው እንዲተኩ አያደርጉም። የጥቅም ጉዳይ ነውና።

ኢትዮጵያዊያን የምናካሂደው ትግል፣ የብሔራዊ የአርነት ትግል እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ኢትዮጵያ በታሪካዊ ጠላቶቿ ብዙ እንደተዶለተባትና እንደተሴረባት መገንዘብና እንዲሁም ትግላችን ከባድና ውስብስብ እንደሆነም መረዳት ይኖርብናል።ትግላችን የአገራችን ባለቤት የመሆንና የነፃነት እንጅ የሌላ እንዳልሆነ ብዥታ ሊኖርብን አይገባም። የዲሞክራሲ መስፈን፣የሰብዓዊ መብት መከበርና የፍትህ ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ ነፃነት ባለውና አገርና እራሱን በራሱ በአገሩ ተወላጅ በሚያስተዳድር ሕዝብ ነው። ከፈረሱ ጋሪው መቅደም የለበትም። ወያኔና ሻቢያ ኢትዮጵያን ወረው ከያዙበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያዊያን ተቀበልነውም፣ አልተቀበልነውም መራራው ሃቅ የአገራችንን ባለቤትነት ተነጥቀናል። ወያኔዎች ከዚህ በፊት እንደነበሩት እንደ ንጉሰ ነገስቱና እንደ ደርግ መንግሥታት ተራ አምባገነኖች ብቻ ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የህዝብ አንድነት ላይ ጦርነት ከፍተው በታሪካዊ ጠላቶቻችን በመታገዝ በቅኝ ገዥነት የተንሰራፉብን ጠላቶቻችን በመሆናቸውም ጭምር ነው።

በመጨረሻም ለችግራችን መፍትሄ የሚሆነው በውጭ አገር ሰዎችና በባእዳን ላይ ተስፋ ማድረግ ሳይሆን፣ እራሳችን ኢትዮጵያውያን ተባብረን፣ በራሳችን ተማምነንና እራሳችንን አጠናክረን ያሉንን ጥቃቅን ልዩነቶቻችንን አቻችለን የወያኔን ፋሽስታዊ የቅኝ ገዥ ቡድን ለማስወገድ በትጋት ከመስራት ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። የውጭ አገር ሰዎችና ባእዳን የእኛን ሥራ ሊሰሩልን እይችሉም። ባእድ ሁል ጊዜ ባእድ ነው። ከባእዳን ጋር ለመዛመድ ብዙ ጊዜ በከንቱ አጥፍተናል። ባእዳን ችግራችን ችግራቸው፣ ስቃያችን ስቃያቸው ሊሆን አይችልም። ባእዳን የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ እንጅ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ጥቅም ይቆሙሉናል ብሎ ማመን ከፍተኛ ስህተትመሆኑን ካለፉት አስራ ሰባት ዓመታት መገንዘብ ይቻላል። ዘላቂ ጥቅማችንን አውቀን፣ ካለፈው ስህተታችን ተምረንና በአንድነት ከሰራን ባእዳን ወደ እኛ የሚመጡና የሚያከብሩን እንጅ እኛ እነሱን የምንለማመጥና ደጅ የምንጠና አንሆንም።

ኢትዮጵያ በልጆችዋ ለዘላለም ተከብራ ትኖራለች!
የኢትዮጵያ ነፃነት ቅርብ ነው!

## ሕገ ወጦች ሲጋለጡ

በረኸኛው የወያኔ መንግስት ሕገ እግዚአብሔርን ጥሶ ቀኖና ቤተክርስትያንን አፍርሶ የራሱን ቤተክህነት አቋቁሞ የቤተ ክርስትያን አባል ያልሆነውን ሰው ከውጭ በማስገባት ፓትርያርክ ብሎ በመሾም በህዝብና በአገልጋዮች የተመረጡትን ህጋዊ ቅዱስ አባት ያለ ሕግ ሰብአዊ መብታቸውን ገፎና አስገድዶ ከመንበራቸው በማውረድ ባልታወቀ ቡታ ደብቆ አረመኔያዊ የማስገደል ስልቱን አዘጋጀ።

በ2ኛ ነገ 17፥ 1-7 ንጉሱ አክአብና ሚስቱ ኤልዛቤል የእግዝአብሔርን ሕግና አምልኮ በመደምሰስ ነቢያቱን ለማጥፋት ሲሯሯጡ ታላቁን ነብይ ኤልያስን ተሰደድ ያለው እግዝአብሔር አምላክ ግን ብፁወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስን ከሞት አድኖ እንዲሰደዱ በማድረግ በዓለም የተበተኑ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን ወደ እናት ቤተክርስትያናቸው በመሰብሰብ አገልጋዮች ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናትን በመሾም ሕገወጦች እንዲጋለጡና እውነት ተቀብራ እንዳትቀር ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ።

አባ ጳውሎስ ማን ናቸው?

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ አባል አይደሉም። ዶ/ር ጳውሎስ በአሜሪካ ሀይማኖታቸውን ቀይረው ስማቸውን ለውጠው “ አፖስተሊክ ቸርች„ አዲስ ቤተክርስቲያን አቋቁመው በፈቃዳቸው አባልነታቸውንና አባትነታቸውን የለቀቁ ናቸው።
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ እንዳይጠቀሙ በአሜሪካ የካሊፎርንያ ሕግ ፈርዶባቸዋል።

ለፓትርያርክ ምርጫ የሚቀረበውን ግን የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የሆነ፣ በኃገረ ስብከት ተመድቦ የጵጵስና ስራውን የሚሰራ፣ ተከሶ ፍርድቤት ያልቀረበ፣ ወዘተ እንዲሆን ሕጉ ያዛል።እሳቸው ግን መሪ ቀርቶ አባል ይሁኑ ቢባል እንኳን የንስሀ ግዜ ተሰጥቷቸው ንስሀቸውን መጨረሳቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው።

3. ዓለም አቀፍ የሆነው የክርስትና ሕግ ተጥሷል።

ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ አይተካም እንኳን በመንፈሳዊ በስጋዊም ቢሆን በ አንድ ሀገር ሁለት ፕሬዝዳንት አይሆንም።

4. ጳጳሳትና የቤተክርስቲያን ሠራተኞች (አገልጋዮች) ምዕመናን ተቃውመዋል።

በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ (በተለያዩ ክፍለ ሀገራት) የተሾሙ ጳጳሳት የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ የመምሪያ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት ፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችና ምዕመናን ተሰብስበው ተቃውሞአቸውን ገልፀዋል። አሁንም እየገለጹ ይገኛሉ።

እንግዲህ ይህን የመሳሰለው ሊደብቁት የማይችል ተራራ የሚያክል እውነት ይዘው ነው ብዙ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክርስትያን አባቶችና አገልጋዮች እስካሁን ድረስ እየታሰሩና እየተገደሉ እየተሰደዱ ሳይፈልጉ በግድ ከእናት ሀገራቸው ተለይተው ያሉት።

ሕዝብ የሚአውቀወውን ታለላቀቅ ሕገግ አፍርሶ ሕጋዊውን ፓትርያርክ አውርዶ እኔ ሕጋዊ ነኝ በማለት ማታለል አይቻልም። ሕጉ ራሱ ይከሰዋል ይወቅሰዋል።

አሁንም በተቀደሰው መንበር ላይ የተቀመጡትን ቅዱስ አባት በኃይልና በማን አለብኝነት አውርዶ ቅዱስ ነኝ የሚለው ዶ/ር ጳውሎስና ቅድስና ሰጪው የወያኔ መንግስት ሕግ አፍራሽነታቸውን አምነው እስካልተቀበሉና ሕግን በቦታው መመለስ እስካልቻሉ ድረስ ይህ በዘመናችን ዐቢይ(ትልቅ) የመነጋገሪያ ርዕስ የሆነው የ ኢ.ት.ኦ.ተ. ቤ/ክ ጉዳይ እልባት እስካልተደረገለት ድረስ ችግሩ ገና ወደፊትም ብዙ መዘዝ የሚያስከትል ብዙ የሚያስተች ብዙ የሚያወያይና የሚያፅፍ ሆኖ ይቀጥላል።

የሕግ ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ ሕግን ይመልስልን።
ካሣ ደምሴ ዋኙባቸው(አሻፈንቡርግ)

## የመልካም አስተዳደር ጉዳይ

መለሰ ዜናዊ ብዙ ጊዜ ሲናግር መልካም አስተዳደር የመንግስትም የወያኔ/ኢ.ህአዴግም የቅድሚያ ጉዳይ እንደሆነ ያብራራል። ለዘመናት ህዝቡም ሃገሪቱም የተንገላቱበት የመልካም አስተዳደር እጦት ጉዳይ ስለሆነ እንደመንግስትም መንግስቱን እንደሚመራው ፓርቲም ይህን ችግር ለማቃለል ማሰቡ ጥሩ ነገር ነው። ነገር ግን ችግሩን ከዛሬ አስራ ሰባት አመት ጀምሮ ስናወራው ስለነበርና ዛሬም እንደ አዲስ እያወራነው መሆኑ አሰፍነዋለሁ ወይም በተግባር እተረጉመዋለሁ ከሚል አካል ችግር እንዳለ ጠቋሚ ነው።

እንደ መንግስት መሪ ድርጅት ወያኔ/ኢ.ሕአዴግ ለመልካም አስተዳደር መጥፋት በሁለት መልኩ ተጠያቂ ነው። አንደኛው ስለተጠያቂነት ያለው አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ችግሮቹ ሲነገሩት አልሰማ ማለቱና ከሕዝብ ጋር እልህ መጋባቱ ነው። ወያኔ/ኢ.ሕአዴግ ህግ ሲያወጣ ወይም ደንብ ሲያረቅ በቅድሚያ ታሳቢ የሚያደርገው መቆጣጠር መቻሉና ይህንንም ማረጋገጥ መቻሉ ላይ መሆኑና የረቀቀውን ህግና ደንብ ሲያፀድቅ ተፈፃሚነቱ በራሱም ጭምር ሳይሆን በሌሎቹ ላይ ነው በሚል አመለካከትና እምነት መሆኑ ትልቅ አለመታደል ነው። በተደጋጋሚ እንደታየው በተጠያቂነትና በህግ የበላይነት ዙሪያ ለሚነሱ ችግሮች መልስ ሁለት አይነት ነው።

*መንግስት ሲያጠፋና ከህዝብ ቅሬታ ሲቀርብ የዲሞክራሲ ልምዳችን አናሳ ስለሆነ፣ ስለ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ያለን ተመክሮ ገና በቅጡ ያልዳበር ስለሆነ ነገሩ በሂደት ይስተካከላል ይባላል ሌሎች ሲያጠፉ መልሱ በምንም መልኩ ቢሆን የሕግ የበላይነት መከበር ስላለበት ሁሉም ከህግ ውጭ ስለማይሆን ተገቢውና አፋጣኝ እርምጃ ይወሰዳል የሚል ነው።*

*ለዘመናት ያየነው ግን ዜጎች በህግ ፊት እኩል እንዳይደለ ወያኔ/ኢሕአዴግ የራሴ የሚላቸውየሀገሪቱ የበኩር ልጅ ተብለው ጥፋታቸው በሹመት ሲታደስላቸው ነው። እንዲህ አይነት አሰራር ባይኖርም ዛሬ ድረስ እንደበፊቱ የመልካም አስተዳደር ችግር ችግራችን ሆኖ ባልተነሳም ነበር።*

*ጠቅለል ባለ መልኩ መልካም አስተዳደርን ለመገንባት ዲሞክራሲንና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን አምኖ መቀበልና ተግባራዊ የግድ ይላል። ወያኔ/ኢሕአዴግ በስልጣን ላይ ባሳለፍናቸው17 አመታት ደግሞ ዲሞክራሲን ሰባኪ፣ በተግባር ግን እንግዳ የሆነበት ድርጅት ሆኖ ይታያል። የሰላምና የዲሞክራሲ መንገድ የእኔና የእኔ ብቻ ነው በሚል አግላይ አስተሳሰብና አሰራር ከቶም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ልንገነባ አንችልም። ኢሕአዴግ "እኔ ካልመራኋት ይህች ሃገር አለቀለት" ከሚለው አስተሳሰብ መላቀቅ አለበት።ንጉሱም ደርግም ይህን ይሉት ነበር።የመሪዎች ምርጫ ባለቤቱ ህዝቡ ነውና ለህዝብ ይተውለት።*

*ራሄል መኮንን*

## <u>*ኢሕአዴግ በገበሬው ስም መንገዱን ያቁም!*</u>

*ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያና የአለም ህዝብ የሚያጭበረብርበት የተለያየ መንገድ እንዳለው ለማንም ግልፅ ነው። የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች በአገኙት አጋጣሚ የገበሬውን ስም አንስተው አይጠግቡም ምክንያቱም በስም እየነገዱ ትርፋማ ሆነዋል። ይህንንም ገበሬውና የገበሬው ልጆች እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ እንደሚያውቀው ወያኔን ላስታውሰው እወዳለሁ። ያ ባሕሉን እምነቱን ጠብቆ የአገሪቱን ምሁራንን ያስተማረ፣ በተለያየ አጋጣሚ የሚመጣውን ጠላት ተዋግቶ ዳር ድንበሩን ያስከበረ የሀገር ልጅ የሆነው ገበሬ ወያኔ በስሙ ከቶ ሊነግድበት አይገባም።*

*የገበሬውን ስም አንስተው የማይጠግቡት የበሉበትን ወጭት ሰባሪ ወያኔ ገበሬውን ለተለያዩ ችግሮች ዳርገውታል። እራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም ንብረቱ ከዱር አራዊትና ከጠላቱ የሚጠበቅበትን መሣሪያ ለወያኔ ጭፍሮች እንዲያስረክብ በማድረግ ባዶ እጁን አስቀርተውታል። ይህም ገበሬው የወያኔን ግፍ የተሞላበት አስተዳደር ተቃውሞ ብረት እንዳያነሳ የተደረገ ሴራ ነው። ዛሬ ገበሬው አርሶ ሃገሩን እራሱን እንዳይጠቅም በወያኔ አባላት እየተንገላታ ይገኛል። ነገር ግን የወያኔ መሪዎች ገበሬው ከጎናቸው እንደሆነና ለገበሬውም የሚያስፈልገውን ሁሉ እያደረጉ እንደሆነ የሀሰት ጥሩንባቸውን እየነፉ ይገኛሉ።*

*ወያኔዎች ለእያንዳንዳቸው የግል የጤና ዶክተር ሲኖራቸው ገበሬው ግን በአካባቢው አንድም የጤና ረዳት ለማግኘት የህልም እንጀራ ሆኖበት በወባና የተለያዩ ወረርሽኝ በሽታዎች ከወያኔ ግፍ አስተዳደር ጎን ተሰልፈው እየተጫወቱበት ነው። የገጠሪቷ ሴት የመጠጥ ውሃ ፍለጋ በቀን ብዙ ኪሎሜትር ስትጓዝ ለገበሬው ቆመናል ባዮቹ ግን በተንጣለለው ቤታቸው ቅጥር ግቢ የመዋኛ ገንዳ አላቸው።የገበሬው ልጆች ትምህርት ለማግኘት ብዙ ኪሎሜትር በባዶ እግራቸው ሲጓዙ ገበሬው ወክሎናል ባዮቹ ግን ልጆቻቸውን አሜሪካ አውሮፓ ልከው ያስተምራሉ።ገበሬው የሚያበራው ለምባ አጥቶ በጨለማ ሲኖር ዘመነኞቹ ግን በየቤታቸው ዘመናዊ ጄነሬተር አስገብተው ጨለማ ለምኔ ብለዋል።*

*በአሁኑ ወቅት ገበሬው የሚያርሰውን መሬት ወያኔ በተለያዩ ኩባንያዎች ስም በመውሰድ ላይ ይገኛል።ገበሬው የሚያመርተውን ምርት በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛት ወደ ውጭ በመላክ የወያኔ ኩባንያዎች ትርፋማ እንዲሆን አድርገውታል።ገበሬው ግን በተለያዩ እዳዎች ወጥረው ይዘውት የእርሻ በሬዎቹን እስከማጣት ደርሷል።*

*"ሞጣ ቀራኒዮ ምነው አይታረስ፣*
*በሬ ሳላይ መጣሁ ከዚህ እስከዚያ ድረስ፡" ተብሎ የተነገረው ቅኔያዊ አነጋገር ጥንት በነበረው የርሀብና ችግር ጊዜ ነበር። አሁን ግን ወያኔ ባመጣው ጣጣ መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል።*

*ሁላችንም እንደምናውቀው አብዛሀኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው በገጠራማው የሀገሪቱ ክልል ነው። ስለ ሆነም ወያኔ ያለየሌለውን ሀይል በመጠቀም(በጉልበትና በሃሰት ፕሮፓጋንዳ) ገበሬውን እየተጫወተበት ይገኛል። ነገር ግን ገበሬውን የሚያደራጀውና አይዞህ ከጎንህ ነኝ የሚለውን የሀገሩን ልጅ ካገኘ ወያኔን ለመደምስ ከማንም በላይ እንደሚያውቅበት ሁላችንም ልንገነዘበው ይገባል። ይህንንም እራሱ ወያኔ ጠንቅቆ ያውቀዋል። በመጨረሻም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የማስተላልፈው ሁላችንም ወያኔን ለመጣል ለምናደርገው ትግል ዋናው የትግላችን ሀይል ገበሬው እንደሆነ አውቀን ትግላችንንወደፊት ከገበሬው ጋር መቀጠል ይገባናል።*

*ገበሬው የለውጥ ሀይል ነው።*
*ዮናስ አምሳሉ(ሁለሆረስት)*

# ደርሶባችሁ ይሆን እናንተም እንደኔ!!!
# እውን ኢሕአፓ መሆን ያኮራል?

ከቤልጅግ አሊ

ካለፈው የቀጠለ (አደራ ቅጽ2 ቁ.3)

# የመጨረሻው ሰይጣን

## ክፍል አምስት

- እንግዲህ እማማ እዚህ ነው የምንኖረው ። አካባቢው ጥሩ ነው። ወደዚህ ታች ጫካ አለ ውስጥ ውስጡን መንገድ ስላለ ትንሽ መዞር ይቻላል። እዚህ አካባቢ አንድ ዶክተር ስላለ እንዲመረምሮት እጠይቀዋለሁ ። በተረፈ የሚስማማዎት ይመስለኛል። ልጅትዋ ክፍልዋን ለእርሶ ለቃ አዘጋጅታለች። ግን ከእሳቸው ጋር ነው የማድር ብላ መሬት አንጥፋለች ። የእርሶን ጨዋታ የናፈቀች ትመስላለች::
- ጥሩ ማለፊያ አዳራሽ አይደለም እንዴ የያዛችሁት እባካችሁ። ከዚያ ጥቅጥቅ ካለ ከተማ እንኳን አወጣሽኝ። እኔ እኮ ከተማም እምብዛም ነኝ።በጣም ነው ደስ የሚለኝ ከኔ ጋር ታድራለች ። አልጋው ለሁለት ይበቃን ነበርኮ።
- አይ ተዝናንተው ይደሩ።ለሷ መሬቱም ይመቻታል።እዚህ ቤት ክራዮም ይረክሳል ። ልጅ ለማሳደግም ደግሞ ጥሩ ነው። ልጆቹ በቶሎ አይበላሹም ።
- ከተማው ብለህ ልጅ የሚያበላሽ? እንደው የቤተሰብ አስተዳደግ ወይም የወላጆች ሁኔታ ነው እንጂ። በአለፈው ሳምንት እዛ ከተማ ይዛኝ ሄዳ አንዳንድ ልጆች አይቼ ነበር ። አማርኛም አይችሉ አለችኝ። ለምን? ብዬ ስጠይቅ ማንም የአስተማራቸው የለም አሉኝ ። እንደው በጣም አዘንኩ። እባካችሁ ምን አይነት ዘመን ደረስን።

– እናትና አባት ከልጆቻቸው ጋር የማይግባቡበት ዘመን ።
– አንድ አይነት ቋንቋ እንኩዋ የማይነጋገሩበት ዘመን ።
– ችግሩዋን ሴት ልጅ ለእናትዋ የማትነግርበት ፤ ብትነግርም እናትዋ የማትረዳበት ዘመን።
– ወንድ ልጅ ለአባቱ ሚስጥሩን የማይነግርበት ቢነግርም አባቱ የማይረዳበት ዘመን።
– ምን አይነት ግዜ ነው እባካችሁ!!! አስጠሊታ ዘመን የዘመን ድሪቶ ።
–እባካችሁ ተውኝ። የልጆቹ ችግር አይመስለኝም የወላጆቹ ነው ። የተበላሹት ልጆቹ አደሉም።ቀድመው የተበላሹት ወላጆቹ ናቸው።
– ማንነታቸውን የሳቱ። ጉራማይሌዎች፣ ባህላቸው የጠፋቸው። ልጁን ቋንቋ ሳያስተምር የቀረው እሄኔ ኢንቬስተር ሆንኩ ብሎ ሲያዘጠዝዋ ነው ።የገዛ ልጁህን እንደጉዲፈቻ ልጅ ማሳደግ? ታሪካቸውን ባያውቁ ቋንቋቸውን እንኩዋን ሊያውቁ ይገባ ነበር"። ተወኝ ባክህ ተወኝ ።

- እሱስ ልክ ነው እማማ።መቼስ እማማ ከእርስዎ ጋር ስቀመጥ በጣም ደስታ ይሰማኛል።በነገራችን ላይ በጣም ነው የማመሰግንዎት ጓደኛዬ እንደገና አስታረቁኝ ።
- አይ ልጄ መች ተጣላችሁና። ይህንንማ በደንብ አውቀዋለሁ።አለመግባባት የሚፈጠረውኮ አንደኛው በሌላው ላይ የተሳሳተ አመለካከት ሲኖረው ነው።እኔ ምንም የጨመርኩት ነገር የለም። የተናገርኩት አንተ እንዳልተለወጥክ ብቻ ነው።እውነቱን ልንገርህ እኔም እስከማገኝህ ቸኩዬ ነበር። ተለውጦ ይሆን? ብዬ አሳብ ገብቶኝ ነበር።እስከማይህ፣ እስከማወራህ ፣ ማን እንደሆንክ እስከማውቅህ ፣ ጨንቆኝ ነበር። አትፍረድብኝ እዛ እኛ ጋ የሚመላለሱትን እያየን ሁሉም እነርሱን እየመሰለን ተቸግረናል።

„የአገራችን ሰው ከውጭ የሚመጡትን እያየን ተስፋ ቆረጠ። ብዙ የሚያውቁ ናቸው ብለን ያልጠበቅናቸውን ያህል ከእኛ የባሰ መሀይም ሆነው አገኘናቸው። ብዙዎቹ ከኛ ነጥቀው ለመብላት ነው

የሚፈልጉት።በየሰፈሩ ትንንሽ የጉራጌ ሱቆችን ከዚህ መንግስት ጋረ ተመሳጥረው ከአዘጉ በኋላ መልሰው በኢንቨስተር ስም ሊገዙ ሲራወጡ ስንመለከት ምን አይነት ስዕብና ነው ያላቸው? ብለን ከልባችን አዘንባቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በተከታታይ በየቡናው ቤቱ አስረሽ ምችው ሲሉ ከርመው አገሪቱ በጣም ተሻሽላለች ብለው እኛን ሊያስምኑን ይጥራሉ። ስለዴሞክራሲ ሲያወሩ ስለኛ አገር የሚያወሩ አይመስለንም።ለእነርሱ ሌላ ኢትዮጵያ የተሰራች እንጂ ይህቺኑ የኛኑ አገር አይመስለንም።

አንድ እዛ እኛ ሰፈር የነበረ አንተ የምታውቀው አይመስለኝም ። ያኔም ከናንተ ጋር ብዙ አይገጥምም ነበር። ታዲያ እሱ ይመጣል ተብሎ አባትና እናቱ ያለ የሌላቸውን አውጥተው ቤቱን አድሰው ደግሰው ሲጠብቁት እሱ ታዲያ ሆቴል ይዞ አባቱንና እናቱን መጥታችሁ ጠይቁኝ ቢላቸው አባትየው እሬሳዬ እዚህ ይወድቃል እንጂ እሱም አይመጣም እኛም አንሄድም ብለው ወሰኑ።እረገሙትም፣ልጅነቱንም ካዱት።በኋላም ከማንም ሳይማከር የመኪና ማጠቢያ አሰገብቶ ተከለና ማንም የሚያሳጥብ አጥቶ አሁን ታዲያ እንደእብድ ብቻውን እየተናገረ ሲዞር ነው የሚውለው።ወደ ውጭ አይመለስ ነገር የተበደረው ገንዘብ ብዙ ነው። እዚህ አይቀመጥ ምን በልቶ የት ተቀምጦ። እናት አባቱ ቤት አይመለስ ያኔ የሰራውን ያውቀዋል።እንደሱ አሳብማ አንድ መኪና በስላሳ ብር አጥቦ ሀብታም ሊሆን ነበር። የኛ አገር ሰው በሰላሳ ብር ዘበኛ ቀጥሮ ከፈለገ በየቀኑ መኪናውን ያሳጥባል። በዛውም አንድ ሰው በመርዳቱ ይደሰታል።እንግዲህ እሱ የሚጋፈው ከዘበኞቹ ነው። ከፈለገ ወደ ገጠር ሄዶ መሬት አያለማም ነበር?እንደው በቀላል ሀብታም ለመሆን መጣደፍ ነው እንጂ። ግን ብዙዎቹ እዛው አዲስ አባባ ከደሃው አፍ ለመቀማት ሲሮጡ ነው የሚውሉት።የረባ ነገር የሰሩትም የለም።በፈረንጅ አገር ከመንግስት እርዳታቸውን እየለቀሙ እዚህ ደግሞ ከደሃው ስራውንም መኖሪያውን ለመቀማት ሲታገሉ ይታያሉ።ትልቅ ሱፐር ማርኬት ለመክፈት ጉልት ሻጭዋን ማስነሳት ምን አይነት ተፈጥሮ ነው?የደሃዋን ጉሮሮ ዘግተው የነእሱን ከርስ መሙላት።መቼስ ምን እናደርጋለን ይስፋቸው አገሩ።መንግስት እንደሁ ለነእነርሱ ነው የቆመው። ልጆቻችን የተወለዱበትን ቦታ እኛም እድሜ ልካችንን የኖርንበትን ሰፈር በሰተርጅና አንዱ ሆዳም ቦታውን እፈልገዋለሁ ስላለ በአስቸኳይ እንድንነሳ ይደረጋል ። እኛም አልቅሰን ተላቅሰን በሃገራችን ባይተዋር ሆነን ለባለግዜ ሁሉንም ትተን እርቀን ወደ ደሃዎች መሰብሰቢያ ጣቢያ ሄደን አዲስ ኑሮ እንጀምራልን። የሚገርመው እኛ እንኖርበት የነበርው ቦታ ፎቅ ካልሆነ አይሆን ብለው እኛ ከልክለው ከለቀቅነው በኋላ እነርሱ በኮንቴነር ከፋፍለው ቤት ሰርተው እያከራዩ ይኖራሉ።ትልቁ ፎቅ እስከሚሰራ ተብሎ በጊዜያዊነት የተሰራው የኮንቴነር ቤት ይኸው አረጀ። አየህ ልጄ ያኔ መሬት ላራሹ ስትሉ ገበሬዎቹ በተወለዱበት ቦታ ጭሰኛ መሆናቸው ነበር ጥያቄውን ያስነሳው። ባላባቱ መሬቱ ሰው የለበትም በማለት ከመንግስት ከአስፈቀደና የመሬቱን ባለንብረትነት ወረቀት ከያዘ በኋላ፣ ገበሬውን ወይ ለኔ ጭሰኛ ሁን ወይም መሬቱን ልቀቅ ብሎ ያስገድደው ነበር።ፖሊስም መንግስትም ከባላባቱ ጋር ነው የቆመው።የአሁኑ ደግሞ ከውጭ የሚመጡት ወያኔን በውጭ ሲያገለግሉ ቆይተው ጉርሻ የኛ መሬት እየተሰጥጣቸው እኛ ደግሞ እየተባረርን ነው።ይህ ግፍ ምን ያህል እንደሚቀጥል አናውቅም ግን በቶሎም ይጠፋል የሚል አሳብ የለኝም ።

ይህንን የሆዳሞች መንጋ እያየን ጓደኛህም ሆነ እኔ አንተን ተለውጠ ይሆን ብለን ብንጠረጥር አይፈረድብንም። ይህ የኔ አሳብ ነው ጓደኛህ ደግሞ ሌላም ይኖረዋል። እሱን መጠየቅ ነው ።

ባለፈው ስለዚያች ልጅ ጠየቅከኝ ይህቺ መውጫው ላይ በቀይ ሽብር የጣሉዋት።መቼም ከጓደኛህ የደበቅሁት አንድ ነገር አለ ላንተ ላጫውትህ አንድ ቀን ግዜው ሲደርስ ትነግረዋለህ ።የእሱን መሞት የተረዳን ለት ማታ ላይ አንዲት ልጅ ተሸፋፍና መጥታ እድንኳን ወስጥ በጣም ማልቀስ ጀመረች ። አልጮኸችም ግን ስቅስቅ ብላ እየተንዘፈዘፈች ስታለቅስ ሆዴ አልችል ቢል ጮክ ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ።እሱዋም ተከተለችኝ። ግን ሰው እንዲያያት አልፈለገችም ።
ማን ነች ብለን ግራ ተጋባን ።ለቅሶውን ስትጨርስ ቀስ ብላ ወደ እኔ መጣች እግሬ ስር ተንበርክካ

እግሬን እየሳመች ማልቀስ ጀመረች።እግሬንም በእንባዋ አራሰችው።ተይ በቃ ብላት የመጨረሻ ቀኔ ስለሆነ ላልቅስ ይፍቀዱልኝ ለማለት ቀና ስትል እሷ መሆኑዋን አወቅሁ። እኔም ማልቀስ ጀመርኩ ሁሉም በድንኳኑ ውስጥ ያሉት ማለቀስ ጀመሩ።ልክ አስከሬኑ ከቤት የሚወጣ መሰለ። ነፍስ አባታችን በምሽት በማልቀሳችን በቁጣ ተነስተው ገዘቱ ።

„ ዘመኑ የከፋ ነው ። የሁላችንም ሕይወት ዛሬ ትጥፋ ነገ ትጥፋ የሚያውቅ የለም። ከአፈር ተፈጥረሃልና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚለውን ቃሉን ሁላችንም ለመፈፀም ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ ነው። በአሰብነውም ሆነ በአላሰብነው ሁኔታ ቃሉን ልንፈጽም እንችላለን ። ነገር ግን ሀዘንን ማጥበቅ አያስፈልግም። ገና በአደጋ ላይ ያሉ ብዙ ልጆቻችን ስላሉ ሃዘኑን ትተን ፀሎቱን መጀመር ይኖርብናል ። ፈጣሪ አምላካቸችን ይህን የመጣብንን የመከራ ዘመን ያሳጥርልን ዘንድ ለልጆችም ጥንካሬን ይሰጣቸው ዘንድ ልመናችንን መቀጠል አለብን“ ብለው ተቀመጡ።

አኔም እስዋን አባብዬ ካስቆም በኋላ ውሃ እንድትጠጣና አጠገቤ እንድትቀመጥ አደረግሁ ። አሁንም ሰው እንዲያያት ስላልፈለገችና ስትሳቀቅ ስላየሁ ሂጂ ጓዳ ገብተሽ ጠብቂኝ መጣሁ አልኳት ።ትንሽ ቆይቼ ብሄድ ጓዳ ሳይሆን እሱ ክፍል ውስጥ መሬት ላይ እየተንከባለለች ፎቶውን ታቅፋ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ደረስኩ። ተይ እንዲህ መሆን አያስፈልግም መበርታት ነው አልኳት ። ለአንድ አፍታ ቀና ብላ ስታየኝ ልጄ ያ ሁሉ ቁንጅና እግዜር እስዋን ብቻ ሲሰራ ያመሸ ነው የሚመስለው። የቅንድቡዋ፣ የአይንዋ፣ የፀጉሩዋን ሁኔታ ልነግርህ አልችልም መቼም አንተም ታውቃታለህ ። አንድ ግዜ በሰፊው ተንፍሳ እማማ ፦

„ አንድ ቀን ድል መጥቶ ለኔ ቤተስቦችና ለእናንተም ጭምር መተጫጨታችንን ለመግለፅ የነበረን ፍለጎት ከሁሉ የላቀ ነበር።ያ ተስፋችን ዛሬ ጠዋት የሱን መሞት ስሰማ፣ ያ ሁል ጊዜ የምንመኘው እውን እንደማይሆን ሳውቀው ምርር ብዬ አለቀስኩ ። እሱ ጓደኛዬ፣ እጮኛዬ፣ ጓዴ፣ ነበር። ሁሉንም በአንድ ቀን አጣሁ ። አሁን እዚህ ተቀምጫ ባዶነት ይሰማኛል ።የወደፊት አላማዬ ከሽፈ ፣ ጓዶቼ በብዛት ሞቱ ፣ እኔም ቀኔ የተቆጠረ ነው። ዛሬ እዚህ የመጣሁት አብረን እነግራችኋለን ያልነውን የኔንና የሱን አላማ ብቻዬን ለመናገር ነው። እግዜር ፈቃዱ ከሆነ እከተለዋለሁ። ከተረፍኩም የሱን አስከሬን የወደቀበት ቦታ ፈልጌ በክብር እቀብረዋለሁ ። እርሶን የምጠይቆት አንድ ነገር ነው፣ እኔ አሁን ለቀበሌ እጄን እሰጣለሁ የፈለጉትን ሊያደርጉኝ ይችላሉ።ለእናቴ ቃል የገቡላት ግን እጅዋን ከሰጠች አንገላትም እስር ብቻ ነው ብለዋል። ግን ምናቸው ይታመናል።አሁን ምንም የቀረኝ የለም። እሱን ገለውታል።እነርሱ የቀመሱትን ችግር እኔም ልቀምሰው እፈልጋለሁ ። ስለዚህ ስሞኑን የተገደሉት የተጣሉበትን ቦታ በሞላ ፈልገው ፅፈው ያስቀምጡልኝ ከተረፍኩ እድሜ ልኬን እፈልገዋለሁ አይፍሩ የሱ አፅም አይጠፋኝም ስትለኝ እሷን መስማት ትቼ እየተንዘፈዘፍኩ አለቅስ ነበር ። ወለድን እንጂ የልብ ጓደኛም እናት ነችኮ ልጄ።

ከዛም እጅሽን ከምትሰጪ እባክሽ እኛጋ ተደብቀሽ ተቀመጭ አልኳት ። እሷም ደግነት እሱ ከርሶ እንደወረሰ ያስታውቃል።እናቴን በደንብ ስታውቂያት ትወጂያታለሽ ይለኝ ነበር።ግን እኔን ካላገኙ እናቴን ይቦጫጭቋታል። በዚህ እድሜዋ ምኑን ትችለዋለች ብለው። እኔው እንደጀመርኩት እኔው እጨርሰዋለሁ። በሉ አሁን ልሂድ የሚወስዱኝ አብዮት ጥበቃዎች የሚመጡበት ሰአት ነው ብላኝ በቆራጥነት ተነስታ ሞቱዋን ልትቀበል ሰማዕታት ልትሆን ዞርም ብላ ሳታይ ሄደች። ያንን ቆራጥነት ምን ግዜም አልረሳውም።

ይህንን ጉድ አልነገርኩትም ። አንድ ቀን ስለ ቀይ ሽብር ተነስቶ ሲወራ ስለሷ ሲነገር እንባው ከመቅስፈት ዱብ ዱብ ሲል አየሁትና መንገሬን ተውኩት ። አሁን አንተ ኑዛዜ እየሰበሰብክ ስለሆነ ይህንን ኑዛዜዬን ቀኑ ሲያመች ንገረው። መቼም ይህም አንዱ ድላችሁ ነው ፍቅራችሁ እስከ መቃብር ድረስ ነው። እናንተ ብትሆኑ ኑሮ በሽታው አያጠቃችሁም ያልኩት በዚሁ ምክንያት ነው። አንድ ለአንድ ስለምትሆኑ የሚያስፈራም አይሆንም ነበር።

- እኔም እማማ ባለፈው ዳር ዳር ያለኩት ይህንን የሚያውቁ ስላልመሰለኝ ነው መቼም እሱ ያነሳው እንደሆን እንጂ የቆየ ፍቅር አንስቼ አልበጠብጠውም። ለማንኛውም የሚፀፈውን እናያለን ።
- ልክ ነህ ልጄ ። እሷን እላይ ከሰፈር መውጫው ጋ ገለው የጣልዋት ለት እኔ እንደገደልኩዋት ነው የቆጠርኩት። ምነው እግሯ ላይ ወድቄ ብለምናት ኖሮ ብዬ አሰብኩ ወይም አባቱን ብጠራቸው ኑሮ ብዬ አሰብኩ። ግን ከአይንዋ የሚነበበው

ከሱ ጋር ለመገናኘት እንደቸኮለች
ለሞሞት እንደተጣደፈች
ሰማዕታት ለመሆን እንዳሰበች
በደሟ ታሪክ ፅፋ ለመለፍ እንደፈለገች።
ይነብብ ነበር ከአይኑዋ ላይ
የቆራጦች የኢሕአፓ ራእይ ።
በትግል መሞት ሕይወት
ዳግም ትንሳኤ ልደት ።

- እኔ በደንብ ነው የማውቃት እማማ ድል ቢሆን ኖሮ የመጀመርያው ሚዜ እኔ ነበርኩ ። የተቀየመኝም በዛ ይመስለኛል ። አፅሟን አብሬው ስላለቀምኩ ።
- ከስደት እንደተመለሰ ቀበሌውን ሁሉ አመሰው። ሁሉንም መጠየቅ ጀመረ። የት እንደጣሉዋት ማንም የሚያውቅ ጠፋ ። የዛን ግዜ እንዴት አሳዘነኝ መሰለህ ።ሌት ተቀን በየጫካው ሲቆፍር ይውል ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ተስፋ ቆርጦ በተቀመጠበት አንድ ልጅ አንድ ወረቀት ይዞ መጣና እሱን ጠርቶ ሰጠው። ማን ሰጠህ ቢለው አንድ መነፅር ያደረገ ሰው ይህንን ለሱ ስጠው ብሎ ገንዘብ ሰጥቶኝ ሂደ አለን ። ወደላይ ሂዶ ቢፈልገው አጣው።ግን ወረቀቱ ጥሩ ምልክት ነበረው።የምትፈልገው እዚህ ጋ አለልህ ብሎ አንድ ካርታ አደርጎ ነው የላከው። ጊዜ ሳያጠፋ ሰዎች ይዞ ሲበር ሂደ እዛም ትንሽ እንደቆፈሩ የብዙ ሰዎች አፅም አገኙ ። የእርሷ ግን በአደረገችው ቀለበት አገኘው ። ተለቀሰ እንደገና አገር ተሰብሰቦ ተቀበረች። ያኔ አንተን ሚዜውን ያጣህ ይመስለኛል ።
- እኔም አውቄዋለሁ በእዚህ ምክንያት እንደተቀየመኝ ። ሁኔታውን እንደሰማሁ ብደውል የለም አሰኝ እኔም ይሁን ብዬ ተውኩት። በኋላ ግን በእሷ ዘመድ ኣስመስዬ ሃውልቱን አሰራሁ ።ግን ምን ያደርጋል እሷም አለፈች።
- አየህ ልጄ ጥሩ ነው ያረግኸው ። እሱም ይህን የሚያውቅ አይመስለኝም። አወቀም አላወቀ ሰለአንተ አለመለወጥ ስነግረው ደስታ ከድምፁ እሰማ ነበር ። ስልክ አንስቶም አያውቅም ነበር። ምክንያቱ የሚመስለኝ ድንገት አንተ ከሆንክ የሚያነጋግርህ ስሌለለው እንደነበር ይመስለኛል ። እኔ እዚህ ከመጣሁ ጀምሬ ተንደርድሮ ነው የሚያነሳው ይላሉ።እውነቱን ለማወቅ እንደቸኮለ እውነት ነው።እንዳሉትም አልቀረም እሱን ነው ያገኘሁት ።የሆነ ሆኖ ምን አለህ ።
- ታሪኩን ጀመረልኝ እማማ ያንን ደብዳቤ „እሳት ድምፅሽ ድምፄን“ የፃፈው ለእርሷ ነው ለኔ አደለም። ግን አሁን ለኔ ሊልከው አስቧል። እንደደረሰኝ አነብሎታለሁ።
- ማለፊያ ልጄ። ዛሬ የዛን ጨካኝ ታሪክ ትቀጥልልን ።
- ምን ላይ ነው ያቆምው ?
- ኑዛዜውን ነው ። እናቱን እንደማያውቃትና በህፃንነቱ ተንኮለኛ እንደነበር ነው የነገረን።ከዛም አስተዳደጉ በጣም መጥፎ እንደነበረና አባቱ በጣም ይገርፈው እንደነበር ነው ። አባቱም የሰው ህይወት አጥፍቶ ሸፍቶ እንደነበር ነው ባጠቃልይ ። አንተው እራስህ እስት አንብብልኝ ።

ወደ ገፅ 30 ....ይዞራል

## ሲሉ ሰምታ….

እንደ ድሮ ድሮ የአሜሪካ የፌደራሊስት ስርዓት በ1781 እ.ኤ.አ ሲመሰረት መስራቾቹ አፍቃሬ ጠንካራ ብሔራዊ መንግስት የነበሩት (እንደወያኔ ጎጠኛ ራዕይ ሳይሆን) በነበሩት አሌክሳንደር ሀሚልተን፣ ጆን ጆይ ብሎም ጆርጅ ዋሽንግተን እንደሆኑ ታሪክ ይነግረናል:: እነዛም ሰዎች ሚዛናዊና ቋሚ ሆኖ እንዲደነገግ የተቻላቸውን ያህል አድርጓል:: በመሆኑም ቁጥር ስፍር የሌለው የህዝብ ድጋፍ ከዋናው የከተማው ባለሀብት እስከ መናጢው ድሀ ገበሬ ድረስ ድጋፍ ሊቸረው በቅተዋል:: ታድያ የወያኔው ዘረኛና ከፋፋይ የሆነው በስመ ፌደራሊዝም ክርስትና የተነሳው አጥፊ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ከገጠሩም ከከተማ፣ ከሀብታሙ ከድሀ፣ ከተማረው ካልተማረው እየደረሰበት ያለው ውግዘትና ተቃውሞ የበረታው ለምንድን ነው?

ይህ የወያኔ ፌደራሊዝም (ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ) ከላይ የተገለፁት ፈጣሪዎቹ እንደተነሱለት የጠንካራ ብሔራዊ መንግስት ለመመስረት ያለመ የሁሉም ህዝቦች ይሁንታ ያገኘ ሳይሆን ዘርን ማዕከል ያደረገ ጎጠኛና ክልላዊ ባህሪ ያለው የአገሪትዋን ህዝቦች የአንድነት ስሜት የሚያጠፋ፣ወያኔ የኢትዮጲያን ህዝብ ለመበዝበዝ፣ ረግጦ ለመግዛትና ለማሰቃየት እንዲያመቸው የተፈበረከ ሴራ ነው::

ይህ መሰሪ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ህዝብ እየደረሰበት ያለውን ስቃይና መከራ በመቃወም ወያኔ/ኢህአዴግን ከስር መሰረቱ ለመጣል የሚያደርገውን ትግል ለማጨናገፍ በዘረኝነትና ክልላዊነት ቁርሾ ተዘናግቶ የፀረ ጭቆናና አፈና አንድነቱ እንዲፈረካከስና ወያኔ ሀይ ባይ ጠንካራ ተቃውሞ ሳይገጥመው እድሜ ይፍታህ እንዲገዛ የታሰበ ነው:: ከአባት አያቶቻችን ያልተላለፈልንን ጎጠኝነትና ዘረኝነት ነግሶ ኢትዮጵያዊነት የሚባል አኩሪ ቅርሳችን ጠፍቶ የአገራችንን አንድነትና ክብር ተዋርዶ ህዝቡ በዘርና በጎጠኝነት ድር ተጠላልፎ እንደ ወትሮ ከፊት ለፊት የተደቀነበትን ፈርጀ ብዙ መከራና ስቃይ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድነትና በኢትዮጵዊነት መንፈስ ሆ ብሎ እንዳይዘምት አድርጎታል::

ይህ ሆኔታ ደግሞ ወያኔና አጫፋሪዎቹ አገሪትዋን እያወደሙ ባሉበት ሁናቴ ህዝቡ መሰረታዊ በሆኑ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገራዊ አጀንዳዎች ላይ እናዳያተኩር ይልቁንም አጥፊ በሆነው የወያኔ የዘረኝነትና ጎጠኝነት ፕሮፖጋንዳ ታውሮ ፀረ ወያኔ ትግሉ ለማዳከም የታለመ ነው:: ይሄኛው ዘር ያኛውኝ ዘር ሊያጠፋ ነው ሊወጋህ ነው ወያኔ ከሌለ አገሪትዋ ትከፋፈላለች ህዝቡ እርስ በራሱ ይተላለቃል እያለ የዕድሜ ማራዘሚያ መርዝ በህዝቡ ላይ በመርጨት ይገኛል::

ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግልፅ እንደሆነውና ታሪካችንም እንደሚያስተምረን የአገራችን አንድነትና ክብር የተዋረደውበታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በወያኔ መንግስት ነው:: ዘረኝነትና ጎጠኝነት ነግሶ የአብሮነት መንፈስ፣ ተከባብሮና ተሳስቦ የመኖር አኩሪ ባህላችን የቆሸሸው በወያኔ ነው:: ገበሬው፣ነጋዴውና ምሁሩ ተባብሮና ተደጋግፎ ከቦታ ቦታ በነፃነት ተንቀሳቅሶ ገንዘብ ያለው ገንዘቡን ንብረት ያለው ንብረቱን እውቀት ያለው እውቀቱን አስተባብሮ እንዳይሰራ ይህ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የፈጠረው መፈራራትና አለመተማምን በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነዋል::

ሲሉ ሰምታ እንዲሉ ይህ በስመ ፌደራሊዝም የተሰየመው የወያኔ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ አገራችንን ጭራሱን ከማጥፋቱ በፊት እዚህ ይብቃ በማለት አገራዊ ራዕይ ይዞ የቀድሞ የሀገራችን የአንድነት፣ የመተሳሰብና የመከባበር ታሪክ ዳግም ለማስፈን ከሚታገለው ኢህአፓ ጋር መሰለፍ ከማንኛውም ሰዓት በበለጠ አሁን በጣም አስፈላጊ ነው:: ለደቂቃም ሳንዘናጋ እጅ ለእጅ ተያይዘን አገራችንን እየበታተነና ህዝባችንን እያማቀቀ ያለውን ዘረኛ መንግስት አስወግደን ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች በእኩልነትና በመከባበርና በአንድነት የሚኖርባትን ኢትዮጵያ ለማየት የምንታገልበት ወቅት ላይ እንገኛለን::

አለም ገ/ፃድቃን(ሙል ሀይም)

---

## መለሰና አገዛዙ

በቀደምት አባቶቻችን እንደሚታወቀው ሁሉ ኢትዮጵያ ሀገራችን በህዝቦቿ አንድነት እና ሃገር ወዳድነት ለዘመናት ድንበሯን ሳታስነካ አስከብራ የኖረች ሀገር መሆኗ በአፍሪካ ብሎም በመላው አለም የሚታወቅ ነው።

ይህንን የረጅም ጊዜ ታሪክ ለማጥፋት የመጣው የመለስ አገዛዝ ግን ታሪክን በማበላሸት መሬትን ቆርሶ ለጎረቤት ሀገር በመስጠት ለወያኔ ባልገበሩ የተለያዩ ማህበረሰባዊ ተቋማትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚፈፅሙት አይን ያወጣና አንዱን ብሄረሰብ ከሌላው ብሄረሰብ በማጋጨት ሆን ተብሎ በተነደፈ የወያኔ ፖለቲካ ሸፉን ነው።

በመሆኑም ይህንን ጠበብተኝነት የሚያጠቃው ፍትሀዊ ያልሆነ የመለስ አገዛዝ ስርአትን ከስሩ ማድረቅና ማጥፋት ለሀገራችን ሰላምና አንድነት መስፈን እድገትና ብልፅግና መምጣት ዋነኛው መፍትሄ ስለሆነ ማንኛውም የአውሮፓ ሆነ በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገራት ለወያኔ የሚያደርጉትን እርዳታ በማቆም የህዝብን ጩኸትና ብሶት ይሰሙ ዘንድ አጥብቀን እንማፀን።

ሳሚ ቶማስ(አሻፈንቡርግ)

## “የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም„

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦች መኖሪያና መናሃሪያ የሆነች ሀገር መሆኗ ለማንም ግልፅ ነው። በሃገሪቱ የሚገኙ ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸው መለያና የየማንነት መግለጫ ቋንቋ ባህልና ልማድ ቢኖራቸውም በአንፃሩ ደግሞ አንድ የሚያደርጋቸው እሴቶችና የሚያጋሯቸው አያሌ ቁሳዊና መንፈሳዊ የአኗኗር ዘይቤዎች አሏቸው። ከዚህ በበለጠ ደግሞ ለዘመናት የኖረና የዳበረ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በመሃላቸው ነበር አለም። በሀገሪቱ ረጅም ታሪክ በዛሬዋ ኢትዮጵያ የተካተቱ ብሄር ብሄረሰቦች መልካሙንም ሆነ አስከፊውን አጋጣሚና ሂደት በአብዝሀኛው አብረው አሳልፈዋል። ከቅርብ ዘመን ጀምሮ ከዘመናዊ ማዕከላዊና ዓለምአቀፋዊ አስተዳደር መዘርጋት ጋር እንዲሁም ከዓለምአቀፋዊ ክስተቶችና ሂደቶች ጋር በተያያዘ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ የሀገራችን ፖለቲካ አብይ ጉዳይ ቢሆንም የብሄር ብሄረሰቦች ግንኙነት እና የዘመናት ትስስር አያሻከረውና እየሸረሸረው ይገኛል። በእርግጥም በቀድሞው ዘመን የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት አልነበረም ራስን በራስ የማስተዳደርና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትም አልነበራቸውም አሁን በአለንበት ዘመንም የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ሰፍኗል ራስን በራስ የማስተዳደርና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸውም በተግባርና በተገቢው መንገድ ተረጋግጦላቸዋል ለማለት ያስቸግራል። ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘበት 1983 ዓ.ም. ጀምሮ የሽግግር መንግስቱ ቻርተርና በኋላም በህገ መንግስቱ የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነትና ራስን በራስ የማስተዳደርና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ትኩረት ሰጥቶ አስተናግዶታል። መሰረታዊው ጥያቄ ግን ውጤቱ ምንድን ነው? የሚለው ነው። የብሄር ወይም የጎሳ ግጭት እንደ ኢትዮጵያ ባለ ብዙ ህብረብሄር አገር የተለመደና ለዘመናት የቆየ ቢሆንም በመንግስት የተወሰደው በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርአት የመመስረቱ እርምጃ ግጭቶቹ እንዲስፋፉና አዲስ መልክ እንዲይዙ አድርጓል። ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ የፌዴራል መንግስቱንና የክልሎችን የውስጥ አስተዳደራዊ አወቃቀርና የስልጣንና የሀብት ባለቤትነትን ምክንያት ያደረጉ የብሄር ወይም ጎሳ ግጭቶች በየቦታው በተደጋጋሚ እየተከሰቱ ነው።ይህ የሚያሳየው ፌደራላዊ የአስተዳደር ስርአት ለሀገሪቱ ተመራጭና ዋነኛው ግጭቶችን ሊፈታ የሚያስችል የአስተዳደር ዘዴ ቢሆንም አሁን በሀገሪቱ ካለው ችግር አንፃር እንደገና ሊፈተሽና ሊጠና የሚገባው ነው። ቋንቋን መሰረት ያደረገው የ17 ዓመቱ የፌደራላዊ ስርአት ጉዞ ተመክሮ መንግስትን ከእንቅልፉ ሊቀሰቅሰው ይገባል። ፌደራላዊ ስርአቱ በብሄር ብቻ ላይ የተመሰረተ መሆኑንና በአተገባበር ረገድ ያስከተለው ውጥንቅጥ በተደጋጋሚ ብሄርን ከብሄር በማጋጨት ለብዙ ህይወት መጥፋትና ንብረት መውደም ቀዳሚ ምክንያት ሆኗል። እስካሁን ባለው ሂደት ብሄር ግጭቶች አያሌ ሰዎችን ለህልፈት እና ለስደት ዳርጓል። ሆኖም ግን ግጭቶቹ የተለያዩ ብሄረሰቦችን የአንድነት ስሜትና የሚያስተሳስራቸውን የ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ስርአት ህግ እጅግ አስጊ በሆነ መንገድ እየገዘገዙት ነው።ይህ አሁን ባለንበት ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ መንግስትም የዘረጋውን ስርአት ዞር ብሎ ለመፈተሽ ፍላጎቱና ፍቃዱ ከሌለው የወደፊቱ የአገሪቱ እጣ ፋንታ ምን ይሆናል? የሚለው የ አብዝሀኛው ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየላላ የሚሄደው በብሄረሰቦች መካከል ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስር ውሎ አድሮ ወደ የርስ በርስ ጥላቻና አንዱ ሌላውን ላጥፋው ወደሚል ስሜት አያመራም ማለት አይቻልም። በመንግስት ጣልቃ ገብነት እና ሀይል የሚበርደውና በትንሽ የአስራዎችን በዛ ሲባል ደግሞ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት የሚቀጥፍ የብሄር ግጭት የመንግስት ሃይልና ጡንቻ በተዳከመ ግዜ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት መቅጠፉም የማይቀር ነው። ይህንን ስጋት ተጨባጭ የሚያደርጉ ወቅታዊ ሁኔታዎች አሉ። ሀገራችን በአሁኑ ወቅት በሶማሊያ ባለው አለመረጋጋትና መቋጫ ባልተገኘለት የኢትዮ–ኤርትራ የድንበር ውዝግብ ተወጥራለች። ሁለቱም ጉዳዮች እየተባባሱ ያለውና ውለው አድረው የመንግስትን ሃይል የሚፈትኑና ሊያመነምኑ የሚችሉ ናቸው።የሀገሪቱም የውስጥ ፖለቲካ የተስተካከለ መስመርና ስርአት ከመያዝ ይልቅ ችግሮቹ ሳይነኩ ተዳፍነዋል። ከዚህ ባሻገር በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በተለይ በሱዳን እና ኬንያ እየተከሰተ ያለው ፖለቲካን መነሻ ያደረገ የብሄር ግጭት የዘር ማጥፋት እንቅስቃሴ በሀገራችንም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው የብዙዎች ግምት ነው። በአንድ አጋጣሚ በሚፈጠር ውጫያዊ ወይም የውስጥ መንስኤ የፌደራሉ መንግስት ሀይል ቢዳከምና ፖለቲካዊ ቀውስ ቢፈጠር ህዝብ የሚፋጅበት የብሄር ግጭት የመከሰቱ አደጋ የጎላ ከመሆኑ ባሻገር ሃገሪቱን የመበታተን አቅም ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ አደጋው ሊከሰት አይችልም ከማለት ይልቅ ሊከሰት ይችላል ብሎ ያለፈውን ተሞክሮ መመርመርና የፌደራል አስተዳደር ስርአቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን መፈተን የወቅቱ የመንግስት ተቀዳሚ ትኩረትና ስራ መሆን አለበት። አበው ሲተርቱ “የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም„ እንዳሉት ኢህአዴግ በድፍረትም ይሁን በጭንቀት ብሄርን ማዕከል ያደረገ የፌዴራል ስርአት ዘርግቷል። የፌዴራል ስርአቱ የብሄር ግጭትን በመቀስቀስና በማባባስ ለኢህአዴግ ለህዝቡና ለሀገሪቱ ህልውና አደጋ የመሆን አዝማሚያው እየጎላ በመምጣት ላይ ነው፣ የነብርን ጅራት የያዘ ሰው ጅራቱን ቢለቀው ነብሩ ይበላኛል በሚል ፍርሃት እስከ ወዲያኛው እንደያዘው ይቀጥላል ተብሎ አይታመንም። ረዳት ወይም ጥሩ አጋጣሚ ሲያገኝ ለቅቆ ማምለጥ አለበት መንግስትም ከምሁራንና ከህዝብ የሚቀርበውን ጥያቄ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድ እና እንደ አጋዥ ሃይል በመቁጠር የፌዴራላዊ አስተዳደርና አወቃቀር ስርአቱን በመፈተሽ ሀገርንና ህዝብን በሚጠቅም መንገድ ሊያሻሽለው ይገባል፣ ህዳሴ ከዚህ ይጀምራል።

ቶማስ እሸቱ(Würzburg)

## ልጅ ከሆነ ይገፋል።

የሶስት ሺህ አመት ባለታሪክ የሆነች አገራችን ኢ.ትዮጵያ በረጂሙ የታሪክ ጎዳና ክፉንም ደጉንም እንዳመጣጡ ስትመልስ ቀላል የማይባል ዘመናት የየራሳቸውን የታሪክ አሻራ ትተው አልፈዋል።

ሐብቱን ለመዝረፍ ነፃነቱን ለመግፈፍ ባህር ቀዝፈው የብስ አቋርጠው የመጡ ጠላቶች የተለያየ ቋንቋና ባህል ያላቸው ህዝቦቻችን እንደባህላቸውና ቋንቋቸው ለመለያየትና በጠላትነት እንዲተያዩ ለማድረግ የነበራቸውን ህልም ቅዠት በማድረግ ያላቸውን የደም አንድነት በደማቸው አረጋግጠው የተከበረችና የታፈረች አንዲት ኢ.ትዮጵያን የግዛት ወሰን በአጥንታቸው አትመው ሰላም፣ ነፃነት፣ ብልፅግናን የሚሰብኩ ሦስት ቀለማት በአንድነት የተቆራኙበት አላማን በሰንደቅ  ህዝቡ በአንድ ጥላ ስር ተሰባስቦ ባገኘው ነፃነት ሰላምን እንዲያጣጥም በሰላም ጣዕም ደስተኛና የሠለጠነ ለአፍሪካ ህዝቦች ነፃነት ኩራት እንዲሆን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አድርገው ሞተው የማይሞት ታሪክ በደማቸው ይፋ አድርገው አልፈዋል።

የአባቶቻችውን ያልሞተና ከቶም የማይሞት ህያው ታሪክን የተረከቡ አባቶቻችንም የእነርሱን ፈለግ በመከተል ያልተበረዙ ያልተከለሱ ከወርቅ በላይ በእሳት የተፈተነ የጠራ የኢ.ትዮጵያዊነት አመለካከትን በማንገብ በአባቶቻቸው መንገድ በጠላት ቀስት ወድቀዋል፣ ደምተዋል ላይመለሱ በሞት አሸልበው የአገራቸውንና የባንዲራቸውን ክብረ መልሰው ፋሺስቱንም እንዳይመለስ ሸኝተዋል።

ከጦርነት የተረፉ ፋሽስቶችም ለባንዲራችን ሳይወዱ በግዳቸው ክብር በመስጠት የኢ.ትዮጵያን የነፃነት ምልክት ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ የነፃነት ተምሳሌት አድርገው ተቀብለውታል።

እንግዲህ እነሆ ለዘመናት ጠላቶች ተለይተዋት የማያውቋት ሀገራችን ኢ.ትዮጵያ ነጻነቷንና የግዛት ድንበሯ የተከበረው በባንዲራዋ ጥላ ስር በአንድነት ተሰባስበው መሆኑ ሲ.ታሰብ ደግሞ የሰንደቅ ዓላማችን ክብር እምን ድረስ እንደሆነ መገመቱ ከህሊና በላይ እንደሆነ ከወያኔ/ኢ.ሕአዴግ በቀር ሁሉ የሚስማሙበት የሐቅ አንኳር ነው።

ይህን የአንድነት የአትንኩን ባይነት ትኩሳት የታላቅ ተስፋና የእምነት ምስጢር የሆነውን ባንዲራችንን ከሐዲው የወያኔ/ኢ.ሕአዴግ ቁንጮ መለሰ ዜናዊ "<u>ጨርቅ</u>" ሲል ማጣጣሉን የሰማ በልቡ ያላነባ ቢ.ኖር ተናጋሪው መለሰ ብቻ ነው።

ታዲያ ዛሬ ምን ተገኝቶ ነው እብሪተኛው መለሰ ዜናዊ የኢ.ትዮጵያን ባንዲራ ለማክበር የፈለገው? የሚል ጥያቄ በሁላችንም አእምሮውስጥ የሚመላለስ ጥያቄ ነው።

የኢ.ትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞም ባንዲራውን ያከብራል፣ ይወዳል ለክብሯም ይሞታል።

የክልል አሻንጉሊት መሪዎችስ ከመለሰ እጅ የተቀበሉት ባንዲራ ቀድሞ አያውቁትም? ወይስ ለየክልሉ የተለያየ ሰንደቅ አለማ አስፈልጓቸው ነው። ዶሮን ሲ.ያታልሏት ነው ነገሩ። ይህ ከሆነ አሁንም እያታለሉን ነው።<u>**ያበጠ ሆድ ሁሉ በውስጡ ልጅ የለም።**</u> ወያኔ- ኢ.ሕአዴግ ባንዲራዋን የሚወድና የሚያከብር ከሆነ እንደባንዲራዋ አህዳዊ መንግስት መመስረት፣ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር የግድ ነው። ይህ ከሆነ የኢ.ትዮጵያ ህዝብም ባንዲራዋም ለዘላለም ይኖራሉ።

ድል ለኢ.ትዮጵያ ህዝብ።
ቤተል ወንድሙ(መንደን)

---

## የወያኔ ግፍ መቼም አያበቃም

የአንድ ህብረተሰብን እድገት ከሚጎትቱ ጉዳዮች ጎታች ባህሎች፣በሽታና ርሀብ እንዳሉ ሁነው ሃላፊነት የጎደለውና ዴሞክራት ያለሆነ የአምባገነን ስርአትም በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ለዚህም በአሁኑ ሰዓት ያለህዝብ አመኔታና ድጋፍ ስልጣን ተቆናጥጦ ያለውን "ዴሞክራሲያዊ" ለመምሰል እየሞከረ የ አንድን ጎሳና ግለሰብ አምባገነናዊነት የሰፈነባት አገራችንን መመልከት በቂ ነው።
ይህንን አስከፊ የጭቆና አገዛዝ እንዲያበቃ ለማድረግ አያሌ የተቃዋሚ ሀይሎች በተለያየ ግዜ የተለያ የትግል መስኮችን ሲሞክሩ ቆይተዋል።ይሁን እንጂ በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ማለትም የህዝቦች መብት ተከብሯል፣ በሀገራችን ሰላም አለ፣ ነፃ የኢ.ኮኖሚ ገበያ እየገነባን ነው። ወዘተ ወዘተ የሚለው ልፈፋ የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ አልቻለም። የወያኔ የውሸት ተውኔት እርቃኑን ቀርቷል።የወያኔ መንግስት ያጣውን የህዝብ ድጋፍ ለመበቀል በተለመደው የጭፍጨፋና ግፍ ህዝቡን በማሰቃየት ላይ ይገኛል።

ሶስና ኤፍሬም (ቩርዝቡርግ)

---

## <u>የሀገራችን ህልውናና ደህንነት የሁሉም ዜጋ ሐላፊነት ነው</u>

ሐገርን ለመገንባት ዴሞክራሲ ለማስፈን የሕዝብ ነፃነትና ብሔራዊ አንድነትን ለማምጣት መንግስት ግንባር ቀደም መሪ መሆን ሲገባው ወያኔ ግን ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጨት የጎሳ ፖለቲካ በማራገብ በስልጣን ላይ ለመቆየት ብቻ በሚያደርገው ደፋ ቀና ሀገርን መበታተንና አስከፊ ውድቀት እያደረሰ ይገኛል።
በዚህ ሁኔታ አሁን ሀገራችን ኢ.ትዮጵያ ያለችበትን የመከፋፈል አደጋ ሲ.ታይና በዚህ ከቀጠለ ነገ ሊፈጠር የሚችለውን ደም ለበስ ትርምስ እናሰላስልና ያለብን የግለሰብ ይሁን የድርጅት መቆራቆስ ወዲያ ጥለን ትንሽ ትልቅ ሳንባባል ለሀገራችን ህልውና ና ለሕዝባችን ደህንነት ስንል መርሐዊ አንድነትን ፈጥረን ከፋፋይ ወያኔን/ኢ.ሕዴግን በአንድነት መታገል የግድ ይላል። የአንድነት ትግል የማይደረምሰው ጨቋኝ ስርዓት ሊኖር አይችልም።

ሙሉቀን ዓለም

# የእነማን አለብን የአገዛዝ ስርዓት

የነፃው ፕሬስ ውጤቶች ሆኑ መላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ የህግ የበላይነት መልካም አስተዳደር ዲሞክራሲ ፍትሃዊ አሰራር ዕድገትና ብልፅግና እንዲሰፍን ያለማቃረጥ ይጠይቃል። ሁሊም ግራ በመጋባት ህልውናውንና ሀገሩ የርሱ መሆኗን በመጠራጠር ያሰላስላል። በእርግጥም ነገሩ ግራ ያጋባል።

በአንድ ሀገር የመንግስት አመራር ውስጥ በጠበንጃ አፈሙዝ የሀይል መሰረት ላይ የተቀመጠ አናሳ ቡድን "እገዛለሁ" የሚለውን ሀገር ታሪክ ። አንድነት ሕዝባዊ እሴቶች በሰላማዊ ቅርሶች የኢኮኖሚ እድገትና ተቋማቱን እያወደመ የትምህርት ስርአቱ እያሽመደመደ የወታቱን ተስፋ እያጨለመና ሁልግዜም ህዝቡን በሽብር እያመሰ የሚንቀሳቀስ"መንግስት" ምን ብለን እንደምጠራው ግራ አጋብቶናል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ህይወት ማለት እርግጠኝነት የሌለበት የጨለማ ከበባ ማለት ነው። ወያኔ ከሚያራምዳቸው ስትትረራቴጂያዊ ድርጊቶች ስንመለከት ይህን የጨለማ ከበባ ዘመን ቁልጭ አድርገው ይገልጹልናል። እነሱም የማያባራ ሽብር የህዝብን እርስበርስ መናከስና ቅጥፈት ናቸው።እነዚያ ሰይጣናዊ መሳሪያዎች አንድ በአንድ እንመለከታለን።

1. በራሳቸው ውስጥ የተረጋጋ አእምሮ የሌላቸው ሰዎች ለቤተሰባቸው ለጎረቤታቸው ለስራ ባልደረባቸውም ሆነ ለሌላው ህብረተሰብ ጤና ሊሰጡ እንደማይችሉ የስነልቦና ተመራማሪዎች ደጋግመው የሚገልጹት ነው። ወያኔ በሽብር ተወልዶ በሽብር አድጎ በሽብር ስልጣን ላይ የሚገኝ ነው። ህዝቡን ተቃማትን ህግን የዲሞክራሲያዊ ስርአቱን የሰከነ መስተዳደርን አይወድም። የገዛ ጥላውን ሳይቀር አያምንም። በህዝቡ መካካል በመስተዳደሩ ውስጥና በተቋማት ይዘት ውስጥ የማያባራ ሽብር በመፍጠር ስልጣኑን ለመቀጠልና ለማራዘም ይጥራል።

በአለፉት አስራ አራት አመታት የፌደራልና የክልሎች አስተዳደር በተለያዩ ጊዚያት የመዋቅር ለውጥ በማድረግ አተራምሷቸዋል። የቀበሌ መስተዳደሮችንም ለመርካታ ጊዚያት በመሰለውና በፈለገው ወቅት ቀይሯል። መስተዳደሩን ለሚፈልጓቸው ባለሟሎች ስልጣን ሰጥቷል።የማየፈልጋቸውን ሰንካላ ምክንያቶች በመስጠት ከስራ አባሯቸዋል። ጠበቅ ሲልም በስውር ይገድላል ያስገድላል። በማንኛውም የስራ መስክ ማንም ሰው ተረጋግቶ የስራ ዋስትና ተሰምቶትና ህጋዊ ዋስትና ኖሮት በሰላምና በነፃነት የሚኖር የለም። ብዙ ግዜ እንደታየው ከሆነ ሰዎች ከስረራ እንዲባረሩ የሚደረጉት በሚያሳዛን ሁኔታ ብሔራዊ በዓላትን በማስታከክ ነው። ይህ አይነት እርምጃ ሆነ ተብሎ የሰዎችን መንፈሳዊ ሽብርና ቤተሰባዊ ሰቆቃ ከፍ ለማድረግ ሲባል ነው። ሌላው ወያኔ ወደ አገዛዝ ስርአት ራሱን ካስቀመጠበት ግዜ ጀምሮ በሰራተኛው ህዝብ ላይ በተከታታይ ወቅት እየፈፀመ ያለው የማሸበሪያው ሰዓት ግምገማ ነው። ግምገማ ማንንም ሰው ሰጥ ሰጥ አድርጎ ለመያዝ የተነደፈ የዲክታተሮች መርህ ሲሆን አሁን ከስራና ከስልጣን ለማፈናቀል የሰዎች ሰብአዊ ክብር ለማዋረድ፣ ሀገራዊና ህዝባዊ አመለካከት ያላቸውን ለማስወገድ ለሚያደርጋቸው ፀረ-ዲሞክራሲያዊና ኢ- ሕዝባዊ በሆኑ እርምጃዎች ሽፋን ለመስጠትና ሰራተኛውን እርስበርሱ ለማናከስና የጥርጣሬ ሽብር ለመፍጠር ወያኔ ግምገማን ዋና ስራዬ ብሎ ይጠቀምበታል። በግምገማ አለቃን ከጭፍራ፣ ጭፍራ ከአለቃ አናክሷል ርስበርስ በአይነ ቁራኛ እየተጠባበቁ እንዲኖሩ ያደርጋል። ሕዝብ የተረጋጋ የመኖር ዋስትና እንዳይኖረው ተከታታይ ሽብር መፈጠርን እንደዋና የስራ ፖሊሲ አድርጎ ይጠቀምበታል።

2. በሕዝብ መካከል የእርስበርስ መናቋርና ጥላቻ እንዲስፋፋ በማድረግ ሰይጣናዊ ስራ የሚተገብረው ደግሞ ሕዝብን በጎሳ ከፋፍሎ እርስበርስ በማፋጀት እያናከሰ አስታራቂ ሆኖ መቅረብ ነው። ይህም የሀገሪቱ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ህዝቦች ሰላምና መረጋጋት አግኝተው በመከባበርና በመተማመን ኢትዮጵያ ሀገራችን ብለው በአንድነት ለመኖር እንዳይችሉና ሀገሪቱን በቀጣይነት በቀላሉ ለመበታተን እንዲቻል ታስቦ የሚሰራ የወያኔ የረዥም ግዜ ፕሮግራም የማይታበል ሃቅ ነው። ኢሕአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ ትበታተናለች ብለው አቶ መለሰ በግልፅ እየነገሩን ያለው ጉዳይ እኮ ነው። እስካለን የልባችንን እንሰራለን " እኛ ከሌለንና ስልጣን የምናጣ ከሆነ ግን አጥፍተናት እጠፋለን" በሚል የመሰላቸው የፃፉት ስራዎች በየግዜው ያለማሰለስ እየሰሩ ናቸው።

3.የዘመናችን የሀሳብ ድንክዬዎችና የራዕይ ውርንጭላዎች ሀገሩ እየጠፋ ስነልቦናዊ ጦርነት እየተስፋፋ ውዥንብር እየነገሰ ሊሄድ የቻለው በሚፈጠረው የቅስፈት ፕሮፓጋንዳ ነው። ዲሞክራሲ መልካም አስተዳደር የህግ የበላይነት የብሔረሰቦች እኩልነት ፈጣን እድገት በልቶ ማደር የአቅም ግንባታ ወዘተ ይሉናል። በተግባር የምናየው ግን የተገላቢጦሹን ነው፡ በእውነተኛ መርህ የሚመራ ዲሞክራሲ ብዙሀኑን የበላይ ነቱን የሚያረጋግጥበት አናሳው መብቱ የሚረጋገጠበት ሲሆን እንደ አሜሪካኖች አባባል ደግሞ ጥሩ ዲሞክራሲ ለሕዝብ፣ በሕዝብ ፣የሕዝብ ፈቃድ የሚንፀባረቅበት ነው። በእኛ የተገላቢጦሽ ነው የሚያሳየው አናሳው የሚገዛበት ብዙሀኑ የሚጨቆንበት ሕዝባዊ ፈቃድ ያላገኘ ነው። እየተሰራበት ያለው የብሔረሰቦች እኩልነት ሳይሆን የአንድ አናሳ ብሔር የበላይነትና ጭቆና እንዲነግስ እየተደረገ ነው። በአሁኑ ወቅት ከምንግዜውንም በከፋ ሁኔታ ብሔረሰቦች የተናቁበት የተዋረዱበት የተመዘበሩበት በትምህርት ልዩነት ወደኋላ የቀዩበት መሪዎቻቸው የታሰሩበትና ደብዛቸው የጠፋበትና ሐገራዊ አርአያቸው የከሰመበትና ብዙሃኑ ከድህነት ወለል በታች የሚማቅቅበት ነው።

በመሆኑም ሐገራችን በአሁኑ ግዜ በነዚህ ሁሉ ውስብስብ ሰው ሰራሽ ችግሮች እግር ከወርች ታስራ ከድህነት ወለል በታች የምትገኝና ሕዝቦቿም ምንም አርአያ የሌላቸው ሆነው ወራትና ዘመናት ሂደታቸውን ጠብቀው የሚጓዙበት ቢመስልም የችግርን መፍትሂ መፈለግ የ እያንዳንዱ የሀገሪቱ ዜጎች ግዴታ ስለሆነ ሁሉም በእያለበት ግዴታውን ለመወጣት ምንግዜም ያላሰለሰና ቀጣይነት ያለው ስራ የሚጠበቅ ነው።

በእምነት ተክሌ ጌትነት( ፎርዝቡረግ)

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

# ግጥሞች

## ኢ.ሕ.አ.ፓ

ኢ.ሕ.አ.ፓ ነው በተረፈ !!
ብዙሐኑን ሕብረ ብሔር ያሳተፈ፣
በትግል ተፈትኖ ያለፈ።
ኢ.ሕ.አ.ፓ የሕዝብ አለኝታ፣
የሚታገል ሳያመነታ፣
ወያኔን እስኪረታ።
አሁንም ሕዝቡ ከጎኑ ነው፣
ይደግፈዋል እንደቀድሞው።
ሰለቸኝ ሳይል የሚታገል፣
በጽናቱ የሚቀጥል፣
ኢ.ሕ.አ.ፓ ነው የሚያበቃን ለድል።
እደግፈው አብረን እንንጓዝ፣
ሕዝብ ስልጣን እስኪይዝ።
ሕዝብ ተነስ ታጠቅ !
በሐሳብ አትጨነቅ፣
አይቀሬ ነው የወያኔ መውደቅ።
ኢ.ሕ.አ.ፓ ያውቃል መንገዱን፣
የትግል ውጣ ውረዱን፣
ሽንፈቱና ድሉን፣
እንታገል ከጎኑ ሆነን።
ኢ.ሕ.አ.ፓ አሁንም ይጣራል፣
ሕዝብን ለድል እናብቃ ይላል፣
ጥሪው ነው ሰምተን እንከተል።

ኤርሚያስ አፈወርቅ(Wisbaden)

## በስልጣን መመካት

ሕግን አለማክበር በስልጣን መመካት፣
ሕዝብን ንቆ መኖር ያደርሳል ከውድቀት።
ቀን የጨለመ እለት የያዙት ሲጠፋ፣
አለሁ የሚል ሲርቅ ወዳጅም ሲከፋ፣
መሄጃው ይጠፋል ሜዳው ይሆናልፈፋ።
በስልጣን መመካት ሕዝብን ማሰቃት፣
ሕፃናት ተርበው ሲያለቅሱ መደሰት፣
መውጫ ይጠፋዋል ቀን የጎደለ እለት።
በሕዝቡ እየማለ በስሙ ለምኖ፣
ብሶቱን እንዳይገልጽ በጠሩ አፍኖ፣
አስሮ ያሰቃየዋል ልጆቹን በትኖ።
ፍርድ ቤቱ የሱ ፈራጅ ዳኝ እሱ !
እራሱ አጥፍቶ እራሱ መክሰሱ፣
ስንቱ ተሰቃየ ሕግ በመጣሱ ?
ሕዝብ ወክለን ብለው በስሙ ምለው፣
ምንም ሳይፈይዱ ወንበር አሙቀው፣
ሐገር ይዘርፋሉ ፓርላማ ገብተው።
በስልጣን መመካት፣
በስተመጨረሻው ያደርሳል ከቅሌት።

ከኤሊያስ የማነ (ሆፍ ሐይም)

## እስከ መቼ

በሳባ ኢዛና ታሪክሽ ቆንጆ ነው
በአፄ ካሌብ ልብነ ድንግል እኛ የምናውቀው
በጣሙን አዘንኩኝ ሳየው ያንችን መሪ
ይብቃሽ እናት አለም አሁን ግን አምርሪ
በደም የሰከረ ሀገር በቀል ባንዳ
ከስሩ ይነቀል ይድረስበት ፍዳ
አለባቸው እዳ የስንቱ ህይወት
ማህፀንሽ ሳይደርቅ ተመልከች እማማ የስንቱን ህልፈት
በስንቱ ተጎዳን እኛ ልጆችሽ
በቃ አይጠቅመንም ይጥፉ ከምድርሽ።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!
ሞሚና አህመድ

## ጠንክረን እንነሳ

እናት ሀገራችን ስትቆስል ስትደማ
ልጆቿ በርሃብ ሲያልቁ ስንሰማ
የሞተውስ ይሁን ነፍስ ያለው ሲቀበር
የወገኔ ጩኸት ውስጤን አሽማቆ ሲንቀረቀር
የፈሰሰ ደሙ በየመንገዱ ዳር
እንዲሁ እንደዋዛ በመና እንዳይቀር
ተነሱ ወገኖች አረ ዝም አትበሉ ሁላችሁ
ምስኪኑ ወገኔን ተጎሳቁሎ እያያችሁ።
ይኸው ደግሞ አሁን አሻፈረን ብሎ በድምፁ ሲቀጣ
ወያኔዎች አያፍሩም አመጡብን ጣጣ
ኅበዝ ክንዳችንን አስተባብረን ጠንክረን እንነሳ
ወያኔን ገርስሰን ኢትዮጵያ ትነሳ።
ከዲጃ ላሎ

## መብት ለማስከበር

ሙቀት ግለት ሆኖ ችቦ ሲያቀጣጥል
ፋና ወጊ ሆኖ ልብን ሲያንቀለቅል
መብት ለማስከበር ለነፃነት ትግል
ጎሰኛን ሊያጠፋ ከስር ሊመነግል
እሳት ሆኖባቸው የህዝባችን ትግል።
ለመብት የታገሉ በነፃ ድምፃቸው
ዲሞክራሲ ጠፍቶ በናት ሀገራቸው
መሳሪያ ባይፈሩ ወኔ ሳይከዳቸው
መልዕክት ተስተጋባ ከሰሙ ገኘአቸው
የትግል እሳቱ በአዕምሮአቸው ገብቶ
ቀየው ተቀጣጥሏሎ ትውልድ አሰተጋብቶ
ውስጣችን ተጣርቶ ለነፃነት ፈክቶ።
ወኔያቸው ተነስቶአል መንፈሳቸው ሞቆአል
ለነፃነት ለመብት ልቦናቸው ተነሳስቷል
ኢትዮጵያዊ ወኔ ችቦው ተቀጣጥሏል
የነፃነት ጉዞ ዛሬም ህያው ሆኗል።
ጎራዴው ቢመዘዝ መከራ ቢከመር
አካሉ ቢሰዋም ቢወድቅ ለሀገር
ከቶ አይፈታም ይህን መሰል ማገር።

ፍሬ ዘውድ ነጋሽ( ቢሾፍስሃይም)

## ነቀርሳ ነው

እማማ ምጥሽ ጣርሽ በዛ፣
የወለድሽው እንዳይባረክ  እንዳይበዛ።
ይጠረኛል ያልሽው የባረክሽ፣
በሽታ ረሃብን በምድርሽ፣
ጉቦ፣ ፍትህ አልባነትን በቤትሽ።
ከእኩይ ሰይጣን ጋር ተመካክሮ፣
ሲጨፍር ለሚ ድር፣ በኀጠኝነት ታውሮ፣
ልፍትህ ሰላምሽ አለመስምር፣ ለሚታገል አእምሮ፣
ለልቅሶ ዋይታሽ፣ ላጣ ጆሮ።
እንዲህ ላለው አተላ፣
በቁሙ በስብሶ ለተላ፣
የአገር ሸክም ቀፎ መዝጊያ ግልብጥ ሌባ፣
ስሙ በታሪከ መዝገብ  ለማይገባ።
እክ እነትፍ ብለሽ አውጭው፣
ድሮመ ከፅንሱ ነቀርሳ።

ጌታምሳ ሞገስ(ከሃናው)

## ስደት ብሎ ኑሮ

ከሀገር ከወላጅ ከቤተሰብ ርቆ፣
ደስታ የማይሰማው ሁልጊዜ ተጨንቆ፣
የሚፈልገውን በውስጡ አምቆ።
ለምን ይሰደዳል የሰው ልጅ ከሐገሩ?
ዴሞክራሲ መብቱ ባለመከበሩ፣
ዴሞክራሲ መንግስት ከሌለ በሀገሩ።
ከሐገሩ ወጥቶ በማያቀው ሐገር፣
ቋንቋው ጠጥሮበት ሲጠፋው መናገር፣
ይረግመው ጀመረ የወጣበት ከሐገር።
ተሰዶ መኖሩን ማንስ ሰው ይመርጣል?
ስቃይን ለማየት ከሐገሩ ይወጣል?
ዴሞክራሲ ቢኖር በትውልዱ ሐገር፣
ተሰዶ መኖሩን ለምን ይመርጥ ነበር?
ስደት ብሎ ነገር ሐገር ጥሎ መውጣት፣
ራስን አድን ብሎ ዳግም መሰቃየት።
የዓለም መንግስታት እዬት በደላችን፣
መታሰር መገደል ፍትህ ማጣታችን፣
ሕግ አለመከበር በኢትዮጵያ ሀገራችን።
የሰው ልጅ መታሰር የሰብአዊ መብት መጣስ፣
ሕይወት ትርጉም አጥቶ የሕዝባችን ማልቀስ፣
ምን ይሆን ፍርዳቸሁ እናንተ ጋ ሲደርስ።
በጣም ስለበዛ የሚያጠፋው ሕይወት፣
ተፅኖ አድርጉበት በዘረኛው መንግስት።
ስደት ብሎ ነገር መኖር በሰው ሐገር
ምንም ሰላም የለም ሁልጊዜ መሸበር።

ሪታ ገዛሽኝ (ሆምቤርግ)

## ትግላችን

ወያኔ/ኢህአዴግ የኛ ጠላታችን፣
እድሜውን  አራዝሞ ሆኗል በሽታችን፣
ኀበዝ ተሰባሰብ ይቀጥል ትግላችን፣
እድሜ እንዳይኖረው በዚች ባገራችን።
መስሎት ይሆን ሊኖር ይህ ኀጠኛ መንግስት፣
አንዱ ካንዱ አጣልቶ እውነት ሊሰነብት፣
ስሩን ሰዷል ያ ወያኔ ነብሰ በላው ዱር አራዊት።
ቸ! በል ጀግና ይብቃን መሰቃየት፣
በስደት በእስር ቤት፣
ትግላችን ይፋፋም ወያኔን ለማጥፋት።

ሳባ ክፍሉ(ኖይ ኪርሽን)

## የተዳፈነ እሳት

በወርሃ ግንቦት የተቀጣጠለው
የዴሞክራሲ እሳት የሚንቀለቀለው
የወያኔን ጎራ ያተረማመሰው።
በ አጋዚ ጥይት ቢመስልም የጠፋ
ጋደም አለ እንጅ መቼ አንቀላፋ።
የነፃነት እሳት ያርበደበዳቸው
የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ ያስደነገጣቸው
የሞት ሽረት ትግል ሆኖም ምርጫቸው።
ንፁሃን ዜጎችን ቢገድሉና ቢያስሩ
መርዛማ ስራቸውን ቢረጩ ቢዘሩ
ሕሊና ካላቸው ከታሪክ ይማሩ።
የነፃነት እሳት አንዴ ከነደደ
ሊጠፋ አይችልም አጥፊን ካልወሰደ።
ባባገነን መሪ በጠባብ ዘረኛ
በውሸታም ከሃዲ ሆድ አደር ቅጥረኛ
ኢትዮጵያ አትገዛም ሞተን ሳናልቅ እኛ።
ወንዝ ሐይቁ አልቆ ውሃ ስንጠማ
በለምለም አፈር ላይ ዳቦ ስንሻማ
ምነው ዘዴ ጠፋ ለኛ የሚስማማ?
ቤታችንን ለቀን የሰው ቤት ስንጠና
ጉዳችንን ችለን ሸፍነን ገበና።
ልመናችን በዝቶ ችግራችን ከሮ
እየደበደብን የቅሌት ከበሮ
ዘለላለመም መከራ ዘላለም እሮሮ
መሞት ይሻለናል ከዚህ አይነት ኑሮ።
የተዳፈነ እሳት መጨሱ መች ቀረ
አመድ ሆኖ አልቀረ እንደተቀበረ።
ብረዛው አፈናው ብተናው ቢከፋ
መንደዱ አይቀርም አትቁረጡ ተስፋ።
ኢትዮጵያዊው እሳት እንደገና ሲነድ
አጥፊውን ማገዶ ያደርገዋል አመድ።
ተዳፈነ እንጂ አልጠፋም እሳቱ
ይለቀም ቅጠሉ ይፈለጥ እንጨቱ
ቆስቆስ ቆስቆስ አርጉት ወገኖች በርቱ
በነፃነት ብርሃን እንዲነጋ ሌቱ
ለመቼ ሊሆን ነው ኢትዮጵያዊነቱ።
ንጋት ታደሰ(ፑርዝበርግ)

## ታጋይ ጓዶቻችን

ቀደብ ብለን ነበር ያወጅነው ነፃነት፣
ዳሩ ምን ይሆናል መብት አልተገኘበት።
ምድጃ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም፣
አበው ሲተርቱ ደረሰብን በእኛም።
በእኩልነት መንገድ ነፃነት ቢታወጅ፣
ብዙ ጓዶቻችን ተቀጠፉ ከደጅ።
ከስንዴ መካከል አይጠፋም እንክርዳድ፣
ኢሕአፓ ይውደም ተባለብን በግድ፣
ነፃ ውይይቱ ስለማይፈቀድ፣
በኮድ መወያየት ይለመዳል በግድ፣
ሌሊት በጨራቃ ነበር ፅሁፋችን፣
ለአላማ የፀኑ ብርቱ ጓዶቻችን፣
በጥይት እሩምታ በግፍ አለቁብን።
እናት መብት የላትም በይፋ ለማልቀስ፣
አባት መብት የለውም በይፋ ለማልቀስ፣
አንተ ሰው አነበብክ አንተ ጣልክ ወረቀት፣
እየተባለ ህዝብ ተዘጋ ወህኒ ቤት።
ስንቱን አሳለፍነው በዛ መበደል፣
አንድ ቀን በትግስት ውጤት ይመጣል።
ታጋይ ጓዶቻችን ዳግም ያብባሉ፣
አርማቸውን ይዘው ላገር ያበራሉ።
ሳይጨልም አይነጋም ለታገሰ ሰው፣
እድሜና ጤና ነው እኛ እምንጠይቀው።

ዮርዳኖስ ዮሐንስ(ሃለ)

## እነ አሉ -ምን አሉ?

እነ አሉ- ዴሞክራሲ ሞልቷል አሉ፣
ማሰር መግደል የለም የለም አሉ?
እነ አሉ የውሸት አባት፣
እነ የወሬ አባት መንግስት።
አሉ ርሃብ ችግር   የለም አሉ፣
ጥጋብ በጥጋብ ነው አሉ።
እነ የውሸት አባት የወያኔ መንግስት፣
ስማ አንተ ፍትህ አልባ መንግስት።
ሰፊው ህዝብ ጠንቅቆ ያውቅሃል፣
ያንተውን ማጭበርበር መቅጠፉን ማታለል።
ስማ አንተ የመለስ መንግስት፣
ስማ አንተ ጨቋኝ መንግስት።
ምንም ብትናገር የባጠ የቋጡን ፣
ምንም ብትሞክር ለመሸፋፈን፡
መቸም ጠንቅቆ ያውቅሃል አለም በውሸትህ፣
የምትናገረው የምታደርገው መሰሪ ተግባርህ።
ስማ አንተ የውሸት አባት፣
ስማ አንተ ፍትህ አልባ መንግስት፣
ይበቃል ማጭበርበር መዋሸት፣
ይበቃል ረግጦ ቀጥፎ መግዛት፣
እጅ ለጅ ተያይዘን ተነስተናል አንተን ለማጥፋት።
አንዳርጋቸው አስራት(ሞርስ)

## ግመሉ ወደቀ

ሌት ከቀን ጠብቀው ከጠላት መንጋጋ፣
ከፍለው ያሸለቡት የዜግነት ዋጋ።
ቅድም አያቶቻችን የበጅዋትን አገር፣
አፍርሶ ለመጣል አድርጎ እንዳልነበር።
የህዝብን አንድነት ህብረት አፈራርሶ፣
አገር እንደ ቁጢት ቆራርሶ በጣጥሶ፣
የታሪክ ይቅርታ የሌለው አደጋ፣
እድገት የሚያቀጭጭ ስርዓት ሊዘረጋ።
ወቅቱ ያዘቀጠው የነተበ አላማ፣
ወንዝ የማያሻግር የሆነ ደካማ።
አንግቦ ወያኔ ከጫካ ሲመጣ፣
ህዝባችን ገንፍሏል በንዴት በቁጣ።
የየብስና የአየር ባለቤቱን፣
የችግሩን ሁሉ አሸናፊነቱን።
ኢሕአዴግ በትዕቢት አሳጥቶት ዋጋ፣
በህዝብ ላይ ተረት ጀመረ ያወጋ።
"ምንም ሳያገደው ይጓዛል ግመሉ፣
ያቆሙት መስሏቸው ውሾች ይጮኻሉ፣"
አለና ወያኔ በሕዝብ ተሳለቀ፣
ዛሬ ምን ይዋጠው ግመሉ ወደቀ።
ስለ አወዳደቁ ለሚሻ መረጃ፣
እንባ ነው የጣለው አይደለም ጠብመንጃ።
ግመልና ውሻ ድመትና አንበሳ፣
እባብና ዘንዶ ዝሆንና ስሳ፣
ጭራሮና ዝግባ ሽክላና ብረት፣
የክብሪት ፍምና የቮልካኖ እሳት።
እያለ በዚህ መልክ እያመዛዘነ፣
ጥንካሬ ያለው እራስ እንደሆነ፣
የግመሉ ጉዞ እንደማይገታ፣
ቢያወራም ወያኔ በቃላት ጋጋታ፣
የግፍ ጭነት ይዞ ግመሉ ወደቀ፣
እርም ያወጣ ወያኔ አለቀ ደቀቀ፣
ኅልያድ ከትቢያ እንደተዘረጋ፣
ወያኔ ውድቀቱን ይቀበል በፀጋ።

መርድ ሐብቴ ይመር(ቮርዝቡርግ)

## አጋር

ሕይወት እስትንፋሱ ላይጠፋ፣
ወደፊትም ለማይጠፋ፣
ሕያውነቱን ያስፋፋ፣
ሲጮኽ በየቦታው በተስፋ።
መኖራቸውን በ ዕድሜ ላቆጥሩ፣
ሰማናቸው በድምፅ  አልፈውም በተግባር ።
አስተጋቡ ጩኸታቸውን የሕዝብ ሰቆቃን ፣
የሀገር መዳኛዋን ዐይደለም መጥፊያዋን።
አሁንም ይጮኻሉ፣
አለን እያሉ አለን እያሉ።

ባምላክ ፋሪስ

ወደ ገጽ 38 ይዞራል....

## የአምባገነኖች ሥርዓት በኢትዮጵያ

ሕዝባችን ለዘመናት የተጠናወተውን ከአንድ አምባገነን ወደ ሌላ አምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት ዝውውርን አሽቀንጥሮ ለመጣልና በምትኩ በነፃ ፍቃዱ በሚሰጠው ድምፅ የሚያቋቁመው ሥርዓትና የሚሰይመው መሪ ባለቤት ለመሆን ከሶስት አመታት በፊት በተደረገው ምርጫ ያደረገው ከፍተኛ ተሳትፎና ሰላማዊ ተጋድሎ ያሳየው ብስለትና ቆራጥነት ያስመዘገባቸው ድሎች በአገራችን ታሪክ ምን ጊዜም ሲታወስ የሚኖር እጅግ አኩሪ የፖለቲካ ግኝት ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ውድ አገራችን የሕግ የበላይነት የሰፈነበትና አንድነቷ የተከበረ ከቀጣይ የአምባገነኖች ሥርዓት አዙሪት ተላቃ የሁሉም ዜጎች እኩልነት ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች የተረጋገጡባት እሱም የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የዘላቂ ሰላም ባለቤት እንዲሆን በደምና በጥረቱ ይኸ ቀረው የማይባል መስዋዕትነት ከፍሏል እየከፈለም ይገኛል። ይሁን እንጅ የናፈቀው የታገለለት መስዋዕት የሆነበትና አይከፍሉ ፍዳ የከፈለበትና እየከፈለበት ላለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለተጠማው አስተማማኝ ሰላም ባለቤት ለመሆን አልታደለም። ዓለምን ያስደነቀ አኩሪ የሕዝብ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጂም ጊዜ ታሪኩ በምርጫ ካርድ አማካይነት እውነተኛ ፍላጎቱን ያስተጋባበትና ለለውጥ ያለውን ዝግጁነት ያስመሰከረበት አመፅን ኮንኖ ሽብርን አውግዞ ሰላማዊ ትግልን ስልቱ አድርጎ በመንቀሳቀስ በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን እንዲቻል ያረጋገጠበት መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ የታየበት ፍላጎቱና ውሳኔውን በማያሻማ ሁኔታ የገለጸበት ታሪካዊ ክንዋኔ ነበር። ያን የመሰለ ሕዝባችንን እውነተኛ የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ የሚያስችልና ሁሉም ተጠቃሚና አትራፊ ለሚሆንበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሰረት የሚጥል የሕዝቡን ሰላማዊ ተጋድሎ ለፍሬ እንዳይበቃ በገዥው ፓርቲ ቁንጮዎች ሴራ በአጭሩ እንዲቀጭ መደረጉ በቁጭት የሚታወስ ጉዳይ ነው። የሕዝብ ድምፅ ቢከበር ተጠቃሚው በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈው ክፍል ብቻ ሳይሆን በገዥው ፓርቲ ወገን ያለውንና በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ቀጣይ ትውልዶች ሁሉ ይሆን እንደነበር ገዥዎች ሊታያቸው አልቻለም። ተስፋ የተጣለበትና በጉጉት የተጠበቀው የሕዝብ ድል ተቀልብሶ መልካም ጅማሮ ፈር ስቶ አገሪቱን እየከፋ ወደሚሄድ አጠቃላይ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች እንድታመራ እየተገፋች ትገኛለች። ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ አሁን የሚከተለው አሠራር ካልተገታ ለዴሞክራሲ ሂደት ግንባታ ፀር ከመሆኑም ሌላ በየጊዜው እየከፋና ይበልጥ እየተወሳሰበ የመጣውን የአገራችን ሁኔታ በከፋ መልኩ እንዲባባስና ሕዝባችንን ለበለጠ አደጋ እንዲጋለጥ ያደርጋል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ። በዚህ የጥፋት ጉዞ መቀጠሉ በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን ሌላ ለገዥዎችም እንደማይጠቅም ከቶውንም ሊረዱት የቻሉ አይመስልም። ታሪክና የጊዜው አጋጣሚ አመች ሁኔታና ዕድል ባለመጠቀም ታሪክ ይቅር የማይለው ብሔራዊ ስህተት በመፈፀም ለሰፈነው የፖለቲካ ቀውስ ገዥው ፓርቲ ታላቁን ድርሻ አበርክቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢሕአዴግ በብቸኝነት በሚያዘጋጀው ምርጫ ሂደትም ሆነ ውጤት እንዲሁም በምርጫ ቦርዱ ምንም ብዥታና አመኔታ እንዴለለው የታወቀ ነው። ኢሕአዴግ ሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶችን በልዩ ልዩ መልክ አስፈራርቶና አግልሎ አባሎቻቸውን አዋክቦ እንደ መንግስት የፖለቲካ ስርዓቱን ጡንቻና መዋቅሩን እንደ ፓርቲ ደግሞ ልምዱንና ካድሬዎቹን ተጠቅሞ እንደተለመደው ካለ ሁነኛ ተቀናቃኝ ሙሉ በሙሉ አሸንፎ ይዞታውን እራሱ ለራሱ አረጋግጦ የሚያልፍበት እንደሆነ ግልፅ ነው። የዴሞክራሲ ሥርዓት ሕዝብ ነፃና ፍትኃዊ በሆነ ምርጫ መሪዎቹን የሚመርጥበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚለውጥበት በፖለቲካ ሥርዓቱ ሂደትና እንቅስቃሴ በነፃነት የሚሳተፍበት መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቱ የሚጠበቅበት የሕግ የየበላይነት የሚረጋገጥበት ግልፅነትና ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ የሕዝብ ሥርዓት ነው። አስራሰባት ዓመታት በሥልጣን ላይ ከመቆየት በኋላም እንኳን በተለመደው የጥሬ ጉልበት ጎዳና መቀጠላቸው የሚያሳዝን ነው። በሕዝብ ዩንታ የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮችም የተመረጡበት አካል ለግል የሥራ ዋስትና ማረጋገጫና የመታያ ቦታ ሳይሆን በነፃነትና ካለአንዳች ተጽዕኖ አሳባቸውን የሚያንሸራሽሩበት የሕዝብን ችግርና የአገርን ጉዳዮች ኃላፊነት በተላበሰ መንፈስ ወይይትና ክርክሮች የሚደረጉበት እያደጉና እየሰፉ የሚሄዱበት ሁኔታ የሚመቻችበት የሕዝብ ሥልጣን በውክልና የሚታይበትና ከፍተኛ ኃላፊነት ማዕከል እንጂ ከሕዝብ ጋር እልህና ትንቅንቅ የሚገባበት ተቃዋሚ እንደ ጠላት የሚታበትና በሰጠው አስተያየት የሚወገዝበት ወደ ጠርዝ የሚገፋበትና አገር ነክ የሆኑ ጉዳዮች እንደ አልባሌ የሚታዩበት የቀልድ መድረክ አይደለም።

ገነት ጌታነህ(Würzburg)

## Melese Zenawi & TPLF

As you are aware the rift between yours government & the Ethiopian peoples is widening and the speed of that separation is gaining momentum as that happens resistance to the status will.

Emerge with greater strength and vigour despite your keen ability to discern an impending crisis I would Suggest that the way out of this crisis will easily elude you as it is so contradictory to whom you really are That it may not seem like a choice at all Instead as it is likely that you will only Intensify that use of Oppression and force to control the people you my not fully comprehend how you are creating a moister Which will evenly ally

turn around and destroy you? Your approach Instead of controlling the resistance of The People is actually increasingly unifying the people against you in their struggle towards freedom democracy the rule of law it is only a matter of time before the succeed you Victory to people.

Leila Abdula Ibrahim

## Lesson in Repression

Violation of Academic Freedom in Ethiopia being educates can be a risky business in Ethiopia Students and teachers often among the Most politically active elements of society are Frequent victims of human right violations Including extra judicial killing arbitrary arrest And denial of Freedom of association and Expression Ethiopian leaders since Hailesilasse Have targeted the academic community the Current government continuation of such abusive Practices emphasizes the serious obstacles facing Ethiopia before basic rights are respected and Enforced not only on university campuses but Across the country this report focuses on three Major abuses respected unjustified use of lethal Force by security force to put down political Protest by students continued repression of the Independent Ethiopia Teacher Association Whose members include many of Ethiopia most Distinguishes Professor and stifling of Independent thought through denial of university Autonomy and government control of Ethiopia the ruling party of which has is roots in a student Movement has repeatedly.

Kadir Hussen (Zurich Schweiz)

## የግል ፕሬሶች በኢትዮጵያ ጨርሶ መታገድ እስከመቼ?

በጠመንጃ አፈሙዝ ስልጣን ተቆናጠ ያለው የወያኔ መንግስት ለአስራ ስምንት ዓመታት ስልጣን ላይ በቆየበት ዘመናት ለህዝቡ ይሄ ነው የተባለ የለውጥ ውጤት ሳያመጣ በስሩ ያሉትን ጥቂት የማይባሉ የወያኔ አገልጋዮችን ብቻ በግለሠብ ደረጃ እየጠቀመና በህዝብ ሀብትና ሀብትና ገንዘብ የግል ኑሮአቸውን እያደራጁ እዳሉ ለህዝበ ድብቅ አይደለም።

ይህን በወያኔ መንግስት ቅጥር አባላቶች የሚደረገውን በህዝብ ስልጣን፣ ድምፅ፣ ሀብት መጠቀሙን ለህዝብ ጆሮ እንዲደርስ ክፍተኛ ትግል ከሚያደርጉት አካላት በዋነኝነት የነፃው ፕረስ።

በአገራችን በ1997 ዓ.ም. በነበረው ህዝባዊ ምርጫ በተለይም በዋና ከተማችን አዲስአበባ እንዲሁም የአገራችን ዋና ዋና ከተሞች በሚባሉት ቦታ ሊደገረግ የታቀደውን የምርጫ አፈናና ማጭበርበር በማጋለጥ አኩሪ የሆነ ተጋድሎ ማድረጉ የማይረሳ የትግል ውጤት ነበር።

በዚህም አኩሪ የውጤት ስራው የነፃው ፕረስ እጅግ ውጤታማ በመሆኑ በወያኔ መንግስት ጥርስ ውስጥ መግባቱ በጣም ግልፅ ነበር። ስለዚህም የግል ጋዜጦችን ከማገድ ጀምሮ የአሳታሚ ድርጅቶችን እስከመዘጋትና የግል ጋዜጣ አሳታሚ ባለቤቶችን ማሰሩ አይዘነጋም።

ይህ በእንዲህ እያለ በአገራችን ላይ 2000 ዓ.ም ላይ በተደረገው የማሟያ ምርጫ ዳግመኛ የመጋለጥ ሁኔታ እንዳይገጥመው ገና ምርጫው ከመጀመሩ በፊት ከእስር የተረፉት እጅግ በጣም ጥቂት የተባሉትን የፕረስ ድርጅቶችን ጨርሶ በመዝጋት የስልጣን ወንበሩን ያለምንም ተቀናቃኝ እንዲፈናጠጥበት ያስቻለው ሲሆን ሊወዳደሩት አብረውት የቀረቡትን የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ምርጫው ከመጀመሩ በፊት ተስፋ ያስቆረጠና የማሟያ ምርጫውን ጥለው እንዲወጡ ያስገደደ ነበር።

በአጠቃላይ ያደጉት አገሮችን ትተን በአህጉራችን በአፍሪካ እንኳን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እያደገበት ባለበት ሰዓት እድገቷን ሁልጊዜ ለምንናፍቀው አገራችን ግን የፕሬስ ነፃነትን እንኳን ለማግኘት ያልታደለች አገር ሆናለች። ገዥው የወያኔ መንግስትም ጠዋት ማታ እሱን የሚያወድሱትን በስሩ የሚንቀሳቀሱትን የኢንፎርሜሽን ድርጅቶችን ይዞ የአገዛዝ ዘመኑ ቀጥሏል።

ይህንን የአገዛዙን ቀንበር ለመጣል ሁላችንም ተደራጅተን መታገል አለብን።

ኤልዳ ኃይሉ( ከብሬካ ፊልድ)

# ታሪከ ኢሕአፓ በጥቂቱ

ሀገሩ ኢትዮጵያን ለማማሻሻል ከገባችበት የመከራ፣ የሰቆቃና የችግር ታሪክ ለማውጣት አስቸጋሪ የሆነና መራራ፣ ሀሞትን የሚጠይቅ ትግልን የጀመረ የኢትዮጵያዊያን ስብስብ ፓርቲ ኢሕአፓ። የዚህ አንጋፋ ፓርቲ አባላት ከ1940ዎቹ አመታት ጀምሮ የተገኙ ፍሬዎች ሲሆን ሁሉም በቅን መንፈስ ለበጎ አላማና ግብ የተሰባበቡ በዘመናችን እጅግ፣ብሩህ አዕምሮ የነበራቸው አርቆ አሳቢና ለወገን ተቆርቋሪ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ።ናቸውም። ብዙዎቹ አባላት ዘመናዊ ትምህርትን ለማግኘት ከታደሉት ጥቂት ወጣቶች መካከል ሲሆኑ አብዛሀኞቹ በቀለም ትምህርታቸው የላቁ ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉት የተሰማሩባቸው የትምህርት ተቋሞች ድንቅና ምስጉን ተብለው በአርአያነታቸው ይጠቀሱ የነበሩ ናቸው።ስለ ሕዝቡ ዋይታና ጉስቅልና እንዲሁም የገዢው ክፍል ቁንጮ አባላት ስግብግብነት፣ቆርቁዞ በቀረው የአገሪቱ ኢኮኖሚና ባጠላበት የፖለቲካ ፍትህ አልባነት ከዛሬ የነገው ተስፋ ስለተሚጠጠበት ሀገር ሁኔታ የሚቆጠቁጣቸው ትውልዶች ነበሩ። መሸቆጥቆጥና ታማኝነት ብቻ የዜጎች ግዴታ አድርገው ሊወስዱት ያልቻሉና አለቅጥ ከተንሰራፋው ፊውዳላዊ ሥርዓት ጋር እምቢኝ ያለ ትውልድ በገዛ ራሱ ባሕርይ ለመተማመን እንዲችል የራሱ የሆነ መለዮ ይኖረው ዘንድ በራሱ ባህል ላይ አምፆ መነሳትና ከተገዥነት ማምለጥ ነበረበት፣ ስለሆነም ለስርዓቱ አልገዛም ብሎ ሕሊናው የመከረውን ሁሉ እያደረገ የወደፊት ጉዞውን ጀመረ።

ትውልዱ ከአማራው፣ ከትግሬው፣ ከኦሮሞው፣ ከጉራጌው ከሌሎችም የሀገሪቱ ብሔረሰቦች የተውጣጣ ሲሆን ከሚጋሩት የፖለቲካ ዕምነትና ለሐገራቸው ከነበራቸው የመቆርቆር ስሜት የተነሳ ስብስቡ እጅ ለእጅ የተያያዙ ሕብረብሔራዊና ሕብረ-ልሳን ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ ነበር። የዚህ ትውልድ (ፓርቲ)ግንባር ቀደም አባላት በቅን ፍላጎት ተነስተው ነበር ከባቢያቸውንና ሀገራቸውን ለመለወይ የመጀመርያ ተቃውሚቸውን የተነፈሱት። በ1960ኛዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ውስጥ ከሌሎች የህይወት ምርጫዎች ይልቅ የሀገሩን ጉዳይ ቅድሚያ በመስጠት ነበር ጭንቅና መከራ ታልፎ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ) ሊያቆጠቁጥ የበቃው። ኢሕአፓ ብዙ ተከታዮቹን አሰልፎ በተለይም ወታደራዊው መንግስት ስልጣን ከያዘ በኋላ በተካሄዱ የፖለቲካ ክንዋኔዎች ላይ ጉልህ ሚና ተጫውቷል። ለዚህ ነው ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ የሆነ ሥፍራ ያለው። ያነሳቸው የፖቲካና የኢኮኖሚ ጉዳዮች የሕዝብ ነፃነት፣ ዜጎች በሀገራቸው ላይ በነፃነት የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመቃወም፣ የብሔረሰቦች መብት መከበር፣ የሀገር ነፃነት(ሉአላዊነት)፣ የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የታገለና እየታገለም ያለ ፓርቲ ነው። ብዙዎቹ ጥያቄዎች ምላሽ ያላገኙና ዛሬም ቢሆን ምላሽን የሚሹ ጥያቄዎች ናቸው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ይሏል በዘመኑ የወደቁና ታላቅ ተጋድሎአቸው ታሪካቸውን ለቀሪው ትውልድ ጽፈው ያለፉትን ጀግኖች ፈር መያዙን ይረዱአል።

አሁንም ቢሆን ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ አንድ ሆኖና ተሰባስቦ ለዘመናት የ ኢትዮጵያ ልጆች የታገሉለትን አላማ ከዳር ማድረሱ የዚህ ዘመን ፍሬዎች ለሆነው ሞራላዊና አገራዊ ግዴታ ነው። መልኩን እለዋወጠ ከሚመጣው ጉልቻ የማይጣፍጥ ወጥ ከመብላት በአንድነት ተሰባስቦ ትላንት የነበረችውና ዛሬም ያለችውን ወደፊትም ለምትኖረው ኢትዮጵያ የተከፈለላትን መስዋዕትነት ማስታወስና ከእኔ ምን? ብሎ መጠየቅን ማሰብንና ወስኖ ወደ ትግሉ ኢሕአፓ ጋር መቀላቀልን ይደር የማይባል አጣዳፊ የሀገር ጉዳይ ነው። **ከታሪክ ተጠያቂነት የሚያመልጥ የለምና!!**

ዳዊት ሚካኤል(ሂነፍ)

## ***Woyane is responsible*** (Tsige Bekele)

Woyane has been blamed of intentionally undervaluing the level of deadly drought facing millions of its people, some of whom are being denied of emergency food aid by the country’s military. The humanitarian crisis, caused by three years of unsuccessful rains, currently influences about 4,6 million people, though the official number could jump to high as 6,7 million this week. United Nations agencies say that the real number at risk 8 million, an estimate disputed hotly by Addis Ababa, which is insisting on publishing a much lower figure.

According to my sources in Addis Ababa, the figure has risen very substantially, maybe even doubled.

The crisis is at its most worrying in the vast deserts of the Ogaden region, where the UN’s World Food Programm (WFP) in reports a confidential alert to donors that it is receiving increasing reports of hunger-related morality. About two million people are at risk until the main rains fall next spring if they at all. The people around Ogaden region accused that they have nothing to eat and that the only people who receive food are the military forces. According to the reports the UN has raised about 60 per

cent of $325 million it seeking in emergency relief for Ethiopia and says that it is suffering the shortfall of about 300,000 tones of aid.

The WEP has told donors that it blames Ethiopia's delays in recognizing the extent of call causing the rapid depletion of existing food stocks. Herdsmen in villages almost completely cut of from the outside world said that many of their animals had been killed by Woyane soldiers, who also deprived them of water. The Un says that it has negotiated with the Ethiopian army for the military's role in food distribution to be kept to a minimum. As an Ethiopian citizen I find it too shameful, to hide the well known Hunger and let the people die. Every body has a responsibility to face the truth and fight against hunger in our beloved country.

---

## Had I been the Jury……….. (Mikiay Taddesse Sayoum)

I swear to give a true verdict for the following five crimes of Melese Zenawi and his Messengers.

**1. Human rights infringement**

A. The Meles-Led Ethiopian military has committed the following crimes against the Anuak population in remote southwestern region of Gambella since 2003.

- Widespread murder: government soldiers murdered more than one hundred Anuak civilians in these assaults
- Rap: woman on their way to fetch water and gather firwood, and have invaded homes and raped the innocent woman living there.
- Burned several villages: looted homes as well as cattle and other livestock when they pass through Anuak villa

B. In the Ogaden region, Melese has committed war crimes, burning homes and property, and firing upon and killing fleeing civilians

C. Did not take sole responsibility of shameful killing and frightening of innocent civilians during the instability created after the 1997 National Election

D. viciousness against the academic establishment in January of 1993

- Melese ordered his police to gun down and injure hundreds of Addis Ababa University students for serenely exercicsing their freedom of expression

E. the present immurement of Artist Tewodros Kasshun (a.k.a Teddy afro) on unreal accusations

**2. Thievery**

Since he took his power for granted, Meles has used economic deficiency as tool of subjugation, and has subjected the vast majority of the people to immense misery. No dictator in history has unashamedly and successfully utilized mass starvation for the purpose of propagating authoritarian rule to the same degree as Meles has done so

A. Stealing people's money by the name of tax and corrupting it.

B. Stealing the money found from donators that are much concerned than the citizens and saving it in banks of Europe and USA.

**3. Exclusive control of the most respected Judical system**

A. Not practicing the rule of law!

B. assigning judges who are not chosen the people

**4. Press Freedom**

Journalists in the country have been arrested in numbers and charged with disloyalty, and some say that Ethiopia now ranks among the world's leading jailers journalists since government onslaughts in November 2005, with many private newspapers now forbidden from publishing, and a wanted list for more journalists.

**5. Invasion**

A. Killing and injuring innocent Somalia citizens and people

B. Invading the country Somalia

## Art. 39 #1 Governor of Ethiopia

During this time in our world, leaders of the countries work day & night & also they are always in stressed that how they can manage their people & develop their countries.

At the time when they are going to take their position they have to pass the difficulties which create the way to the point & also they have togive the answer what & how they can resist if they are going to be attcked ba the problems during the governing period of their countries.
It might be a good & real examples if we look at USA, South Africa countries & so on which is happend now. But for our countries it happenes the oppsite. That is the articles & rules are always created which is used toget rid the country instead of trying to develop it.

That is one of the constitution Art. 39 which designed by Woyane memmbers is used as implement for the government to the isolation of Ethiopian territory into minority & then to make disappeared from the world.
The main purpose of Art.39 as we know, was not to develop the nationalities, socilaly & economically, but also to be used the cover to isolate in to divisions nationalities. The article hence the language & ethinic based divisions of the country excite &motivated radical conflict against minorities on trumped upcharges.

One of the concrete examples is the latest conflict between Oromo & Conso, Oro mo & Gumuz ( EHRCO. Pg. 13-21). When we are going to screen out the idea for the dominant nationality, it is absolutely important that the minorities in Ethiopia to be well protected, from being trampled upon by the major ethinic groups be it Oromo or Amhara. In these conflict 145 human being lives were lost, approximately 43 people were harmfully injured, 20teachers were displaced from their villges & job areas, 22 houses were burned, 42 students quite their school. Accordingly the report more ethinic classes were reported in this calander year than any other time. Does Meles Zenawi & his Woyane group have care about this ethinic conflicts? Clearla not, particularly Mele Zenawi doesn‘t care about it, Because it is his main dream until now. He always says to his false parlament that it is not my business it is the implementation of Art. # „39“ which is one fo constition of country.

Therefor when we look at it, it is main enemy designed by Meles Zenaei to full fill his dream.
And **also truely Art. # 39 is the main leader of the country along with the consiquence to get rid of Ethiopia and ist Nationality from the world**.

Saron Mesfin( Würzburg)

# ታሪኩን የረሳ ቅርሱን የዘነጋ የሞተለትንም ያልሰጠው ምስጋና ጠላት ይገዛዋል ባሪያ አርጎ ቀጥቅጦ ማን ሊያዝንለት ይሆን እሱ ራሱን ጥሎ?

## *ከገፅ 17 የቀጠለ*.... የመጨረሻው ሰይጣን

*የአባቴ ጫካ መኖር የሚቾቹን ዘመዶች ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ሰው ሁሉ በጣም ሰላሰጨነቃቸውና አባቴም በበኩሉ በየሽማግሌዎቹ ቤት በሌሊት እየሄደ እንዲያስታርቁት ስለጠየቀ የአካባቢው ሽማግሌዎች ተሰብስበው ወደ ሚቾች ቤተሰቦች ሄደው ሽምግልና ተቀመጡ ። የታወቁት ሽማግሌ እንዲህ ብለው ተናገሩ ።*

*„ዘመዶቹ ወገኖቼ ያገሬ ሰዎች፡ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አሮጌው በሃል በአዲሱ እየተተካ ባለፈው የተሰራው ሰህተት የተከታዪን ትወልድ ኑሮ ሳያዛቡ ለሚቀጥለው ትውልድ የተሰፋ ብርሃን እየሰጠነው ልናልፍ ይገባል“።*

*„የቆየ ቂም በማስታወስ መገዳደል ደም ሳልመልስ ብሎ ማለቂያ ለሌለው የእርስ በርስ ትልልቅ መዘጋጀት ጊዜው ያለፈበት ተግባር ሊሆን ይገባል። የተሰራው ጥፋት ተሰርቶአል። የፈሰሰን ውሃ መመለስ አይቻልም ።ጥፋትን በጥፋት መመለስ ደግሞ ምንም ጥሩ ውጤት አያመጣም“።*

*„በፍቅር ተነድፎ በሰይጣን ፈረስ ተሳፍሮ ለኛም ለቂያችንም የሚያሳፍር ተግባር መፈፀሙ ሁላችንም እናውቀዋለን፡፡የነገሩን ክብደት ለማጣጣል አይደለም ። የተሰራው ስራ ግን ቂያችንን ሰፈራችንን ከዘር ዘር እየተላለፈ በፍቅር የተሳሰረውን ኑሮአችንን እያደፈረሰው እስከ መቼ እንኖራለን በማለት ነው“።*

*„ነገር ግን እድሜ በሰጠን ፀጋ ሁኔታውን በደንብ ስናስበው ገና ጨቅላ የሆኑትን ልጆቻችንን በቂም አርግዘን በቂም ወልደን ቂም አስተምረን እኛ ያወረስናቸውን ቂም ተከትለው እርስ በርሳቸው እየተፋጁ እንዲኖሩ የሚያደርግ ስለሆነ አስበን መክረን ነገሩን ካጠናንው በኋላ ይህንን ሁኔታ ልንቋጨው ይገባል ብለን እናንተ ጋር መጥተናል። የእድሜያችን መግፋት እናንተም ተመልክታችሁ ጉልበታችን ሳይሆን አስተሳሰባችን አስባችሁ እንቢ እንደማትሉን በማመን ነው„። ብለው ጨረሱ፡፡*

*ከሚች ወገን ደግሞ ሽምገል ያሉት ተነስተው ። ደካማነታችንን አይቶ ደማችንን የሚመልስ የለም ብሎ የጥጋብ ፈረስ እየጋለባ መጥቶ ሕፃናቶቹን አለአባት ፣ ሴቶቹን አለ ባል ፣ እኛን አለመጠጊያ ላስቀረን እብድ ጋር ነው ታረቁ የምትሉን ። ባንታረቀውስ እንደፈለገ እይዘረፈ እየደበደበ እየቀማ መኖር ማን ከለከለውና ነው ።*

*ሌላኛው ሽማግሌ በተራቸው።ማሰብ ያለብን ለልጆቻችንን ምንድነው የምናስተምረው፣ ምንስ ነው የምናወርሰው ብለን ነው ። ቂም፣ መከራ፣ ችግርና ደም የምናወርሳቸው ከሆነ የኛ መሰቃየት አንሶን እነርሱንም ለዚህ መጥፎ ባህል የምንዳርጋቸው ከሆነ፤ እየጣሉን እየተሰደዱ አለጧሪ አለቀባሪ ነው የምንቀር ። እነርሱ እኛን ያጋደለንን ጉዳይ እንደሞኝ ተግባር ነው የሚቆጥሩት ። ይክፋም ይልማም እቡይ ተግባርን ማቆም ደግሞ የታላቅ ሰውነት ምልክት ነው እንጂ የደካማነት መች ሆነና ።*

*የሚች ቤተሰቦች ከነገ ዛሬ በተኛንበት አቃጠለን፣ ሳናስበው ፈጀን ብለው በሰቀቀን መኖሩ ስለሰለቻቸው፣በዚያም ላይ የደረሰ የሚከላከልላቸው ልጅ ባለመኖሩ የሽማግሌዎቹን አሳብ ብዙም አልተቃወሙትም ነበር። አባቴ የደም ካሳ ከፍሎ ተታርቆ እንዲገባ ተደረገ ። ያለውን ንብርት ሁሉ ሸጦ ካሳውን ከፈለ ። አዲስ አበባ ያለው ወንድሙ ባይረዳው ኖሮ ከፍሎም አይጨርሰውም ነበር ።*

*እናቴ አባቴ አባትዋን ከገደለበት ጊዜ ጀምሮ እንኳን የሚያገባት የሚያነጋግራትም አልነበረም ። ሁሉም አባቴን በመፍራት ከናቴ ይርቁ ነበር ። አባቴ ታርቆ ሲገባ የቆየ ፍቅሩዋ አገርሽቶባት አበቴን ለማየት ጓጓች ። ድሮ ወደሚገናኙበት ምንጭ ማዘውተር ጀመረች ። አባቴም በበኩሉ እናቴን ማግኘት ቢፈልግም እናቴ አባቷን ስለገደለ ይቅርታ እንደማታደርግለት ስላሰበ ብቻ እናቴን ከማግኘት ተቆጥቦ ሲቀመጥ ፤ አንድ ቀን እቤተክርስትያን ውስጥ በሩቅ ያያታል ። እናቴም በአይኑ እንደሚከታተላት አውቃ እያሾለከች ስትመለከተው ቆይታ አጋጣሚ አግኝታ ፈገግ ትልለታለች። በበነጋታው አባቴ ወደ ምንጩ ሄዶ እናቴን ይጠብቃታል ። እሶም ቀጠሮ እንዳለው ሰው በሰአቱ ትመጣለች ። አባቴም ሌላ ሰው ሳያየው በጨለማ የሚገናኙበትን ቦታ ነግሮአት ይሄዳል ።*

*ለመጀመሪያ የተገናኙት በአንድ የአባቴ ዘመድ ቤት ውስጥ ነበር ። እናቴ ለበዙ ጊዜ ታስበው የነበረውን ለመጠየቅ በመጓጓት ፣ ምነው እንጥፋ ብትለኝ ያኔ?ምነው ብትጠልፈኝ ኖሮ? ምነው? ምነው? ብላ ስቅ ብላ አለቀሰች።*

አባቴም ይህን ያህል የምትወደው አይመስለውም ነበር ። በዛ በሻካራ እጁ ፊቱዋን እየጠረገ፣መቼስ ፍቅርሽ ነድፎኝ የማደርገው አጥቼ፣በህልሜም በውኔም እየመጣሽ ስታሰቀይኝ፣በክብር ብጠይቃቸው አዋረዱኝ ። ምን ላደርገው ብለሽ ነው ። አንቺን ከማጣት እራሴው ብጠፋ ብዬ አደረግሁት እንጂ መቼስ የደም ጥማት የለኝ አላት ። እትያው ገብታ ሙቀቱን እየወሰደች እሷም ሙቀትዋን እየሰጠችው በጣም እየተጠጋጉ መጡ። በዚያውም እኔ ተረገዝኩ ። ሽማግሌ መላክ የማይቻል ሆነ ።ቀኑ እየገፋ ከመምጣቱ በፊት አባቴ እናቴን በስምምነት ተነጋግረው ውሃ ለመቀዳት ሰትወርድ ጠለፉት ።

አባቴ እያረጀ ሲሄድ የሚቾች ልጆች እየጎረመሱ ነፍስ እያወቁ መጡ። ወሬ አይደበቅም ሰለ አባታቸው አሟሟት ሰሙ።ሁል ጊዜ አባቴን ሲያዩ ጥርሳቸውን መንከሳቸውን ቀጠሉ ።አንድ ቀን አባቴ ገበያ ውሎ ሲመጣ ወደ ምሽት ላይ የአባቴ ጠላቶች ጠብቀው በአረጀ ጊዜ ሊገሉት መጡ። ከከተማ እኛ ወዳለንበት ለመምጣት ብዙ የሚያስኬድ ባይሆንም አንድ አነሰተኛ ወንዝና ትንሽ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ማቆረጥ ነበረበት። አበቴን እዛ ወንዝ ወስጥ ጠብቀው ቀጠቀጡት ደበደቡት።ነፍሱ እያለ ምላሱን ቆረጡት ። ብልቱን ሰልበው አጠገቡ በሚገኝ ዛፍ ላይ አንጠለጠሉት። ገድለነዋል ብለው ጥለውት ሄዱ ። እኔና እንጀራ እናቴ ሲያመሽ ጊዜ ልንፈልገው ሄድን ። እመሬት ወድቆ በደም ተውጦ ደረስን ።ሁኔታውን ሳስበው ሁል ጊዜ ይታወሰኛል፡፡እስከ ዛሬ ድረስ በህልሜም በውኔም ይመጣል። ስለሱ ሳስብ የሰው ፍጡር ያስጠላኛል።

አባቴን በርበሬ ከአጠነኝ በሆላ በጣም ባልወደውም እንደዛ ሆኖ ሳየው እንባና እልክ አነቀኝ ። አባቴ ሁል ግዜ መጥፎ አልነበረም ። አንዳንዴ ከእሱ በአልጠበቅሁት ሁኔታ ደካማዎችን ይረዳል ። ከእርሱ ላነሱ ይመፀውታል። እንጀራ እናቴ እኔን ጫካ ወስጥ ተደብቄ እንድጠብቃት አድርጋ አንዳንድ የአባቴን ዘመዶች ለመጥራት ሄደች ። የአባቴም ዘመዶች መጥተው ሰው እንዲህ ሆኖ አያየውም ብለው አባቴን በጨርቅ ጠቅለው ወደ ቤት ከአገቡት በሆላ ሊነጋጋ ሲል አረፈ። እንጀራ እናቴም መጮህ ጀመረች ። ጎረቤትም ተሰበሰበ። በዛው ቀን እንዲቀበር ተወሰኖ አባቴ ተቀበረ። እቀብሩ ላይ የአባቴን ሱሪ አሲዘውኝ ሳለቅስ ዋልኩ ።በቀኑ ሙሾ አውራጅ እንዲህ አለች ፡፡

ጋብቻ ቢጠይቅ አባት እንቢ ቢለው
የተጠጋው ጋኔል ግደል ግደል ሲለው
ሰውሮበት ኖሮ ደም መላሽ እንዳለው
አባቷን በጥይት ገድሎ አሳረፈው ።

የአገር አጉራ ዘለል የሰፈር ወንበዴ
አግብቶ አሳያቸው ልጅቱን በዘዴ
ወልደው ከብደው ሳለ ሞቆ ትዳራቸው
ደሙ ፀዳ ብለው በመዋለዳቸው።
አማቹ ይገለኛል ብሎም አልጠበቀ
የሚች ልጅ አደገ ቂም እንደጠበቀ ።
ደም በደም ነውና ወትሮም የሚፀዳው
ልጅየው በተራው አማቹን ገደለው
ደም ይበቀል ይሆን የሚች ልጅ በተራ?

ገዳዩ አንተ፡ የሞተው አባቱ
አንተን ቢገድለው ምን አለው እንጀቱ
ለመከራ የጣፈው የጠዋት እድሉ
ሃዘኑ ቅጥ አጣ አለወጣም ከልቡ ።

የአካባቢው ሰው የአባቴን ገዳዮች ለመያዝ ምንም ጥረት እንደማያደርጉ የታወቀ ነበር። መቼስ የገጠር ሰው ከባለወቅት ጋር መጣላት አይወድም። ቢጣላስ ለማን ብሎ? ለየትኛው የአባቴ ጥሩ ስራ ተብሎ ነው ደምስ የሚቃባው፡፡ቀብሩ አልፎ ሰልስቱ ከወጣ በኋላ ዘመድ ተሰበስቦ እንግዲህ እዚህ አገር መኖር አትችልም የአባትህ ጠላቶች አንተንም አይለቁህም ። ስለዚህ ከዚህ መሰወር አለበህ አሉኝ ። እኔም ከአባቴ ወንድም ጋር በመሆን ጉዞዬን ወደ አዲስ አበባ ቀጠልኩ።

……………………….ይቀጥላል።

# ጳውሎስ ኞኞ
# 1926 ---1984 ዓ.ም.

## ሀገር ማለት ምንድን ነው?

ግዑዝ መሬት፣ አፈሩ፣ ወንዙ፣ ተራራው፣ አየሩ ወዘተ ምርምርን፣ አድናቆትን ቅላጼንና ትርጉም ከመስጠቱ በፊት ሀገር ማለት ምን ማለት ነው?
ሀገር ማለት ሕዝብ ሕዝብ !
ሕዝብ ደግሞ ያፈራል ሰውን። ሰውም እንደ ፍጡርነቱ ሕዝብ አፍርቶታልና ሃገር ሃገር ማለት ካልቻለ መፈጠሩን ረስቶ የጭካኔ ጥርሱን ያሾለው መልአከ ሞት መጥቶ እስኪወስዳቸው እናይና ከተወሰዱ በኋላ እሮሮ እናሰማለን።

## ልጅነት

የጳውሎስ የልጅነት ስሙ አማረ ነበር። ለእናቱ አንድ ነው። እናቱ ወ/ሮ ትበልጫለሽ አንዳርጌም ለልጃቸው አንድ ናቸው። አማረ ግና የሁለት አመት ህፃን ሳለ እናቱ ከባላቸው ስለተፋቱ በተዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ ይዘወት እየዞሩ ነበር ያሳደጉት።እሱም ሲያሳድግ ውለታውን መለሰ። በሄደበት ሁሉ እናቱን አስከትሎ፣ በኖረበት ሁሉ እናቱን አብሮ አኑሮ፣ በህይወት ፍፃሜ ወደ መቃብር ሲወርድም ከሀያ አንድ ዓመት በፊት የሞቱት የእናቱ አፅም ተገልኅ አጥንታቸው ከጎኑ እንዲያርፍ ተደርጓል።

የአባትን ምንነት ሳያውቅ፣ ቋሚ የገቢ ምንጭ በሌላት እናት እጅ ማደግ ዕጣ ክፍሉ የሆነው ጳውሎስ የተወለደው ቁልቢ አካባቢ ህዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም. ነበር፡ ልጅ አጥተው በስለት እንደወለዱት እናትዬው ተናግረዋል።ልጁም የእናቱ ችግር በጊዜው ገብቶት ብልህ፣ አዛኝና፣ ኑሮ የማሸነፊያ መንገ ችን ቀያሽ ሆኖ አድጓል።

ጳውሎስ ትምህርቱን ከአራተኛ ክፍል ቢያቋርጥም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ አክስቱ ወ/ሮ በላይነሽ ቀጀላ የሚሰጡት አስተያየት አለ።

"እኛ ጳውሎስን ለማስተማር አላቀተንም። እንዲያውም አዲስ አበባ አምጥተን በጊዜው የሚኒስተር ልጆች የሚማሩበት " ላዛሪስት ሚሽን " የተባለ አዳሪ ት/ቤት አስገብተነው ነበር። ነገር ግን እናቱ አንድ ቦታ ስለማትቀመጥ ከትምህርት ቤቱ አስወጥታ ወደ ድሬደዋ ወስዳዋለች። እናቱ በጣም ስለምትሳሳለት ከአጠገቧ እንዲለይ አትፈልግም ነበር "ይላሉ።

እናት ደግሞ ልጅዋን ከጉያዋ የማትለቅበት ምክንያት ይኖራታል። የወ/ሮ ትበልጫለሽም ህይወት ልጃቸው ነበር። መፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ ስለሚወዱ አማረንም በልጅነቱ እያነበቡለትና እያስነበቡት ፍቅርና ዕውቀት ይዞ እንዲያድግ አደረጉት። መሰረተ ክርስቶስ ት/ቤት ገብቶ በመማሩም ለመፅሐፍ ቅዱስ ዕውቀቱና ለቋንቋ ችሎታው መዳበር መሠረት ሆኖታል። እናቱ ካደገ በኋላ ጳውሎስ የሚለውን ስም የሰጡትም ከመፅሐፍ ቅዱስ ወስደው ነበር።

ጳውሎስ በልጅነቱ የደስ ደስ ያለው ቀይ፣ደማም፣ ሉጫ ፀጉር ነበር።(ምን አልባትም "አማረ" የሚለውን ስም ያወጡለት በመልኩ ለመሰየም ይሆናል) አንድ ቄስ እነ ጳውሎስ ቤት በመጡ ቁጥር “ጣሊያን„ ማረድ የምንጀምረው ከዚህ ነው እያሉ በቀለሙ ተመሳሳይነት እየቀለዱ ያስፈራሩታል። ጳውሎስ ይጠላቸዋል። በሆዱም ቂም ይይዝባቸዋል። አንድ ቀን ቄሱ ሲመጡ ጠብቆ ቢላዋ ይይዝና እሳቸው እንደሚያደርጉት ሁሉ "ልረድ" ይላል፣ ቤተሰቦቹ የቢላውን ስለት አዙረው በደንደሱ በኩል ያሲዙትና ይለቁታል። ቄሱም አንገታቸውን ሰጥተውት የታረዱ በማስመሰል ሲጮኹለት ጳውሎስ ይደሰታል። ስብዕናውን የሚፈታተኑትን መፋለም የጀመረው ያኔ ገና በልጅነቱ ነበር።

ከእናቱ ጋር ኑሮን ለማሸነፍ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ብልህና ብሩህ አዕምሮውን ያሳያል። ዕንቁላል እየቀቀለ ባቡር ላይና መንገድ ዳር

ይሸጥ ነበር። በዚህ የስራ መስክ ተጫራቹ ስለበዛ አንድ ዘዴ ፈለገ። የእንቁላሉን ሽፋን የተለያየ ቀለም በመቀባት እያሳመረ ማቅረብ ጀመረ። "ለየት ያለ ባለ ቀለም እንቁላል" በመሸጥ የገበያ ውድድሩ አሸናፊ ሆነ።

"ሸርቤቲ" የሚባል ለስላሳ መጠጥ ጳውሎስ ራሱ እየቀመመ ይሸጥ ነበር። በርካታ ሎሚዎች ገዝቶ በገረወይና ውሀ ውስጥ ከጨመቀ በኋላ በስኳርና በቀለም በጥብጦ በጠርሙስ አሽጎ ለገበያ ያውላል።ህዝቡ እየተሻማ ገዝቶ ይጠጣል። አሁንም ሌላ የንግድ ተቀናቃኝ ይመጣል። ጳውሎስ ደግሞ አቅጣጫውን ይቀይራል።

ጭራ እየሰራ በመሸጥ፣ ፓስቴ በመነገድና በመሳሰሉት የስራ መስኮች ኑሮውን ገፍቷል። ካደገም በኋላ የመላእክትን ምስል እየሳለ ሲሸጥ የተጠቀመው ዘዴ የሚረሳ አይደለም።

ጳውሎስና አቶ ታደሰ አበበ የታላቅና የታናሽ ልጆች ናቸው። ብዙውን የልጅነትና የወጣትነት ጊዜም አብረው አሳልፈዋል። ጳውሎስ የመላእክትን ስዕል በካርቦንና በተለያየ ቀለም ይስላል። አቶ ታደሰ በየጠጅቤቱ እየወሰደ ይሸጣል።

አንድ ችግር ተፈጠረ። ከስዕሎቹ ግርጌ የመላዕክቱን ስም ስለሚፃፍበት የገብርኤልን ምስል የሚፈልግ ሰው የሚካኤልን ወይም የአቦን አይገዛም። አንዳንዶቹ ስዕሎች ሳይሸጡ ይመለሱ ጀመር።

"ዛሬ ደሞ ያጋጠሙኝ ሰዎች የገብርኤልን ስዕል የሚፈልጉ ብቻ ናቸው" በማለት አቶ ታደሰ ያልተሸጡለትን ስዕሎች ይዞ እየተናደደ ይመለሳል።

ጳውሎስ አንድ ዘዴ ፈለገ። ተመሳሳይ የመላእክት ስዕሎች ሳለና ስማቸውን ሳይፅፍበት ሰጠው።

"ታዲያስ? ...." አለው ታደሰ።

"የሚገዙህን ሰዎች የሚፈልጉትን የመላእክት ስም እየጠየቅህ ፃፍበት አለው" ጳውሎስ።

አቶ ታደሰ ይኸኛው መንገድ የሚያዋጣ ሆኖ አገኘው። እንደገገርው ፍላጎት የመላእክቱን ስም ከግርጌ እየፃፈ፣ ተመሳሳዩን ስዕል በተለያየ ስም ቸበቸበው።

## የተልዕኮ ጥሪ

ስልጣኔ ብርሀኑን ባልረጨበት ዘመን ክትባት የወሰዱ ከብቶችን ካልተከተቡት ለመለየት ጆሮአቸው ይቆረጥ ነበር። ጳውሎስ በልጅነቱ ወደ ጅጅጋ ሄዶ በእርሻ ሚኒስቴር ውስጥ በወር ስምንት ብር ደመወዝ የተቀጠረው ይህንን ሥራ ለማከናወን ነበር። በኋላ በፅህፈት ሠራተኝነት ወደ ጤና ጥበቃ ተዛውሮ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ገባ። ደመወዙም ወደ ሰማኒያ ብር አደገለት። የሚያምር የእጅ ፅሁፍም ነበረው።

በዚህ ሥራው ላይ እያለ አንዳንድ ነገሮችን በመጫጫር ለጋዜጣ መላክ ጀመረ። እንደማንኛውም ወጣት ደግሞ አንዲት ልጃገረድ አፈቀረ። ዘመኑ ፍቅርን በይፋ የሚገልፁበት አልነበረም። ጳውሎስ አንድ ግጥም ፅፎ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይወጣለታል። ግጥሙ በሌላ ማህበራዊ ጉዳይ ላይ የተፃፈ ሲሆን፣ ቁልቁል የመጀመሪያዎቹ ፊደላት ሲነበቡ“ ፈለቀች ትወደኛለች፣ እኔም እወዳታለሁ„ የሚል ይሆናል። ፈለቀች ማለት ያፈቀራት ልጃገረድ ናት። ፍቅሩን በስውር መንገድ ገልፆ ጋዜጣውን ለጓደኞቹ ሲያሳያቸው ተደነቁ። በዚህ አይነት እጁን እያፍታታ ወደ ስነፅሁፍ ሙያ ብቅ ሲል የጋዜጠኛነት ዓለም ጠራው።

ያን ግዜ"አዲስ ዘመን" የመንግስት ልሳን ሲሆን "የኢትዮጵያ ድምፅ" ግን በሀገር ፍቅር ስር የምትተዳደር ሳምንታዊ ነፃ ጋዜጣ ነበረች። ጳውሎስ ሰማኒያ ብር የሚያገኝበትን ደመወዙን ትቶ በሀምሳ ብር ደመወዝ የድምፅ ጋዜጣ ሰራተኛ ሆነ። ችሎታውን የተመለከቱ ኃላፊዎችና ባለሥልጣኖች ወደፊት ዕውቅ ጋዜጠኛ እንደሚወጣው ተነበዩለት። ህይወቱ የመደበችለትን የተልዕኮ ጥሪ ገና በወጣትነቱ ተቀበለ።

የአጎቱ ልጅና የዕድሜ ጓደኛው አቶ ታደሰ አበበ እንደሚገልፀው ከሆነ፣ ጳውሎስ ጨዋታ ወዳድ የፍቅር ሰው ነበር ሙዚቃና ዳንስን በወጉ አልፎበታል። ደጃች ውቤ ሰፈር ደምቃ በምታቀልጥበት ዘመን የዳንስ ተዋናይ ሆነው አብረው አሳልፈዋል። ሙዚቃዋን ሞዝቀዋል። ህይወቷን ኖረዋል።ይሁን እንጂ ውቤ በረሃ እንደ ራሷ ቅልጠት ጳውሎስን አቅልጣ አላስቀረችውም። ይልቁንም "የ አራዳው ታደሰ፣ የጌታቸው ሚስቶች፣ የኔዎቹ ገረዶችና የመሳሰሉትን ፅሁፎች ፅፎባታል፣በብዕሩ ጠቅሷት አለፈ።" የህይወቱን ተልዕኮ የሚዘነጋ ሰው አልነበረም።

## የዝነኝነት መንደርደሪያ

በድምፅ ጋዜጣ አማካኝነት ጳውሎስ የብዕሩን ድምፅ አሰማ። ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ በታደለው የማስተባበርና፣ የመቀስቀስና የማቀናጀት ጥበብ ጋዜጣዋን በስፋት ለህዝብ አስተዋወቀ። የድምፅ ማጉያ ይዞ ሌሊቱን በከተማው በመዞር በበነጋታው ቢጋዜጣዋ

የሚወጡትን ፅሁፎች ሁሉ ያስተዋውቅና ይቀሰቅስ ነበር።"ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ሮኬት ትተኩሳለች፣....ቡሃቃ ሰርቆ ሲወጣ የተያዘው ሌባ በነገው ጋዜጣ ይወጣል" የሚሉ ርዕሶች ለቅስቀሳ ከተጠቀመባቸው አንዳንዶቹ ናቸው።

ድምፅ ጋዜጣ ተወዳጅ ሆነች። ለአመት አስር ሺህ ተገምቶ የነበረው የስርጭት ቁጥሯም ወደ ሰላሳ ሺህ ደረሰ።አዘጋጅዋ ጳውሎስ ኞኞም ዝናን አተረፈ። ጋዜጣዋን ለሚያሰራጩና ለሚሸጡ ወጣቶች ዩኒፎርም አሰፍቶላቸው በከተማው ደምቀውና ተለይተው እንዲታዩ አደረጋቸው።ይህ ሁኔታ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስር የነበረውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፈፅሞ እንዲወድቅና ከውድድር ውጭ እንዲሆን አደረገው።ነፃዋ "ድምፅ" አደገች፣ መንግስታዊው"ዘመን"ወደቀ።ይህ ደግሞ መንግስትንና የመንግስት ባለሥልጣኖችን አስቆጣ።ተግሳፅና ግልምጫንም አስከተለ።

በጊዜው የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ኃዋርያት በንዴት ጳውሎስ ዩኒፎርም ያለበሳቸውን ጋዜጣ ሻጮች ሰብስበው እስር ቤት አስገቡዋቸው። ጳውሎስ ምሬቱን ፅፎ በድፍረት በጋዜጣ ላይ አወጣው።"ሚኒስትሮቻችን ጋዜጣ ሻጮቻችንን እየያዙ ማሰር ጀመሩ " የሚል ፅሁፍ በጋዜጣ ላይ ተነበበ። የድምፅ ጋዜጣ ተወዳጅነትና የአዘጋጁዋ ድፍረት ያስቆጣቸው ባለሥልጣኖች ቀስ በቀስ ጋዜጣዋ ታጥፋ በማስታወቂያ ሚ/ር ስር እንድትወድቅ አደረጉ።

## ፍቅርና ትዳር

ጳውሎስ አራት ኪሎ አካባቢ ቤት ተከራይቶ ከእናቱ ጋር ሲኖር በአቅራቢያቸው አንዲት ወጣት ሴት ይመለከታል። ስሟም አዳነች ታደሰ ነው። እሷም የምትኖረው ከወላጆቿ ጋር ነበር። የአዳነች ደም ግባትና ውበት የጳውሎስን ልብ እየሰረሰረ ይገባል። በድምፅ ጋዜጣ አማካኝነት ስሙ የገነነበት ዘመን ስለነበር፣አዳነችም የጳውሎስን ማንነት አውቃ በርቀት መተያየት ይጀምራሉ።በጉርብትና የርቀት ሰላምታ ካልሆነ በስተቀር የቅርብ ግኑኝነት አልነበራቸውም። ስለ አዳነች ተወዳጅ ፀባይ ከአካባቢው የሚሰማው ሁሉ፣ በውበቷ ላይ ተጨምሮ፣ የጳውሎስን ልብ ለፍቅርና ለትዳር ያነሳሳዋል። ሆኖም ተቀራርቦ ለመጫወተወ አመቺ ሁኔታ አልነበረም።

የአዳነች አባት ይሞታሉ።ይህ አጋጣሚ ለጳውሎስ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርለታል።ቤቷ ድረስ ሰተት ብሎ ገብቶ ማስተዛዘንና ማፅናናት ይጀምራል።ሐዘኗ በረድ ሲል ካርታ ያጫውታታል። መቀላለድና መገላለፅ ይከተላል።የጳውሎስ እናትም በጉርብትናቸው መሠረት ለአዳነች ቤተሰቦች ቡና አፍልተው በማጠጣት ያፅናናሉ።የመቀራረቡ በር ከተከፈተ በኋላ ጳውሎስና አዳነች በፍቅር ይከንፋሉ።ጊዜ መስጠት አላስፈለገም።ምኑንም ምኑንም አደራርገው በ1955ዓ.ም. ወደ ትዳር ዓለም ገቡ።

ጳውሎስ ከዚህ አለም በሞት እስከተለያት ድረስ ወ/ሮ አዳነች ታደሰ ጋር በትዳር ሃያ ዘጠኝ አመት ያህል አሳልፈዋል።የትዳር ዘመናቸው የደስታ፣የፍቅር፣ የመተሳሰብና የመረዳዳት እንደነበረ ወ/ሮ አዳነች ትናገራለች።ጳውሎስም በሕይወት ዘመኑ እጅግ የሚወደው ነገር የአዳነችን ፈገግታ፣ የአዳነችን ሺሮና የአዳነችን ስም እንደነበር ይነገርለታል።በማንኛውም አጋጣሚ እንደምንም ብሎ የአዳነችን ስም በጨዋታ መሃል ያስገባል፣ ለአዳነች ያለውን ፍቅር ይገልፃል።ምግብ ሲበላ ምንግዜም የአዳነችን ጉርሻ ይጠብቃል።እሷም በጳውሎስ ላይ ሙሉ እምነትና ፍቅር ነበራት።እንደ ሚስት አፍቃሪው፣ እንደ እናት ተንከባካቢው መሆኗን ከጎረቤቶቿ ጀምሮ የሚያውቃት ሁሉ ይመሰክርላታል። እሱ ፋታ አጥቶ መፅሐፍ ሲያነብ እሷ በጉርሻ ትመግበዋለች።ፀባዩን አውቃ፣ስሜቱን ተከትላ፣ ተልዕኮውን አክብራ እስከ መጨረሻው አብራው ኖራለች።ጳውሎስ ጡረታ በወጣ ግዜ ለሽልማት ቀርቦ "በጣም የቅርብ ጓደኛህ ማነው?" ተብሎ ሲጠየቅ "የቅርብ ጓደኛዬ ሚስቴ ናት" ብሎ እሷንም አሸልሟታል።

ጳውሎስ ሌሊቱን ሲያነብ ያድራል።ይህ ሁኔታ አዳነችን መጀመሪያ ረብሿት ነበር። መብራት እያየች እንቅልፍ ስለማይወስዳት ትራሱን ፊቷ ላይ እየደፋች ትተኛም ነበር።ቀስ በቀስ ለመደችው። እንዲያውም ጳውሎስ ሌሊቱን ሲያነብ ደስ የሚል ታሪክ ካጋጠመው ከእንቅልፏ ቀስቅሶ ይነግራታል ወይም ያነብላታል። አንድ ጊዜ ደክሟት ተኝታ ጳውሎስ እንዴት አድርጎ እንደቀሰቀሳት ወ/ሮ አዳነች በትዝታ አጫወተችን፣-

"አዳነች፣ ተነሽ ተነሽ" ብሎ ይነቀንቃታል።

"እባክህ ደክሞኛል ልተኛበት" ትላለች አዳነች።

"ስለ አንድ ሀብታም ታሪክ ላነብልሽ ነው"

"ታዲያ ለኔ ምን ያደርግልኛል?.....እንቅልፌ ይበልጥብኛል "

"ታሪኩ በጣም ብዙ ሚስቶች ስለነበሩት ሀብታም ሰውዬ ነው" ሲላት ፣ አዳነች ዓይኖቿን ገልጣ ብድግ ትላለች።

"ሴቶች የሚስት ወሬ ሲነሳ አያስችላቸውም ብዬ ነው" ብሎ ጳውሎስ ቀለደባት።

ወ/ሮ አዳነች ለጳውሎስ የሙያ ረዳቱም ነበረች። በተለይ ጡረታ ለወጣ በኋላ፣ በመጨረሻው የእድሜ ዘመኑ፣ጳውሎስ በርካታ የታሪክና የምርምር ስራዎችን ለመስራት ያቀደው አዳነችን ይዞ ነበር። የሚስቱን ጡረታ አስከብሮ እሱ የሚፅፋቸውን ነገሮች ቤት ውስጥ በታይፐ እየመታችለት በመረዳዳት ለመስራት ትልቅ ዕቅድ አውጥቶ ሳይሳካ ቀረ።ጳውሎስ ቀድሞ አለፈ። "አዳነች ከእንግዲህ ሙሉ ጊዜዋን የሙያዬ ረዳት ሆና ማሳለፍ አለባት።የቤተሰብ ህይወታችንም የተረጋጋና ያማረ ይሆናል። በአመት ውስጥ ለተወሰነ ግዜ አዳነች አውሮፓን የማየት ዕድል እንዲኖራት አደርጋለሁ።የተጀመረው የፐሬስ ነፃነት በአስተማማኝ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ፣ እኔም በርካታ ስራዎቼን ለህዝብ አቀርባለሁ" እያለ ሞት ቀደመው።

## እርሙን በጊዜ......

በ1950ዎቹ ውስጥ ጳውሎስ የሶሻሊዝም አፍቃሪ ሆኖ ነበር።በየመፅሐፍቱ ያነበበው የእኩልነት፣ የፍትህና የጋራ ብልፅግና ቲዎሪ አመርቅኖት የምዕራቡን የተዛባ ስርዓት አስጠልቶት ነበር። አልፎ አልፎም በድምፅ ጋዜጣ ይህንኑ ህልሙን አስተጋብቷል። መሰረቱ ለሰው ልጆች የነበረው ፍቅርና አክብሮት ነው። በጊዜው አሜሪካ ሀገር የትምህርትና የጉብኝት ዕድል ያገኝና "አፍቃሪ ሶሻሊዝም" መሆኑ ተጠንቶ ይደናቀፍበታል። ለዚህ ማካካሻ ደግሞ የሶቪየት ኤምባሲ ለ አስራ አምስት የምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች የጉብኝት ፓስፖርት ያዘጋጅለታል። የመጀመሪያ ጉብኝቱ ወደ ሶቪየት ህብረት ይሆንና ለጉዞ ሲነሳ አምባሳደሩ የታሸገ ደብዳቤ ይሰጠዋል። ደብዳቤውን ሶቪየት ህብረት ገብቶ ከአውሮፕላን እንደወረደ ለሚቀበለው ሰው እንዲሰጥ ይታዘዛል።

ጳውሎስ ቀደም ብሎ የሩሲያኛ ቋንቋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጥናት ችሎ ነበር። የደብዳቤዋ ነገር ጉጉት ያሳድርበትና አውሮፕላኑ ውስጥ ከፍቶ ያነባታል።

"ይህ ሰው የሩሲያኛ ቋንቋ በደንብ ስለሚያውቅ አጠገቡ ምንም ዓይነት ሚስጢር እንዳታወሩ" የሚል ፅሁፍ ሆኖ ያገኘዋል። የመጀመሪያዋን ሶሻሊስት ሀገር ለመጀመሪያ ግዜ ከልቡ መጥላት ይጀምራል። ሶቪየት ህብረት ውስጥ የዜና አውታሮች ነፃ ያለመሆናቸውን ህዝቡም የውጭ ወሬ የማይደርሰው መሆኑን ሲመለከት ጥላቻው ያድጋል። በማረፊያ ሆቴሉ ውስጥ የተመደበለት አስተናጋጅ ያለ እሱ ፈቃድ መንቀሳቀስ እንደማይችል ሲነግረውና ሲከታተለው ደግሞ "አንጋፋዋ ሶሻሊስት ሀገር" ሲያል መሆኗን ይገምታል።በአይነ ቁራኛ የሚጠብቀውን ሩሲያዊ ሰላይ እንደምንም አታልሎ ወጥቶ የሕዝቡን ስሜት አጠና። በሶሻሊስት አምባገነኖች የታፈነው የሶቪየት ህዝብ ለድንች ሰልፍ ሲስገበገብ ተመለከተ። የምግብ ሸቀጥን ጨምሮ ምንም ነገር ከውጪ ወደ ሀገሪቱ እንደማይገባ አረጋገጠ።

ልቡ በጥላቻ እንደቆሰለ ወደ ቼኮዝሎቫኪያ ሄደ። እዚያም ያየው ሶቪየት ህብረት ውስጥ የጠላውን ነበር። ወደ ሃንጋሪም ሄደ። ያው ነው።ሁሉም የሶቪየት ህብረት ተቀዳሚና ተከታይ ልጆች ሆነው ህዝባቸውን ማፈናቸውን ተመለከተ። በቃው። ጉብኝቱን አቋርጦ፣ ሶሻሊዝምን ጠልቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

ሶቭየትን ከመጎብኘቱ በፊት በርዕዮተ- ዓለም የማይግባባው አንድ ጓደኛው የደጃዝማች ልጅ ነበር። ከሶቭየት ሲመለስ በቀጥታ ወደዚያው ጓደኛው ቤት ሄዶ እርቅ መሠረተ። "ከዚያ ወዲህ ስለሶሻሊዝም የሚያነበንቡት ሁሉ አይገባኝም። በጊዜ ነው እርሜን ያወጣሁት" ብሎ ጳውሎስ ራሱ አጫውቶናል።

ከብዙ አመታት በኋላ ደርግ ሶሻሊዝም አንግቦ ሲነሳ፣ጳውሎስ ሆይ ሆይታ ውስጥ ያልገባው ለዚህ ይመስላል። ደርግን በአምባገነንነት ባህሪውና በአረመኔነቱ ይጠላው ነበር። በግልፅ ሆነ በስውር ሲሰድበውና ሲጋፈጠው ኖሯል።"የሰውን ማደግ የሚጠላ ምቀኛ መንግስት ነው። እኔ ለበላሁት እሱ የሚያገሳ ይመስለኛል።" ይል ነበር አዘውትሮ።

**...........................ይቀጥላል።**

ተከታዩን በሚቀጥለው እትም ይዘን እንቀርባለን!!!!

<u>ምንጭ </u>ሩሕ ቅፅ ፩ ቁጥር 3

## የጫካውን ህልም እውን ያደረገ ጨካኝ መሪ

ገና የስልጣን ኮርቻውን ሳይፈናጠጥ የሀገሪቷን ሀብት የመበዝበዝ ፣ ሰውን፣የመግደል፣ ሀገርን ከየትና እንዴት መቁረስና መሸጥ፣ ጎሳን ከጎሳ ጋር እንዴት እንደሚያጋጭ፣ የስልጣን ዘመኔን እንዴትስ እኖራለሁ እያለ ሲነድፍ ሲያወጣና ሲያወርድ የቆየው ወያኔ/ኢ.ህአዴግ ህልሙ ተሳክቶለት የሀሳቡ ሆኖለት ይኸው አሁን በተግባር እየፈፀመና እያደረገው ይገኛል።

ታዲያ ይህንን ተግባሩን ህዝቡ እንዳይናገር፣ እንዳይፅፍ፣ ጩኸቱን እንዳያሰማ በማሰር፣ በመግደል ሌላውንም ከሀገር እንዲሰደደ በማድረግ ላይ ይገኛል። እናም በውጭም በውስጥም የምንኖር ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህንን የወያኔ አስከፊና መራራ አገዛዝ ለዓለም ህብረተሰብ ድምፃችን በማሰማት ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከወደቀችበት የወያኔ አስከፊ ስርዓት ለመታደግ ቆርጠን መነሳት ይገባናል። ዛሬ ለእምዬ ካልደረስንላት ነገ ከወያኔ የሚጠብቃት ዕጣ ሲሶ መሬት መሆን ስለሆነ ለእምዬ ኢትዮጵያ እንድረስላት።

ወገን አጥቶ ሲራብ ከማየት
ወጣኔ/ኢ.ህአዴግ ሸርፎ ሳይጨርሳት
ወገን ለወገኔ እንድረስለት
እግዚአብሔር ለሀገሬ ይስጣት በረከት
ጠላቷን ወያኔ ያንበርክክላት።

ሳሙኤል አጎናፍር

## ተስፋችን የዚች ሀገር

እንኳን ለ2001 ዓ.ም. አደረሳችሁ። አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ተስፋችን የዚች ሀገር ሕዝብ ነፃነት እና ሰላም ይናፍቀኛል። በሚቀጥሉት ብዙ ነገሮች ብዙ ተስፋዎች እንጠብቃለን።ተቃዋሚዎች በአንድነት ሁነው በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ ዴሞክራሲ እንዲመጣ እንደሚታገሉ ተስፋ አለኝ። የዚያን ያልከደም አለም ከነናችን የሚቆምበት እያለ ሰሞኑን ተረሳ ተብሎ የነዚያ የንፁህ ዜጎች ወንድሞቻችን ደም አሁንም ወያኔን እንደ ጥላ እየተከታተለው ነው።በቅርቡ እቡድ ሲናገር ደሞ አዲስ ቢል ይዘው ብቅ በማለት ለወያኔ የእንቁጣጣሽ ስጦታ አድርገውለት ራስ ምታት ሆኖበታል።ርሀብ ሌላው የወያኔ ፈተና ነው።ብቻ ምን አለፋችሁ የሰው ደም እረፍት አይሰጥም የነዚያ ወጣት ልጆች ደም የትም ቢሄድ ይፋረዳል።ደግሞ እኔን የሚናገረኝ ሰው የለም በማለት ገዥ የኢትዮጵያ መንግስት ነኝ ባዩ(ወያኔ ሻቢያ) በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች እህቶቻችንን በርካሽ ዋጋና በመጥፎ ሁኔታ ወደ ተለያዩ የዐረብ አገሮች እያጓጓዘ ይገኛል። ምን አይነት መጥፎ ዘመን ላይ እንደደረስን ያሳያል። ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገራችንን መከበሯ ቀርቶ የውርደት ሀገር ሁናለች። ገዥ ነኝ የሚለው ወያኔ ህዝባችንን መሸጥ፣ መሬታችንን መሸጥ ሆኗል ሥራው። እኔ የምለው ነገር ታዲያ ምኑ ላይ ነው ለሀገር ተቆርቋሪ መሆናቸው፣ የሚታወቀው መሬት ለባዕድ ሀገር መስጠት፣ ሴት እህቶቻችንን አሳልፎ ለዐረብ ሀገር መሸጥ ከዚህ በላይ ምን ያደርጋል? ነገ ደግሞ ሁሉም ሀገር ይሸጣል።ብቻ ይህን ከማድረጉ በፊት ፈጣሪ ከአለበት ይንቀለው።

ብቻ ምን እንላለን። እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን ይባርክልን(ለአንድነት ያድርግልን)

ዘመን ዮሐንስ

## ሀገራችንን ማዳን የምንችለው አንድ ስንሆነ ብቻ ነው።

ሁላችንም እንደምናውቀው የሀገራችን ታሪክ በጦርነት ላይ የተመሰረተ፣ ጦርነቱ የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት በማይፈልጉ የውጭ ሀይሎች ግፊት የሚደረግ ቢሆንም በሌላ መልኩ ደግሞ ለስልጣን በሚደረግ ሽኩቻ የሚከሰት ነው።ይህ ሁኔታ እስከ አሁን ድረስ ቀጥሏል። የአለመግባባት ሁኔታ ሰላምን ስለሚነሳ እድገት ብሎ ነገር የማይታሰብ ነው። አምራቹ ሀይል መሳሪያ ተሸካሚ ስለሆነ ለአገራችን ልማት መዋል የሚገባው አፍላ ጉልበት እየባከነ ነው። በፖለቲካው ችግርና በድህነት ምክንያት የ አገራችን የስራ ሃይል ወደ ወጭ መኮብለሉ አንዱ አስከፊ ውጤት ነው። የተማረ የሰው ሀይል እያጣን መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

በሀገራችን ምድር የፈለቁ ሰይጣናዊ አመለካከት ያላቸው መሪዎች በህዝብና በተማረው ክፍል ላይ እያደረሱ ያሉት ሁኔታ ከመግደል እስከ ስደት ያደርሳሉ። ከወያኔ ጋር የተባበሩ የተማሩ ክፍሎች የሉም ማለቴ አይደለም።ዛሬም ከወያኔ መሪዎች ስር የመሸጎጥ ፍላጎት ያላቸው ቢኖሩም አያስገርምም የሆዳሞች ባህርይ በመሆኑ።

ጦርነት ላንገሸገሰው ሕዝብ ሰላምን አመጣንልህ እያሉ ሰላምን የሚያሳጡ ሰልጣን መያዝ ሲጀምሩ ሀላፊነታቸውን መወጣት አቅቷቸው በጥላቻና በጎሳ ህዝብን የሚያጫርሱ መሪዎች ካየን ከጀመርን 17 አነት ሆነን። እነዚህ ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ምንም አይነት ቀና አመለካከት የሌላቸው ወያኔዎች ሀገሪቷን ከዳር እስከ ዳር እያመሷት ይገኛሉ።

ህዝባችን በሀገሩ ላይ በሰላም በነፃነት መኖር ስላልቻለ በተገኘው መንገድ ሀገሩን ትቶ የሚሄደው ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት ያስቸግራል።
ከስድስት ሚሊዮን ህዝብ በላይ በረሀብ አደጋ ላይ መሆኑን ሰምተናል።የኑሮ ውድነትም እንደ እግረ እሳት እየለበለበው ያለው ህዝባችን ኢትዮጵያ ዛሬ ምድራዊ ሲኦል ሆናበታለች።
ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ አምባገነን መሪዎች የተገነዘበው ነገር ቢኖር በዲሞክራሲያዊና በሰላም መብቱን ማስከበር እንደማይችል ያወቀ ይመስለኛል። ስለዚህ በ አምባገነኖች የተረገጠ መብታችንን ማስከበር የምንችለው ሁሉም የተቃዋሚ ሀይሎች ሀገራቸውን ከጥፋት ለማዳን ያለባቸውን ልዩነት አጥብበው ከሕዝብ ጋር በመተባበር የሚፈለግባቸውን መስዋዕትነት ለመክፈል ሲዘጋጁ ያኔ ነው የወያኔን መሪዎች አስወግዶ አንድነቷንየተከበረና ህዝቦቿ በመፈቃቀድ በመከባበር የሚኖሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት የምንችለው ሁላችንም ያለብንነ ልዩነት ወደ ጎን ትተን በጋር ሀገራችንን ለማዳን ከተነሳን በምናደርገው ትግል ሊየቆመን የሚችል ምንም ሀይል እንደሌለ ማወቅ ይኖርብናል።

ሳምሶን አበበ(Masberg)

# ከግልፍተኝነት የእንካ-ቴስታ ጸባያችን ወይንስ ከዘረኝነት ባሕሪያችን?

**ጌታቸዉ ረዳ**

*ፍምን እፍ ብትላት ትነዳለች። ትፍም ብትልባት ትጠፋለች።ሁለቱም ከ አንድ አፍ የወጡ በመሆኑ ነዉ።...መጽሐፈ ሲራክ ም/28።*

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰ የመጀመሪያዉ ሐረግ የተበደርኩት ከጦቢያ መጽሄት ነዉ።በወያኔ እና በሻዕቢያ ተፈጥሮ በነበረዉ ያፍንጫ ለፍንጫ ደም መፋሰስ ሕዘቡ ገርሞት ለጸባቸዉ የመነሾ ምክንያቶችን ሲያፈላልግ *“ከኢትዮጳየ ጠባቂዉ አምላክ ጣልቃ ገብነት አስከ ትግርኛዉ ተናጋሪዎች ደርሶ-“እንካ-ቴስታ” ግልፍተንነት ባሕሪ እንደሚሆን ምክንያቶችን ተደርድሯል...”*።ከሚለዉካነበብኩት ትዉስታ ነበር።

ህሊናቸዉ ከወገንተኝነት ረግረግ መንቀል አቅቷቸዉ ዛሬም እዛዉ የሚላወሱ ጎሳ ሙርኮኞች ገብሩ አስራትን ከኪሳቸዉ አዉጥተዉ ዋሽንግተን ድረስ አስመጥተዉ በየአሜሪካን ክፍለ ሀገሮች እያዟዟሩ ከአፈንጋጩ አፍቃሬ አንቀጽ 39ኙ እና ከተምበርካኪዉ አፈቃሬ አንቀጽ 39ኙ ከሁለት መልከ ጥፉ ዝንጅሮዎች መሃል ዛሬም ለምርጫ ዉደድር አቅርበዉልናል። አንድ ጸሃፊ እንዳሉት ሱዳኖች *“ዝንጅሮዋ በእናቷ እይታ-ሚዳቋ- ናት”*። ይላሉ፡ ያሉትን ነገር አስታወሰኝ እና ከመልከ ጡፉዎቹ አፈንጋጮቹ እና ከተምበርካኪዎቹ መልከ ጡፉዎች መሀል “ሚዳቋዉን” ገብሩ መርጠዉ አምጥተዉልን፣ ዛሬም ጠጥቁት ይሉናል። ከጦቢያ ጋር ፍቅር ያዘህሳ ባትሉኝ፡ *“ሙሻ ዘር”* በተባለዉ አምዱ ያኔ ገና ድሮ ገና ከአስራ ምናምን ዓመት በፊት የወያነዉ የኢትዮጵያ ራድዮ *“ምን እንጠይቃችሁ? የሚል ፕሮግራም ልናዘጋጅ ነዉ”* ብሎ ነበር መሰል። ጦቢያ ደግሞ *“የጠየቅነዉ መቼ ተመለሰልንና ነዉ!”* ብላ መልሳችላቸዉ ነበር። ገብሩን ጠይቁ የሚል መልክት አይቻለሁ። ከዚያም ከየት አስከ የት ባሕር ተሻግረዉ አዚህ ድረስ እኛን አክብረዉ እንድንጠይቀዎት በመምጣትዎ ምስጋናየ የላቀ ነዉ፡ እያሉ በስብሰባዉ ዉስጥ እጅ መንሳት የቀራቸዉ የዋሃንም አድመጫለሁ።

መጠየቁ መች ከፋ? የቸገረዉ ነገር የቀሳዉስቱ፣ድያቆናቱ፣የ አረጋዊያኖቹ፣ትላልቅ ባላበቶች፣ አገር ወዳድ የከተማ እና ገበሬዉ ለዓመታት ያቀረበላቸዉ ጥያቄ መቸ ተመለሰለት እና ነዉ በጥያቄ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ አቅርቡ ሚባለዉ? ምነዉ በወያኔ የተጎዱ የወያኔ ሰለባ የሆኑ ወንድም ዘመድ ወዳጅ የሉዋችሁም? በሰዉ ቁስል ላይ ግራጫ ባትሰድዱ ምናለበት? በደም መቀለድ እኮ ሃጢያት ነዉ፡ በነዚህ አን ጠየቅም ባዮች፣ የተጠለፈዉ የታረደዉ፣በእሳት የተቃጠለዉ የተገረፈዉ፣ አካለ ስንኩል የሆነዉ የነሱ ታጋይ እና ተራ ህዝብስ ምን ይለናል አትሉም? “ለሰላባዎቻቸዉ” አክብሮት ስጡ አንጂ? ፈጣሪን ፍሩ አንጂ? ከበስተጀርባ እየጨኸ ያለዉ የሙታን እና የቁም ሰለባዎች ቁጨት እና ጭሆት አስቲ ላንዳፍታ በሕሊናችሁ አስታዉስት? ዘሎ ለነገብሩ ለባለ አንቀጽ 39ኞቹ እጅ መስጠት እኮ -ለባለጌ ማራኪ እጅ ሰጥቶ የመሞትን ያህል እኮ ነዉ።ይህን እንዴት ከመቸዉ ረሳችሁት? ለባለጌዎቹ ማራኪዎች እጁን ሰጥቶ ወደ ልምና ተሰማርቶ በገዛ ራሱ አፈር ላይ የተኛዉ ለትልቁ ሰራዊት ያልሆኑትን እነ ገብሩ አስራት ለናንተ ምን ሊበጁችሁ ነዉ? ረጋ! ረጋ! የረ እስኪ ረጋ በሉ!

እስኪ ስለ እናንተዉ የዋህ አወዳሾች ኢትዮጵያዊያን መተቸቱ ወደ ጎን ልተዉ እና ወደ ዋናዉ አርዕስቴ ልመለስ። ገብሩ አስራት ዋሽንግተን ዉስጥ ስበሰባ ጠርቶ በነበረበት ዕለት የተደመጠዉ ጉዳይ ልንነጋገርበት ነዉ የተነሳሁት።አንድ ለመናገር ዕድል የተሰጠዉ ታዳሚ፣ (ተናጋሪዉ የትግርኛ ቋንቋ ተነጋሪ አይደለም- ያአማርኛም ተነጋሪም አይመስለኝም) አቶ ገብሩ በመምጣቱ እና በእዛ መድረክ ተገኝቶ ከህዘቡ ያለዉን ጥያቄ ተቀብሎ እንዲመልስ በመጋበዙ ለጋባገሮቹ እና ለገብሩ ምሰጋናዉ አቅርቦ በገብሩ ስብሰባ ላይ አትገኙ ያሉትን ወገኖች ቅስቀሳ ደግሞ ክፉኛ አዉግዞ ቁጭ አለ።

ተንጨበጨበለት። .........**ይቀጥላል**።ተከታዩን በሚቀጥለው እትም ይዘን እንቀርባለን!!!

## ትግሉን ተቀላቀል

በታሪክ ስናውቀው የኢትዮጵያ አንድነት፣
ተከብሮ ኖሯል በልጆቿ መስዋዕት።
ታዲያ የዛሬው ትውልድ አሁን ባንተ ግዜ፣
በሀገርህ ሰፍኖ ዋይታና ትካዜ።
በወያኔ ሴራ ሀገር ስትፈራርስ፣
እንዲሁ እንደዋዛ ዳር ድንበር ሲቆረስ።
በረሀብ አለንጋ ወገንህ ሲረግፍ፣
ህዝብ በበሽታ እንደ ቅጠል ሲረግፍ።
በገዛ ሀገሩ ህዝብ ባይተዋር ሁኖ፣
በወያኔ ካድሬ ልሳኑ ታፍኖ።
መኖር ሲያስመርረው በገዛ ሀገሩ፣
ፉኖ ተሠማራ በገደል በዱሩ፣
ገልብጦ ሊጥለው ወያኔን ከስሩ።
እናማ ወጣት ባላደራ አንተም በበኩልህ፣
ኢትዮጵያን ለማዳን እንደ ወገኖችህ።
ትግሉን ተቀላቀል፣
ዛሬ ነገ አትበል፣
ክንድህን አፈርጥም ወያኔን ለመጣል።

ትግስት ስዩም(Würzburg)

## የወያኔ ቅኝ ግዛት

እህል የተራበው ውዩ የተጠማው፣
ቢኮረኩሩት አይስቅ ቢናገር ድምጽ የለው።
እህልማ ሞልቷል በኢትዮጵያችን፣
ሽማግሌ አይጦር ልጅ አያድግበት በቁያችን፣
እንዳንቀሳቀስ ታስሮብን እጅና እግራችን።
አብረን ብናስወግድም የአፍሪካን ቅኝ ግዛት፣
ግና መቼ ቀረልን በወያኔ ተረግጦ መገዛት
ጤፉ፣ሽሮና በርበሬው እንዲሁም ሥጋና ቅቤው፣
እንደማይገፋ ተራራ ሽቅብ ወደላይ ዋጋው፣
እንደ አንጋጠጥን ቀረን ሆዳችን እንዳማረው።
ግን የሚደንቀው የወያኔ መፍትሄና እርምጃ፣
ክትፎ፣ ቁርጡን በልቶ ውስኪ ማወራረጃ።
ከህዲው ወያኔ ከልክ በላይ ያደለባችሁ፣
በምስኪኑ ህዝብ ንብረት የተንደላቀቃችሁ፣
ሥልጣን ያጣችሁ ቀን ምን ይላል ሆዳችሁ።
ለገንዘብ ድርጅት ላለምባንክ ንገሩ፣
ለደሀ እንዳልበጀ የሌባው ወያኔ መዋቅሩ።
ወያኔ ተንከቢሱ የበረሀው እባብ፣
ነድፎ ጨረሰው የኢትዮጵያ ህዝብ።
መንደፍ ብቻ አይደለም የወያኔ ሥራው፣
ያስራል፣ያሰቃያል ሁሌም በየጎራው።
የወያኔ ዲሞክራሲ የሀሳብ መግለፅ ነፃነት፣
እስኪናገሩ ጠብቆ እስር ቤት ማስገባት።
በቃ ተነሣ ያገር ሰው ሥንቅህን ክተትና፣
ለትግሉ ለኢትዮጵያ ነፃነት ኅዳና።

ሚኪያስ ታደሰ(Gießen)

## ይቻላል!!!!

የሠው እንባ ሰቆቃ፣
ጩኸት እሪታው ይብቃ።
የህፃናት የለቅሶ ሟይታ፣
የአዛውንት አሣዛኝ ቃስታ፣
የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ይፈታ፣
ከእውነት ይሠራ ይቅር ሀተታ።
ይብቃና ይቁም፣
ይፈታ ህልሙም፣
ይታወቅ የህይወተወ ትርጉም ፣
የኑሮ አላማም።
አፋችን ይከፈት፣
ጥርሳችን ይገለጥ ይሣቅ፣
ሌሊቱም ይንጋ ፀሀይዋም ትውጣ ትፈንጥቅ፣
ጥያቄው እንዴት ፣
አካሄዱም ወዴት?
ለሁሉም መልሱ አንድ፣
ማበር በአንድ
ይጥበቅ አይላላ የመሀላ ገመዱ፣
አንውጣ ከመስመር ከመንገዱ።
ኤሊም አንደኛ ወጣች ቀደመች ጥንቸልን፣
ይላል አይደል ተረቱ ሲያስነብበን።
ተረቱም ለኛ ፍችውም ቀላል፣
ወርቁም መልሱም ነው "ይቻላል"

ቅድስት ፀጋዬ(Alsfeld)

## ባክኖ አይቀር

መስዋዕትነታቸው ባክኖ አይቀር ፣
ተገኝቷል የተማሪው ደብተር።
ተናገሪ አንቺ የትግል አምባ፣
ድምፅሽ ይውጣ ያስተጋባ።
ሐቅ ትፌ፣
ለፍልፊ።
እኒያ ሀገር ወዳድ ወጣቶች የሞቱቱ፣
የሕዝብ ስቃይ ያሰሙቱ።
ሒያው ሆኗል ትግላቸው፣
አንግቦታል ትውልዳቸው ።

መቅደስ ኃይሌ(Korbach)

## ትንሽ ይዝናኑባት!

የጨዋታ ሰንጠረዥ ነው። ሱዶክ ይባላል። ኤዥያኖች ለጭንቅላት(ቅን ለሚያስበው) የሚሰጡት ፈተና ወይም የጭንቅላታችን መሰባስብ(consentration)መፈተኛ ጨዋታ ስለሆነ እርስዎም ይሞክሩት!
የጨዋታው ሕግ 9 ስኬሮች አሉ።ከ1-9 ያሉትን ቁጥሮች በእያንዳንዱ ስኬር መሙላት፣ አግድሞሽ ወይም

## የሠቆቃ ትዝታ

ወይ አለመታደል ይህስ የእርግማን ነው፣
እሬሳ ሻጭ ሲወርድ ሰው በላ የተተካው
አርቀው ያላዩ በወቅቱ የነበሩት፣
አላሰራ ቢሉም እርሶ እንደፈለጉት።
ጀግናው ቴዎድሮስ ምነው፣
ተራግመው የሞቱት እንደዚህ አምረው።
ግዜ አንደማይሽረው አርገው የረገሙን፣
እምዬ ቴዎድሮስ አቤት ምን አረግን።
ሀገሬ ኢትዮጵያ ብለው የሚጠሩዋት፣
ተሸርርፋ አለቀች ነጠኞች ጥሎባት።
ህዝቡም ሥቃይ አየ በጎሳ አስተዳደር፣
ወያኔ ወድቆብን መቀጫ ለሀገር።
እጅግ ያሳዝናል ተሰደን አለቅን፣
መድረሻ አሳጡን ሥቃይም በዛብን፣
በእኩይ ተግባሩ ስናማርር ደርግን።
ሀገር ሻጭ ጠበሰን ቴዎድሮስ ይሰማሉ፣
ኢትዮጵያዊ በሙሉ፣
እንደ ጨው ተበተኑ ከምናልቅ እያሉ።
ለሌላ ሀገር ሲሳይ ሆነዋል በእውነት፣
ስንት አዋቂዎች ላገር የሚጠቅሙት።
የምሁር ጠላቶች የሚተካው ሁሉ፣
አዋቂ እኛ ነን አበቃ የሚሉ።
አስራሰባት አመት ደርግ ቀለደብን፣
ጭራሰ ይባስ ብሎ ወያኔ መጣብን።
በጎጥ አስተዳደር ህዝቡም ግራ ገባው፣
የሚሆነው ጠፋው የቱን ይከተለው።
የመጣው በሙሉ ደንብ እያለ ያወጣል፣
ለኢትዮጵያ ሀገራችን እንዲያው ምን ይበጃል።
የደርግ አስተዳደር ያልጎዳው ቢኖርም፣
በስመ ኢሕአፓ ግን ምንም አልቀረውም።
ቀበሌ እንዲገድል ደርግ ባወጣው ህግ፣
ወጣቱን ጨረሱት ያሳዝናል እጅግ
የኢሕአፓ አባላትን ያለፍርድ ፈጅተው፣
የጥይቱን ዋጋ ወሰዱ አስገድደው
ሬሳም ስትቀብሩ አታልቅሱ ብሎ
ጠባቂ አቆመ ከሠፈር መልምሎ
ያጨካከናቸው ሲሰሙት ይቀፋል
ያየ ሰው ካልሆነ ለማመን ይከብዳል።
በልጅ እሬሳ ላይ እልል በሉ አሉ
የቀበሌ ጓዶች ነግ በኔ የማይሉ
እንደማያልፍ የለም ያም ቀን አለፈና፣
ሕወሐት ተተካ መች ይመጣል ደህና
በጎሳ አስተዳደር የሚያባላው ሕዝቡን
ምንም ስለ አልበቃው አድርጎ የፈለገውን
እንደ ሰንበት ዳቦ ሸራርፎ ጨረሳት
ይሉኝታ የሌለው መለስን ጥሎባት።
ሀገር ቆርሶ ሲሸጥ ለጫካ ጓደኛው
የባህር በር እንኳን አልፈለገም ሊተው
አወይ ጀግና ማጣት ላገር የሚያዝን
አስመሳይ ወያኔን የሚያስወግድልን
ደርግ ይሁን ወያኔ አልበጁም ለሀገር
ሁሉንም አየነው አይሰሩም ቁም ነገር።
መወሬ የሰከሩ እንዲያው ከንቱ ናቸው
ትልቁ አላማቸው ሀገርን መዝረፍ ነው
የተስፋ እንጀራ ዘወትር ቢያወሩም
ከምዕዋት የሚያድን ነገር አላየንም
ትልቁ ሥራቸው የተሳካላቸው
በዘር ከፋፍሎ ህዝብን ማባላት ነው።
በዚህ እኩይ ተግባር በደንብ የተካኑት
ወያኔዎች ናቸው ይነገር በእውነት
ኢሕአፓ ወይ ኦነግ ወዘተ ብለው እያወሩ
የፓርቲዎችን ስም እየደረደሩ
ማውራት መደስኮር ነው እመድረክ ላይ ወተው
መፍትሄ እንዳይጠይቅ አገሬው ሲርበው
እኛ እንዴት እናድርግ እንዴትስ እንስራ
ድርጅቶች ናቸው ያሳዩህ መከራ
እያሉ ጦር ሰብቀው ተዋጋ ለማለት ነው
የወያኔ አባላት ትልቁ ምርታቸው።
እኩይ ተግባራቸው የገባው ካገኙም
ወዲያው ከመቅስፈት ያደርጉታል ውድም
ክፉ ነው ስራቸው ከማንም አይገጥምም
በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተሰምቶ አያውቅም።
ቴዎድሮስ ይማሩን1 ወንድ ይወለድ ብለው
ወያኔን ከሥሩ ነቃቅሎ የሚጥለው።
በ እናት ኢትዮጵያ ላይ የወረደው መአት
ካልተውት በስተቀር አያልቅም ቢፅፉት
እዚህ ላይ ላቁመው ያልኩት ይበቃኛል
ለታሪክ ልተወው የቀረውን በደል።

ገነት አሰፋ(ጀርመን)

## እንዴት ነህ ወገኔ

እንዴት ነህ ወገኔ እንዴት ነህ ልበልህ፣
ረሀብ ጦርነት ሲፈራረቅብህ።
የአሁኑስ ክፉ ነው ጨካኝ አረመኔ፣
በዘር በ ሀይማኖት የሚለይ ስሙ ነው ወያኔ።
አባት የሞተበት አባቱን ቀባሪ፣
እናት የሞተበት እናቱን ቀባሪ፣
ሣይሆን በዳር ቀረ በስደት ነዋሪ።
እናት የሞተበት አያለቅስም ወይ፣
የሠው ልጅ ባገሩ ነፃነት የማያይ።
ማስ ማስ አድርገው ቀበሩት አባቱን፣
ማስ ማስ አድርገው ቀበሩት እናቱን፣
እሱን የት ይጣሉት አገር የሌለውን።
የቀበሮ ጮሌ ከ አንበሳ ሥጋ ቤት፣
ኩላሊቱን ውጦ ብልት ቢጎልበት፣
ሊያታልል ሞከረ ገብቶ በአንበሳ ቤት።

ሣራ እናውጋው (Wachtendonk)

አደራ ቅጽ ፪ ቁ.፬ ኅዳር ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.
Vol.2 No 4 November 2008

# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

FINOTE DEMOCRACY VOICE OF ETHIOPIAN UNITY

WWW. Finote.org e-mail: efdpu@aol.com

ጉዳዩ- ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮን ስለመርዳት

ይድረስ ለኢትዮጵያዊያን ወገኖች በሙሉ

በቅድሚያ የአክብሮት ሰላምታችን ይድረሳችሁ።

ለአለፉት አስር ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሀቀኛ ዜናን የማግኘት መብቱን ሲያስከብር የቆየውና የወያኔን አገዛዝ እያጋለጠ ሕዝብን ሲቀሰቅስና ለትግል ሲጠራ የነበረው ፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ ይህን ግዳጅ ሊወጣ የቻለው በሀገር ወዳድ ዜጎች ድጋፍ መሆኑን የምታውቁት ነው። በኢትዮፕያ ውስጥ ፍኖተ ዴሞክራሲን የሚያዳምጠው ሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን ታዛቢዎች መስክረዋል።በተለይም የሀገሪቷ ነፃ ጋዜጦች ከታፈኑ ወዲህ ፍኖተ ዴሞክራሲ የአንደበት አልባው ሕዝብ ልሳንና አስተማማኝ የዜና ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ የሚካድ አይደለም።

ሁላችንም እንደምናውቀው በአሁኑ ጊዜ ሀቀኛ የሕዝብ ድርጅቶችና ተቋሞችን ለማዳከም ሆነ ለማፍረስ የተቀነባበረ ሴራና ዘመቻ ተከፍቷል። በዚህም መሰረት ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማፈንና የሕዝብ ራዲዮኖችን ለመዝጋት ወይም ለመቀማት የከፋ ጥረትና እንቅስቃሴ በመካሄድ ላይ ነው። በአንፃሩ የሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት የፍኖተን የስርጭት ቀናት ከሶስት ቀን በላይ የማድረግ የበኩላችን ፍላጎት አለ። ፍኖተን ለማስቀጠልም ሆነ ይህን ዕድገት እውን ለማድረግ ደግሞ የገንዘብ እርዳታ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ከፊታችን ተደቅኗል። በመሆኑም ክቡርነትዎ የፍኖተ ዴሞክራሲን ቀጣይነት በመደገፍና ለሕዝቡም ትግልም በዚህ መስክ አስተዋፅዖ ለማድረግ የበኩሉዎን እርዳታ እንዲልኩልን በትህትና እንጠይቃለን። ሀቀኛ ዜናና መረጃ ማግኘት ከመብት አልፎ ለትግሉ በጣም ጠቃሚ ነው።

ለፍኖተ ዴሞክራሲ ቼክ ወይም መኒ ኦርድረ በሚከተለው አድራሻ ይላኩልን።

Koelner Bank eG
Account nr 451 275003
**CODE (BLZ) 37160087**
**Hohenzollernring 31--35**
**50762 Koeln, Germany.**

ወይም

በአሲምባ ድህረ ገፅ ¨www.assimba.org" ባለው ፔይ ፓል አማካኝነት ይላኩልን።

እናመሰግናለን።

በጋራ ጥረታችን ሀገራችን ትከበራለች።
ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

# ስለ ኢሕአፓ ለማወቅ የሚከተሉትን ድሕረ ገፆች ይመልከቱ።

- www.eprp.com
- www.debteraw.com
- www.assimba.org

# ራዲዮ ለማዳመጥ

- www.finote.org

# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (IEWO)

**www.ethiopianwomenorganization.com**

# ስለ ሰብዓዊ መብት በኢትዮጵያ ለማወቅ

- www.socepp.de

ሁሉም
የፖለቲካና
የሕሊና
እስረኞች
ይፈቱ!!!